አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረምረቃ ትምህርትቤት


# ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት

በ


ምሕረት ተስፋዬ


በሂውማንትስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ


ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረምረቃ ትምህርትቤት

# ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት

በ
ምሕረት ተስፋዬ

በሂውማንትስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ
ጥናታዊ ጽሑፍ

አማካሪ
ሰላማዊት መካ

ሰኔ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረምረቃ ትምህርትቤት

# ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት

በ

ምሕረት ተስፋዬ

በሂውማንትስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት

የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ

ጥናታዊ ጽሑፍ

የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

አማካሪ ____________ ፊርማ ____________

ሠርጸው ገላው

የውጭ ፈታኝ ____________ ፊርማ ____________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ርዕስ | ማውጫ | ገፅ


ምስጋና ........ i
የቁልፍ ቃላት መፍቻ ........ ii
የኢትዮጵያና የአማራ ክልል ካርታ ........ iii
የደራ ወረዳ ካርታ ........ iv
አጠቃሎ ........ v
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 2
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4
1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 4
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 5
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.6 የመረጃ አሰባሰብ እና የአጠናን ዘዴዎች ........ 6
1.6.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........ 6
1.6.2 የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 7
1.7 ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅት እና የመስክ ክንውን ........ 9
1.7.1 ቅድመ ዝግጅት ........ 9
1.7.2 የመስክ ክንውን ........ 10
1.8 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች፣ ........ 12
ምዕራፍ ሁለት ........ 13
ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ እና የገዳማቱ አጠቃላይ ገፅታ ........ 13
2.1 ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ........ 13
2.2 የገዳማቱ አጠቃላይ ገፅታ ........ 15
ምዕራፍ ሦስት ........ 26
ክለሳ ድርሳናት ........ 26
3.1. የመሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦችና ሙያዊ ቃላት ብያኔ ........ 26
3.1.1.ተረክ ........ 26
3.1.2 ሃይማኖታዊ ተረክ ........ 27
3.1.3. ቁሳዊ ባህል ........ 28
3.1.4. ቁሳዊ ባህል እና እምነት ........ 28
3.1.5. የቁሳዊ ባህል የመተንተኛ ደረጃዎች ........ 29
3.1.6. የቁሳዊ ባህል መከፋፈያ መንገዶች ........ 29
3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 30
3.2.1 በገዳማትን አመሠራረትና ፎክሎራዊ ገፅታዎቻቸው ላይ ትኩረት ያደረጉ ........ 31
3.2.2 በገዳማት አመሠራረት ላይ ብቻ ያተኮሩ ........ 33
3.2.3 በገዳማት አመሠራረት፣ እየሰጡት ካለው ጠቀሜታና የገቢ ምንጫቸውን ከማሳደግ አንፃር የተጠኑ ........ 35
3.2.4 በኢትዮጵያ ገዳማዊ ሕይወት አጀማመርና በአሁኑ ወቅት ያሉባቸውን ተያያዥ ችግሮች የተመለከቱ ........ 40

ምዕራፍ አራት ........ 43
ከጣና ቂርቆስ ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች ........ 43
4.1 ጥንታዊ፣ ቀዳሚና ከኢየሩሳሌም የመጣ መሆኑን ለማሳየት መሞከር ........ 43
4.1.1 ዋኖችን የራስ ማድረግ ........ 46
4.1.2 በስፍራው የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎችንና የሚነገሩ ተረኮችን ለዋኖቹ መስጠት ........ 46
4.2 ለዋኖች መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት፣ ........ 47
4.2.1 የቦታውን ክብር ወይም ቅድስና ለማጉላት፣ ........ 47
4.2.2 የተረኩን ተአማኒነት ለመጨመር፣ ........ 48
4.3 ተረኩን የበለጠ ተአማኒ ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው ስልቶች፣ ........ 48
4.3.1 ከዋኖቹ ጋር ተያያዥነት አላቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን ቁሳዊ ባህሎችና በዋኖቹ ተሰየሙ የተባሉትን ቦታዎች በማሳየት፣ ........ 48
4.3.2 በዋኖች አማካይነት በስፍራው ተፈፀሙ የተባሉ ተአምራትን ወይም ........ 49
ተግባራትን በመንገር፣ ........ 49
4.4 በተረኮቹ ውስጥ የዋኖቹ ተግባር፣ ........ 51
4.4.1 ዋኖቹ እንደ ስልጣን ተዋረዳቸው አንዱ ለሌላኛው መታዘዝ ፣ ........ 51
4.4.2 ዋኖቹ ስለቦታው ቅድስና እንዲናገሩ ማድረግ ........ 52
4.4.3 በዋኖቹ ስም የገዳሙን መተዳደሪያ ስርዓት ማበጀት፣ ........ 53
4.4.4 ዋኖች ገዳሙን በተደጋጋሚ እንደሚጎበኙት በመተረክ፣ ........ 54
4.4.5 ዋኖቹ ከእነርሱ በታች ላሉት ጥበቃ እና ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ማሳየት፣ ........ 56
4.4.6 ዋናው ፈጸመው ተብሎ በሚነገረው ገድል ስፍራውን ማስከበር፣ ........ 57
ምዕራፍ አምስት ........ 59
የጣና ቂርቆስ ገዳም ቁሳዊ ባህሎች ........ 59
5.1 የኦሪት መስዋዕት ማቅረቢያ ቁሶች ........ 59
5.1.1 የድንጋይ መንበር ........ 59
5.1.2 ጎሞር ........ 60
5.2 ከሥርዓተ አምልኮ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁሶች ........ 62
5.2.1 ስውሩ ቤተ መቅደስ ........ 62
5.2.2 ድንግል ማርያም አርፋበታለች የሚባለው ቦታ፣ ስዕለ አድህኖ እና ዱካዎቹ፣ ........ 65
5.2.3. የአህያዋ ሽኮና ያረፈበት ነው ተብሎ የሚታመንበት ዱካ፣ ........ 66
5.2.4. ደወል ........ 70
5.3 ገዳማውያኑ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው የሚጠቀሙባቸው ቁሶች ........ 71
5.3.1.ገዳሙ የሚጠቀምበት የሰዓት አቆጣጠር ሰንጠረዥ ........ 71
5.3.2.መሶበ ወርቅ ........ 74
5.3.3. የገዳሙ የመቅጫ ቁሶች ........ 75
5.3.3.1.በሣር ማሰር ........ 76
5.3.3.2. በእንጨት ማሰር ........ 77
5.3.3.3. በደሴት ላይ ያለች የማሰሪያ ጎጆ ........ 78
5.4. የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ሥርዓት ........ 78
5.4.1.መኮሬታ ........ 79
5.4.2.ወጥ ........ 79
5.4.3.ጭልቃ ........ 80

ማጠቃለያ ........ 81
ዋቢ ጽሑፎች ........ 83
አባሪዎች ........ i
  አባሪ አንድ ........ i
  አባሪ ሁለት ........ xv

## ምስጋና

ይህ ጥናት ከጅምሩ አንስቶ ከደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ ስህተቶቼን እየነቀሱ በማሳየትና የሚቃኑበትን መንገድ በመጠቆም፣ ያለመሰልቼት ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለረ/ፕሮፌሰር ሰላማዊት መካ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

ለጥናታዊ ጽሁፌ መሰረት የሆኑ የጽሁፍ መረጃዎችን ለሰጡኝና ለቃለ መጠይቅ ለተባበሩኝ ሁሉ ያለኝን አክብሮት በዚህ አጋጣሚ ልገልጽ እወዳለሁ። በተለይ ለዋልታንጉሥ መኮንንና ለታሪኳ ለታ ከአደረጋችሁልኝ ድጋፍ በላይ ለአሳያችሁኝ ቅንነት እግዚአብሔር ያክብርልኝ።

ትምህርት ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ ካለሽ ድርብ ኃላፊነት በተጨማሪ የእኔን ደርበሽ በመሸከም ፍላጎቴ እንዲሳካ እስከ ፍጻሜው ከጎኔ ላልተለየሽው ባለቤቴ አለምዬ የምስጋና ቃላት ያንሰኛልና የፍቅር ባለቤት እድሜና ጤና ይስጥልኝ እላለሁ። ልጄ ያሬድም ከእኔ ጋር ሊኖርህ የሚገባውን የጫወታና የጥናት ጊዜህን እንደተሻማሁብህ አውቃለሁ፤ እናም ለእኔ ስኬት የአንተም ድርሻ አለበትና አመሰግንሃለሁ።

## የቁልፍ ቃላት መፍቻ

1.መቅኑን - መስፈር፣ መለካት፣ ድርሻ

2.አበምኔት - የገዳሙ የበላይ አስተዳዳሪ (የገዳም አባት)

3.መጋቢ - በገዳሙ ውስጥ ያለውን ንብረት የሚቆጣጠርና ምግብ የሚያዘጋጅ

4.ጓል መጋቢ- በተግባር ቤት ውስጥ የመጋቢው ረዳት ሆኖ የሚያገለግል


5.ፉጋ - የገዳማዊያኑ የምግብ መቆነኛ (መቀበያ) ዕቃ፣


6.መኩሬታ - ከተለያዩ የእህል ዘሮች ተቀላቅሎ የሚጋገር የገዳማዊያኑ ምግብ

7.ተግባር ቤት - የገዳሙ የምግብ ማዘጋጃ ቤት

8. ሊቀ አበው - በገዳሙ ውስጥ ያሉትን ደካማ መነኮሳትን የሚያገለግል

## የኢትዮጵያና የአማራ ክልል ካርታ






ምንጭ፦ ሴንተራል ሴንሰስ ኤጀንሲ

የደራ ወረዳ ካርታ

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ከጣና ቂርቆስ የአባቶች እና የእናቶች የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች በመተንተን እና ቁሳዊ ባህሎቹ የሚኖራቸውን ተምሳሌት በመመርመር ላይ የተካሄደ ነው። በጥናቱ ከቤተ መጻሕፍት መረጃዎች በተጨማሪ ጥናቱ ስለሚካሄድበት አካባቢ፣ ከገዳሙ ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ተረኮች፣ በገዳሙ ውስጥ ተምሳሌትነት ስላላቸው ቁሳዊ ባህሎች በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

ለጥናቱ አስራ ሁለት መረጃ አቀባዮች የተሳተፉ ሲሆን ከእነዚህ መካከል አራቱ ቁልፍ አቀባዮች ናቸው። መረጃዎቹም በማስታወሻ፣ በፎቶ ካሜራ፣ በመቅረፀ ድምፅ ተይዘዋል። እነዚህን መረጃዎችም በገላጭ የምርምር ዘዴ፣ በተምሳሌታዊ መስተጋብራዊነት ቲዎሪ (Symbolic interactionism theory) ና በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functionalism Approaches) ለመመርመር ተሞክሯል። ከጥናቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው አስራ አምስት የመጀመሪያ ዲግሪ እና አራት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችና የጥናቱ አካባቢም ተቃኝተዋል።

በጥናቱ በዋናነት በገዳሙ የሚነገሩ ስምንት ያህል ተረኮችንና ተምሳሌትነት ያላቸውን ቁሶች ለማየት ተሞክሯል። ተረኮቹን እንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተመሳሳይነት አንዱን ከሌላው ጋር በማቀናጀት ፣ቁሳዊ ባህሎቹ ደግሞ በአገልግሎታቸው ተተንትነዋል። በውጤቱም ተረኮቹ የገዳሙን ቅድስና ከፍ የማድረግና ገዳማዊያኑን በባታቸው አጽንቶ የማቆየት ተግባር እንዳላቸው ለማሳየት ተሞክሯል። የተረኮቹ አቀራረብ በቤተክርስቲያኗ በታሪክ የሚታወቁት ዋና ዋና ቅዱሳን እና የአምልኮ ስርዓት መፈፀሚያ ቁሳዊ ባህሎች በስፍራው እንደነበሩ ማሳየት ሲሆን ገዳማዊያኑን ለማጽናት ደግሞ ስፍራው ለቅዱሳኑ ቃል ኪዳን መሰጠቱን በመተረክ፣ የገዳሙን ስርዓትም መስራታቸውን በመንገር፣ በየጊዜው በአካለ ነፍስ እየተገኙ ስፍራውን የሚጎበኙት መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ነው የተተረከው።

ቁሳዊ ባህሎቹ በአገልግሎታቸው ከአሪት አምልኮ ጋር የተያያዙ፣ ከአምልኮ ስርዓት ጋር የተሳሰሩና ገዳማውያኑ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው የሚጠቀሙባቸው ሲሆኑ የገዳሙ

ጥንታዊነትና ቅድስና ከማሳየት ባሻገር ለአምልኮ ስርዓት ማስፈጸሚያ ሆነውም እያገለገሉ መሆናቸውን ለማሳየት ተሞክሯል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጋር ተያይዞ በውጭና በአገር ውስጥ ምሁራን በርካታ የጥናት ሥራዎች ተሠርተዋል። ጥናቶቹ በጥቅሉ የሚያተኩሩት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መቼና እንዴት እንደገባ፣ በቤተክርስቲያንና በመንግስታት መካከል ስለነበረው ግንኙነት፣ በተለያየ ወቅት ቤተክርስቲያን ስላጋጠሟት ተግዳሮቶች፣ ለኢትዮጵያ ዕድገት ቤተክርስቲያን ስላደረገችው አስተዋጽኦ፣ የገዳማዊ ሕይወት አጀማመርና ስላሉባቸው ተያያዥ ችግሮች፣ ስለአብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተረኮች ላይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ በጣም ጥቂት ጥናቶች ቤተክርስቲያንን እና ገዳማትን ከፎክሎራዊ ገፅታዎቻቸው አንፃር የተመለከቱ ይገኛሉ። እነዚህ ውስን ጥናቶችም ቢሆን ትኩረታቸው በቤተክርስቲያን ንዋያተቅድሳት ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ገፅታ፣ በገዳማት የጠበል ማጥመቅ ሥነ ሥርዓት፣ የምንኩስና ሥርዓትና የገዳማውያኑ የዕለት ከዕለት ሕይወት ከትዕምርታዊነቱ አንፃር በሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ነው።

ይሁን እንጂ ከገዳማት አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች ይዘት እና የቁሳዊ ባህሎችን ተምሳሌትነት በመመርመር ላይ ያተኮረ አንድም ጥናት አላገኘሁም። ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎችን ለመተንተን ይሞክራል።

ይህ ጥናት አምስት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ ለጥናቱ መግቢያ የሚሆን ሃሣብ የቀረበበት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ ዓላማ እና ዓላማውን ለማሳካት የተነሱ ጥያቄዎችን፣ ጥናቱ የሚያተኩርባቸውን ነጥቦች፣ የመስክ ምርምሩን ሂደት፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና ችግሮቹ የተፈቱበትን መንገድ፣ መረጃ የተሰበሰበበትን ዘዴና የተሰበሰበባቸውን መሣሪያዎች፣ የመረጃ አቀባዮችን የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ መረጃዎ ቹ የተተነተኑበትን ዘዴ ወይም ስልት፣ ወዘተ. አካቶ አቅርቧል።

ምዕራፍ ሁለት ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ፣ የገዳማቱን አጠቃላይ ገፅታ እና የጣና ቂርቆስን የአንድነት ገዳም ታሪክ ዳስሷል።

በምዕራፍ ሦስት ክለሳ ድርሳን የቀረበ ሲሆን ተረክ፣ ሃይማኖታዊ ተረክ፣ ቁሳዊ ባህል፣ ቁሳዊ ባህል እና እምነት፣ የቁሳዊ ባህል የመተንተኛ ደረጃዎች እና የቁሳዊ ባህል የመከፋፈያ መንገዶች የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ተካተውበታል። ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ የሆኑ የጥናት ሥራዎች ተቃኝተውበታል። በዚህ ርዕስ ሁሉንም ጥናቶች በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተመሳሳይነት መሠረት ለጥናቱ በሚያመች መልኩ ለመመደብ ተሞክሯል። በዚህም መሠረት የገዳማትን አመሠራረትና ፎክሎራዊ ገፅታዎቻቸው ላይ ትኩረት ያደረጉ፣ በገዳማት አመሠራረት ላይ ብቻ የተጠኑ፣ በገዳማት አመሠራረት፣ እየሰጡ ካለው ጠቀሜታና የገቢ ምንጫቸውን ከማሳደግ አንፃር የተሠሩ እና በኢትዮጵያ ገዳማዊ ሕይወት አጀማመርና በአሁኑ ወቅት ያለባቸውን ተያያዥ ችግሮች የተመለከቱ በማለት ተዳሰዋል። ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ጥናት ከሌሎች ጥናቶች ጋር ያለውን ዝምድና እና ልዩነት ለማሳየት ጥረት ተደርጓል።

በምዕራፍ አራት ከጣና ቂርቆስ ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች ለመተንተን ተሞክሯል።

በምዕራፍ አምስት በገዳሙ ውስጥ ያሉት ቁሳዊ ባህሎች ተምሳሌታዊነታቸው፣ ከገዳማውያኑ ጋር ያላቸው ትስስር እና ከተረኮቹ ጋር ያላቸውን ዝምድና ለመተንተን ጥረት ተደርጓል። በመጨረሻም የጥናቱ ማጠቃለያ፣ የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር እና አባሪዎች ተካተዋል።

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ገዳማዊ ሕይወት የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው ቢባልም መቼ እና የት እንደተጀመረ የሚጠቁም መረጃ አልተገኘም፤ ይሁን እንጂ በኢስያ አገሮች የሂንዱይዝም፣ የብራሕማኒዝም፣ የቡድሂዝም እና የሺንቶይዝም ሃይማኖቶች ጥብቅ የሆነ የብሕትውና እና የምነና ኑሮ የሚኖሩ አያሌ ተከታዮች እንደነበሩአቸው ይነገራል። በሌላ በኩል በእስራኤላውያን ዘንድ በተለይ ኤሴኒሶች ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለተኛው ምእት አመት ከጨው (ሙት) ባህር በስተሰሜን ምዕራብ፣ ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ በኩል ኩምራን በሚባል ሥፍራ ገዳም መስርተው ይኖሩ ነበር። እንደ አይሁዳውያን ሁሉ በግብጽም የምነና ሕይወት የነበረ ሲሆን በተለይ ሳራፒስን (Sarapis) የሚያመልኩ ሰዎች በመመሪያ የተደገፈ የምነና ሕይወት

እንደነበራቸው ይጠቀሳል(ምክረ ሥላሴ፣ 2000:356_358፤ ተከስተ ብርሃን፣ 1995: 4-5፤ Hastings,1994:781-782)።

የብሕትውና እና የገዳም ኑሮ ከክርስቶስ ልደት በፊት በልዩ ልዩ የሃይማኖት ተቋማት ተስፋፍቶ እንደነበር ሁሉ ከክርስቶስ ልደት በኋላም በይበልጥ በክርስትና፣ በመጠኑ ደግሞ በመሐሙዳውያን[1] ሃይማኖቶች ትኩረት እንደተሠጠው ይጠቀሳል።

በክስትና ሃይማኖት የምንኩስና እና የገዳም ሐይወት አጀማመርን በተመለከተ የሚነሱ የተለያዩ ሀሳቦች አሉ። የመጀመሪያው ገዳማዊ ህይወትን የጀመረው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚል ሲሆን (ያረጋል፣1995:185) ፣ ሌላው ደግሞ በግብጻዊው አባ እንጦንስ (ከ251-356ዓ.ም) አማካይነት እንደሆነ ይነገራል (ካህሳይ፣ 2000:7)።

በኢትዮጵያም የምንኩስና እና የገዳማዊ ሕይወት የተጀመረው በዘጠኙ ቅዱሳን እንደሆነ ይነገራል። በተለይ አባ አረጋዊ[2] የምንኩስና ሥርዓት ጀማሪ ከሆኑት የአባ እንጦስ አራተኛ ትውልድ መሆናቸውይጠቀሳል (Aymro, 1970:23፤ካህሳይ፣ 2000:14-15)።

ክርስትና በኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ክስተት ብቻ ሳይሆን ለዘመናት የማህበረሰቡ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ህይወት ማዕከል ሆኖ በመቆየቱ (Sergew,1970:5) በተለይ በመንፈሳዊው ጥበብ በኩል ቅዱሳት መጻሕፍትን እና የንዋየ ቅድሳት አይነቶችን መሰረት ያደረጉ የዕደ ጥበብ እና የሥነ ጥበብ ስራዎችን በመስራት እፁብ ድንቅ ለሚባሉ ሃይማኖታዊ ቁሳዊ ባህሎች ባለቤት መሆኗ ይነገራል (ብርሃኑ፣ 1997:58)።

---

[1] መሐሙዳውያን መናንያን ደርቪሽስ (Dervishes) በመባል የሚጠሩ ሲሆን ሃያ፣ ሠላሳ እና አርባ ሆነው በሕብረት ይኖራሉ። የገዳሙ አበምኔትም ሸክ (Shaikh) በመባል ይጠራል። ደርቪሾያኑ ከሸካራ ጨርቅ የተሠራ ካባ ይለብሳሉ። አንድ ወጣኒ መናኝ ወይም ደርቪሽ የገዳሙ ቋሚ አባል ከመሆኑ በፊት አንድ ሺህ አንድ ቀናት በአመክሮ ይቆያል፤ ደርቪሾያኑ በገዳሙ ውስጥ ሲኖሩ ዱአ (ፀሎት) እና መንፈሳዊ ሽብሸባ (sacred dances) የሚያደርጉ ሲሆን አልፎ አልፎ ንስሐ ይገባሉ። ከዚህ በተጨማሪም ብቻቸውን በመተኛትና በተናጠል በመኖር በፆም ተወስነው ይኖራሉ። የመሐሙዳውያን ገዳማት በግብፅ፣ በአረብ፣ በፐርሺያና በቱርክ በስፋት ያሉ ሲሆን በተለይ ክሬት በምትባል ደሴት ብቻ ከ22 በላይ ገዳማት ይገኛሉ። (Hastings, 1994:783)

[2] እንጦንስ መቃርስንና ጳላሞንን፣ጳላሞን ጳኩሚስን፣ጳኩሚስ፣ ቴዎድሮስን፣ ቴዎድሮስ አረጋዊ ዘደብረ ዳሞን ይወልዳል (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፡906)

እነዚህን ቁሳዊ ባህሎች በማበርከቱ በኩል ደግሞ የገዳማት ድርሻ ከፍተኛ ነበር ማለት ይቻላል። ከዚህም ባሻገር በየገዳማቱ ተፈፅመዋል ተብለው የሚነገሩት ቃላዊ ተረኮች የገዳሙን ወይም የተረኩ ዋና ተዋናይ የሆነውን ሰው የቅድስና ደረጃ በሚያሳይ መልኩ የሚቀርቡ ሲሆን በገዳሙ ለሚኖሩት ገዳማዊያን እና ተረኮቹን ለሚሰሙት የእምነቱ ተከታዮች ደግሞ የራሳቸው የሆነ ፋይዳ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታሰባል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በዚህ ርዕስ ላይ ጥናት ለማድረግ ካነሳሱኝ ምክንያቶች አንዱ በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለረጅም ዘመናት በሕብረተሰቡ ዘንድ ስር ሰዶ የቆየ የእምነት ተቋም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተረኮቹንና ቁሳዊ ባህሎቹን አያይዞ ማጥናቱ ፎክሎር ለአንድ ማህበረሰብ ወይም ለተወሰነ ቡድን የሚሰጠውን ፋይዳ ለማወቅ ተገቢ ሊሆን ይችላል የሚል ሀሳብ ስለነበረኝ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ከአስር ዓመት በፊት የጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳምን ለመጐብኘት ዕድል ገጥሞኝ ሄጄ በነበረበት ወቅት በገዳማውያኑ አማካይነት የሚነገሩ ተረኮችና የአየኋቸው ቁሳዊ ባህሎች አግራሞትን ፈጥረውብኝ ስለነበር ከፎክሎር አንፃር ማጥናቱ ማህበራዊ ፋይዳ ይኖራቸው ይሆናል ከሚል እምነት በመነሳት ነው።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በገዳማውያኑ ዘንድ የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመር ይሆናል። ይህን ዋና ዓላማ ለማሳካትም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

- በገዳሙ ውስጥ ያሉት ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች የሚኖራቸውን ታሪካዊ እና ማህበራዊ ፋይዳ ለማሳየት ይሞክራል።
- የገዳሙን አመሰራረት ታሪካዊ ሁኔታ ይመረምራል።
- በገዳሙ የሚነገሩት ተረኮች እና ያሉት ቁሳዊ ባህሎች በገዳማው ያኑ ዘንድ እምነትን በመትከል እና በማጠናከር ረገድ ያላቸውን ሚና ይተነትናል።

እነዚህን ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ጥያቄዎች ቀርበዋል

- የጣና ቂርቆስ ገዳም መቼ፣ በማን፣ ለምን እና እንዴት ተመሰረተ?
- ቁሳዊ ባህሎቹ በገዳሙ ውስጥ የመገኘታቸው ትርጉም ምንድነው?
- በገዳሙ ዙሪያ የሚነገሩት ተረኮች መነሻቸው ምንድነው?
- በተረኮቹና በቁሳዊ ባህሎቹ መካከል ያለው ተያያዥነት ምን ይመስላል?
- ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ያላቸው ቁርኝት በምን አይነት መንገድ ይገለጻል?
- በገዳሙ ያሉት ቁሳዊ ባህሎች ያላቸው ተምሳሌት እና ከአምልኮ ስርዓት ጋር ያላቸው ትስስር ምን ይመስላል?

### 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ ከዓላማው የመነጨ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ታሳቢ ይደረጋል።

- ❖ ወደፊት በተለይ በሃይምኖታዊ ፎክሎር ዙሪያ ለሚሰሩ የፎክሎር ጥናቶች እንደ አንድ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል።
- ❖ በተረኮች እና በቁሶች መካከል ያለውን ተያያዥነት በማሳየት ረገድ የበኩሉን አስተዋፅኦ የደርጋል።
- ❖ ሃይማኖታዊ ተረኮች በቀጥታ ከሚያስተላልፉት መልዕክት ባሻገር የሚኖራቸውን ፍካሬያዊ ትርጉም በማሳየት ረገድ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።
- ❖ ቁሳዊ ባህሎች ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚኖራቸውን ተምሳሌታዊ ፍች በማሳየት በኩል ጥናቱ ጠቀሜታ አለው ተብሎ ይታሰባል።

### 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአማራ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን በደራ ወረዳ በጣና ሀይቅ ምስራቃዊ ጫፍ ከሚገኘው የጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች፣ በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ

ባህሎች ያላቸውን ፋይዳ መመርመር ነው። ገዳሙ የአባቶችና የእናቶች ሲሆን የእኔ ጥናት በአብዛኛው የሚያተኩረው በወንዶች ገዳም ላይ ይሆናል፤ ሆኖም ከተረኮቹ ጋር በተያያዘ በተወሰነ መልኩ ስለ እናቶች ገዳም ለማንሳት ይሞከራል። የእናቶችን (ደምበዛ ቁስቋም) ገዳም በጥናቱ በጥልቀት ለማየት ያልተቻለው ገዳሙ ከአመሠራረት ጋር ተያይዞ የሚነገሩት ተረኮች የሚያተኩሩት እና ቁሳዊ ባህሎችም ሙሉ በሙሉ የሚገኙት በአባቶች ገዳም በመሆናቸው ነው። ከዚህ ባሻገር ግን እናቶች በገዳም ውስጥ ያላቸውን የዕለት ከዕለት ሕይወት ለማየት የተደረገው ተደጋጋሚ ጥረት ወንድ ወደ ሴት በዓት አይገባም፤ ሁሉም ሥርዓት ከአባቶች ጋር ተመሳሳይ ነው በሚሉት ምክንያቶች የተነሳ የጥናቱ ወሰን በአብዛኛው በአባቶች ገዳም ላይ እንዲያተኩር ሆኗል።

## 1.6 የመረጃ አሰባሰብ እና የአጠናን ዘዴዎች

### 1.6.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ይህ ጥናት ከቤተ መጻሕፍት ከታተሙ ጽሑፎች እና ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ በመመስረት ማብራሪያ የሚሰጥ ነው። ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት ምልከታን /observation/እና ቃለመጠይቅን /interview/ መሠረት በማድረግ ነው።

አጥኚው ወደ መስክ ከመሄዱ በፊት ስለገዳም እና ስለምንኩስና ምንነት፣ ስለገዳም አመሠራረት፣ ስለቁሳዊ ባህሉና ስለመነኮሳቱ ሕይወት የተፃፉ መጻሕፍትን ከቤተመጻሕፍት በማየት መረጃዎችን ሰብስቧል። በምልከታ ደግሞ ጥናት ወደ ሚካሄድበት ስፍራም በመሄድ በገዳሙ ያሉትን ቁሳዊ ባህሎች፣ የገዳማውያኑን የዕለት ከዕለት ሕይወት ለመመልከት፣ ለመቅረፅ እና ለመመዝገብ ችሏል። ቃለመጠይቁ ደግሞ ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያያዝነት ያላቸውን ተረኮች ለመሰብሰብ፣ ስለቁሳዊ ባህሎቹ ምንነት እና አገልግሎት ለመረዳት፣ የአባላት ቅጣት፣ የምግብ አዘገጃጀትና የአመጋገብ ሥርዓት ለመገንዘብ ጠቅሟል።

### 1.6.2 የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በቃለመጠይቁ ከገዳማውያኑ መካከል የመረጃ አቀባዮችን በመምረጥ መረጃዎችን አደራጅቷል። መረጃ አቀባዮቹን ሲመርጥ በገዳሙ ያላቸውን የቆይታ ጊዜ፣ የተመደቡበትን የአገልግሎት ክፍል፣ የዕድሜ እና የመንፈሳዊ ትምህርት ደረጃ ግምት ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል። በዚሁም መሠረት በቁልፍ መረጃ አቀባይነት የገዳሙን የቅኔ መምህር፣ ዕቃ ጠባቂውን፣ ጸሓፊውን እና መጋቢውን፣ ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባይነት ደግሞ የገዳሙን ሁለት ካህናት፣ ዘበኛ፣ ከብት ጠባቂ፣ ከገዳሙ ጋር በስራ ምክንያት ጥብቅ ግንኙነት አላቸው የተባሉትን በማህበረ ቅዱሳን የሕትመትና ሚዲያ ኃላፊ፣ የአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርክ የስራ ባልደረባና የገዳሙ የልማት ኮሚቴ አባል የሆነውን፣ የክልሉን አንድ የፓርክ ባለሙያና የደራ ወረዳ ባህልና ማስታወቂያ ኃላፊን ለማነጋገር ተሞክሯል። የገዳሙ የቅኔ መምህር የገዳሙን ታሪክ ያውቃል በተባልኩት መሠረት ስለገዳሙ አመሰራረት እና ከአመሠራረቱ ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ተረኮች፣ ዕቃ ጠባቂውን የሌዊ(የሌዋውያን) ዝርያ አላቸው ተብሎ በመታመኑ ምክንያት የገዳሙን ንዋየ ቅድሳት የመጠበቅ ስልጣን ወይም ኃላፊነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተስተላለፈ እንደሚሰጣቸው ስለተነገረኝ የገዳሙን ታሪክ፣ ስርዓት እና ስለቁሳዊ ባህሎቹ፣ ጸሓፊውን ስለገዳሙ አስተዳደራዊ መዋቅር እና የምርጫ ሂደት፣ መጋቢውን ስለገዳማውያኑ የዕለት ከእለት ህይወትና የምግብ ዝግጅት፣ ካህናቱን ስለገዳሙ ስርዓት፣ ስለሰማዕቱ ቂርቆስ ገድልና ስለዘጠኙ ቤተመቅደስ፣ ዘበኛውን ስለእንግዳ አቀባበል፣ እረኛውን ወደገዳሙ የሚገቡት በሬዎች በሙሉ ለምን እንደተቀጠቀጡና የርቢ በሬ ለምን ወደ ገዳሙ እንደማይገቡ፣ የማህበረ ቅዱሳንን የህትመትና ሚዲያ ኃላፊን ስለገዳሙ ስርዓት፣ የልማት ኮሚቴ አባሉን ስለ ልማት እንቅስቃሴያቸው፣ የደራ ወረዳን የማስታወቂያና ባህል ኃላፊን ስለቁሳዊ ባህሎቹና የቦታ ስያሜዎች፣ የክልሉን የፓርክ ሰራተኛውን የገዳም ስሪት ስለአላቸውና ስለሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል።

### 1.6.3 የጥናቱ የአተናተን ዘዴ

ከፎክሎር የንድፈ ሃሳብ መሰረቶች መካከል የአንድን ስነ ቃል ማህበራዊ ፋይዳ፣ ጥቅም እና አገልግሎት ለመተንተን የሚያስችለው የተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functionallism Approaches) ነው። የዚህ ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኝ የሆነው William R.Bascom ፎክሎር የማስደሰት፣ ባህልን የመግለፅ፣ የማስተማር እና የመግታት ወይም የመቆጣጠር ተግባር እንዳለው ይገልፃል(1965፣290-294)። በዚህ ጥናትም በገዳሙ የሚነገሩት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ገዳማውያኑን በማስተማር በመግታትና በመቆጣጠር በኩል ያላቸውን ተግባር ለማሳየ ጥቅም ላይ ውሏል። እንዲሁም ሌላዎቹ ለመተንተኛነት የተጠቀምኩባቸው ዘዴዎች ተምሳሌታዊ መስተጋብራዊነት ቲዎሪ (Symbolic interactionism theory) እና ገላጭ የምርምር ዘዴዎች ሲሆኑ ተምሳሌታዊ መስተጋብራዊነት ቲዎሪን በተመለከተ (Ritezer,2000:360) ተምሳሌቶች የሰው ልጅ አንድን ነገር ከቁሳዊ እና ከማህበራዊ ጉዳይ ጋር በማያያዝ ለመሰየም፣ ለማከፋፈል እና ለማስታወስ እንዲችሉ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ቁሳዊ ባህሎቹን ለመተንተን Sclereth ዘጠኝ የቁሳዊ ባህል መፈክሪያ ስልቶች (the nine models of material culture interpretation) ብሎ ከአቀረባቸው የቁሱን ተፈጥሯዊ ውበት አመልካች፣ ተምሳሌታዊ፣ ባህል ገላጭ፣ አገልግሎት ጠቋሚ፣ የቁሱን የአሰራር ሂደት አመልካች፣ አካባቢ አመልካች፣ ባህርይ ጠቋሚ፣ ማህበረሰባዊ ተኮርና የቁሱን ማህበራዊ ታሪክ አመልካች ከሚባሉት መካከል ተምሳሌታዊ ሞዴል ቁሱ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለዬ ትርጓሜ ሲኖረው የቁሱን ተምሳሌታዊ ገጽታ ለመመርመር ስለሚያግዝና ማህበረሰባዊ ተኮር ሞዴል ደግሞ ቁሱ ለማህበረሰቡ ያለውን ሚና፣ ማህበረሰቡ ለቁሱ ያለውን አተያይ ወይም አመለካከትና በቁሱ እና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር የሚረዳ ስለሆነ ለዚህ ጥናት እንደመተንተኛ ስልት ተጠቅሜባቸዋለሁ። በሌላ መልኩ ገላጭ የምርምር ዘዴን በተለይ የቁሳዊ ባህሎቹን አጠቃላይ ገፅታ ለማሳየት ተገልግየበታለሁ።

## 1.7 ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅት እና የመስክ ክንውን

በዚህ ንዑስ ክፍል ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተደረገ ቅድመ ዝግጅት እና የመስክ ክንውን በቅደም ተከተል ለማቅረብ ይሞከራል።

### 1.7.1 ቅድመ ዝግጅት

ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ስለ ገዳማዊ ሕይወት አጀማመር፣ ስለገዳም ስሪት፣ በስነቃል ስር ስለሚጠቀሰው ስለተረክ፣ ስለ ቁሳዊ ባህል፣ ጥናቱ ስለሚካሄድበት አካባቢ እና ለጥናቱ ስለተመረጠው ገዳም የተፃፉ የተለያዩ መጻሕፍትን፣ መዝገበ ቃላትን፣ የኢንተርኔት መረጃ ምንጮችን፣ ዶክሜንተሪ ፊልሞችን፣ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፎችን እና ሌሎች ያልታተሙ የጥናት ስራዎችን ሰብስቦ ለማንበብ ጥረት ተደርጓል።

ከዚህም በተጨማሪ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ከሞላ ጎደል ለማሟላት ተሞክሯል። መጋቢት 14 ቀን 2002 ከትምህርት ክፍሉ የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ በቅድሚያ ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት በመሄድ ለደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት እንዲፃፍልኝ አስደርጊያለሁ። ከዚያም ወቅቱ ዐቢይ ፆም ስለነበር ለጥናቱ ወደ ተመረጠው ስፍራ ብሄድ ገዳማውያኑ ሱባኤ ላይ ስለሚሆኑ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ ስለተነገረኝ ዐቢይ ፆም ካለፈ በኋላ ግንቦት 18 ቀን 2002 ወደ ደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ፅ/ቤት፣ በመቀጠልም ግንቦት 19 ቀን 2002 ወደ ደራ ወረዳ ቤተክህነት ፅ/ቤት በመሄድ ለጣና ቂርቆስ የአባቶች እና የእናቶች ገዳም ደብዳቤ አስፅፌአለሁ።

ሌላው በቅድመ ዝግጅት ወቅት ገዳሙ ውስጥ ሊያገጥሙኝ የሚችሉትን ችግሮች ወይም ግራ መጋባቶች አስቀድሞ ለመቅረፍ በማሰብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከገዳሙና ከገዳሙ አባቶች ጋር ትውውቅ አላቸው ተብሎ የተነገረኝን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የማሕበረ ቅዱሳን የዋናው ማዕከል የህትመት እና ሚዲያ ሃላፊ ከሆነው ከዲያቆን ብርሃን አድማስ፣ በማህበሩ የባህርዳር ንዑስ ማዕከል አባል፣ የአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝም እና ፓርክ ቢሮ የስራ ባልደረባ እና የጣና ቂርቆስ የአባቶች እና የእናቶች የአንድነት ገዳም

የልማት ኮሚቴ አባል ከሆነው ከአቶ ብርሃኑ ደግፌ፣ ከደራ ወረዳ ባህል እና ማስታወቂያ ኃላፊ ከሆነው ከአቶ ባዘዘው መስፍን ጋር በመተዋወቅ እና የሞባይል ቁጥራቸውን በመያዝ በገዳማውያኑ ዘንድ በቀላሉ ተቀባይነት እንዲኖረኝ እና ሳይጠራጠሩ መረጃ እንዲሰጡኝ ለማድረግ ሞክሬአለሁ።

ከዚህም ባሻገር ለቤተ ክርስቲያን መሳሚያ የሚያገለግል ነጠላ፣ የሰበካ ጉባኤ መታወቂያ፣ የፀሎት መጽሐፍና ማተብ አዘጋጅቻለሁ። በቆይታዬ የገዳሙን ስርዓት ለመጠበቅ እንድችል በገዳማት ስርዓት ዙሪያ የተፃፉ መጻሕፍትን በማንበብና በዚህ ዙሪያ እውቀቱ አላቸው የተባሉ ሰዎችን በማነጋገር ልምምድ ለማድረግ ጥረት አድርጌአለሁ።

### 1.7.2 የመስክ ክንውን

ለጥናቱ ወደ ተመረጠው ስፍራ የእግር ጉዞ አድርጌ የደረስኩት ግንቦት 23 ቀን ነው። ከቦታው እንደደረስኩ የተቀበሉኝ የገዳሙ ዘበኛ ሲሆኑ ወዲያው ወደ እንግዳ ማረፊያ ቤት ወሰዱኝ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ የገዳሙ መጋቢ እና ኋል መጋቢ የገዳሙን ምግብ እና ውሃ አምጥተውልኝ እየተመገብኩ እያለ ወደ ገዳሙ ለምን እንደመጣሁ ጠየቁኝ። እኔም ገዳሙን ከአስር ዓመት በፊት መጥቼ መጎብኘቴን፣ በጉብኝቴ ወቅት ያየኋቸው ቁሶችና በአባቶች ዘንድ ሲነገሩ የሰማኋቸው ተረኮች አስደንቀውኝ ስለነበር እነዚያን ጥንታዊነት ያላቸው ተረኮችና ቁሶች ለማጥናት እንደመጣሁ በመንገር እና ከሚመለከተው አካል የተጻፉልኝን የትብብር ደብዳቤዎች በመስጠት ወደ ቦታው የሄድኩበትን አላማ በግልጽ ለማስረዳት ሞክሬአለሁ።

መጋቢው እና ኋል መጋቢው ወደ ባታቸው ከሄዱ በኋላ አስቀድሜ ከዘበኛው ጋር ቀረቤታ በመፍጠር እና ከአንዳንድ ገዳማዊያን ጋር በመቀራረብ ስለማንነቴ ስለመጣሁበት ዋና ዓላማ፣ ስለገዳሙ ታሪክ፣ ገዳሙ በየጊዜው ስለአጋጠሙት ብርቱ ችግሮች፣ በገዳሙ ተፈጽመዋል ስለሚባሉት ተአምራት፣ ስለ ገዳማዊ ሕይወት እና ፈተናዎቹ እንዲነግሩኝ በመጠየቅ፣ ከእነርሱም በኩል ለሚጠይቁኝ ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት፣ ከገዳሙ ቅጥር ውጭ ባሉት የቅዱስ ያሬድ እና የፅዮን ማርያም አብያተ ክርስቲያናት ምሽት እና ጧት ፀሎት በማድረስ የቆየሁኝ ሲሆን ግንቦት 25ቀን 2002

መጋቢው ወደ ገዳሙ ገብቼ ጥናቴን እንድጀምር ከመፍቀዳቸውም ባሻገር መረጃ እንዲሰጡኝ እና ከሌሎች መረጃ አቀባይ ገዳማውያን ጋር እንዲያገናኙኝ ከገዳሙ ፀሐፊ ጋር አስተዋወቁኝ።

በገዳሙ ቆይታየም ግንቦት 24 ቀን 2002 ከእረኛው፣ ግንቦት 25 ቀን 2002 ከገዳሙ ዕቃ ጠባቂ፣ ከፀኃፊው ከገዳሙ ዘበኛ፣ ግንቦት 26 ቀን 2002 ከመምህሩና ፣ ግንቦት 27 ቀን ደግሞ የገዳሙን የቅኔ መምህር በመያዝ በደምበዛ ቁስቋም የእናቶች ገዳም የሚገኙትን የእደ ጥበብ ውጤቶች በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሬአለሁ።

ሚያዝያ 22ቀን 2003 ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ገዳሙ የመስክ ጉዞ በማድረግ የተጓደሉትን መረጃዎች ለማሟላትና የሞከርኩ ስሆን ከመጋቢው የገዳማውያኑን የዕለት ከዕለት ሕይወት፣ የምግብ አዘገጃጀት፣ ከካህናቱ ጋር ደግሞ ስለገዳሙ ስርዓት፣ ስለ ዘጠኙ ቤተመቅደሶችና ስለ ሰማዕቱ ቂርቆስ ገድል ተጨማሪ ግብዓት አሰባስቢያለሁ።

በምልከታ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ ተሳትፏዊ ምልከታን የምመርጥበት ጊዜ ነበር። በተለይ ድንግል ማርያም አርፋባታለች ተብሎ በሚታመንበት ስፍራ፣ የድንግል ማርያም፣ የሕፃኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው የተባሉ ዱካዎች እና ስውር ቤተ መቅደስ ነው ከሚሉት ቋጥኝ ስደርስ ተንበርክኬ በመሳለም፣ ቦታውን በእጄ በመደባበስ እና ሰውነቴን በማሻሸት፣ ኃጢአተኛ መሆን እና አለመሆንን ለማረጋገጥ ያገለግላል ተብሎ የሚታመንበትን ደወል ለመሸከም በመሞከር (ተሸክሜ ማንሳት አልቻልኩም እንጂ) ተሳተፏዊ ምልከታን ተጠቅሜአለሁ።

በአጠቃላይ መረጃዎቹን በፎቶ ካሜራ፣ በመቅረፀ ድምፅና በቪዲዮ ካሜራ ቀርጫለሁ። በተለይ ወደ ገዳሙ ገብቼ መረጃ ለመሰብሰብ እስከሚፈቀድልኝ ድረስ በነበሩት ሁለት ቀናት መደበኛ ባልሆነ መ ንገድ ከገዳማውያኑ ያገኘኋቸውን መረጃዎች ወደ ማረፊያ ቤቱ ከገባሁ በኋላ በማስታወሻዬ ለማስቀረት ጥረት አድርጌአለሁ። በጥቅሉ መረጃዎቹን በአምስት የቴፕ፣ በሦስት የቪዲዮ ካሴቶች፣ በአንድ የፎቶ ፊልም ለመሰብሰብ ሞክሬአለሁ። በቴፕ የተቀረጹት ካሴቶች በሙሉ ትራንስክራይብ ተደርገው እና ፊልሞቹ ታጥበው ለጥናቱ ማስኬጃነት ውለዋል።

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች፣

ይህን ጥናት ባካሄድኩበት ወቅት የሚከተሉት ችግሮች ገጥመውኛል። የገዳሙን አበምኔት እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ ለማድረግ በእቅድ ብይዝም እኔ በሄድኩባቸው ጊዜያት በቦታው አለመገኘት፣ ከቦታው ርቀት የተነሳ እና ቶሎ ወደ ገዳሙ ለመግባት ባለመፈቀዱ ምክንያት ቻርጅ የተደረገው የፎቶ ካሜራ ባትሪው በመዘጋቱ መረጃ ቁሶቹን ለመያዝ አለመቻል፣ በሴቶች ገዳም ያሉ እናቶች ለማነጋገር ስሞክር የገዳሙ ስርዓት የማይፈቅድ በመሆኑ እናቶችን ለማነጋገር ፍቃድ አለማግኘት፣ አንዳንዶቹ ገዳማዊያን መረጃ ሲሰጡ በቴፕ ለመቀረፅ አለመፍቀድ፣ ለጥናቱ ወደ ተመረጠው ቦታ በጀልባ ለመሄድ ከዘጠኝ መቶ ብር በላይ እንድከፍል መጠየቄ፣ ከገዳሙ ድረስ ለመሄድ መንገዱን አለማወቅ፣ ለመረጃ መሰብሰቢያ የምጠቀምባቸውን እና ሌሎች ለዕለት ፍጆታ የምገለገልባቸውን ዕቃዎች ተሸክሞ ቦታው ድረስ ለመሄድ አለመቻል በዋናነት የሚጠቀሱት ናቸው። የገጠሙኝን ችግሮች ለማቃለልም የሚከተሉትን መፍትሄዎች ሰጥቻለሁ። አበምኔቱን ለማግኘት ባልችልም የእቃ ቤቱ ጠባቂ ከቅድመ አያቶቻቸው ጀምሮ በቅብብል በገዳሙ በእቃ ቤትነት ሲያገለግሉ የቆዩ እና ለገዳሙ ታሪክ እና ስርዓት ከአበምኔቱ የተሻለ እውቀት አላቸው በመባሉ ከአበምኔቱ አገኛለሁ ብዬ የአዘጋጀዋቸውን ጥያቄዎች ዕቃ ቤቱን በመጠየቅ ችግሩን ለመፍታት ችያለሁ። በባትሪ የሚሰራ ፎቶ ካሜራ አዘጋጅቼ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ገዳሙ በመሄድ የምፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሪያለሁ። በሴቶች ገዳም ያለውን ስርዓት በወንዶች ገዳም ያሉትን አባቶች በመጠየቅ ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት አድርጌአለሁ። በቴፕ ለመቀረፅ ፍቃደኛ ያልሆኑትን የመረጃ አቀባዮቹን ሐሳብ በጽሑፍ ማስታወሻ ይዣለሁ፣ ወደ ገዳሙ ለመሄድ መንገዱን ያለማወቅ እና የቁሶቹን መሸከም አለመቻል ችግር ለማቃለል መንገዱን በደንብ ያውቃል ለተባለ ሰው ገንዘብ በመክፈል ችግሩን ማቃለል ችያለሁ።

## ምዕራፍ ሁለት

## ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ እና የገዳማቱ አጠቃላይ ገፅታ

### 2.1 ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ

ጣና ሐይቅ በአማራ ብሄራዊ መንግስት በጎንደር እና በጎጃም አዋሳኝ ይገኛል። ሐይቁ የልብ ቅርፅ ያለውና በኢትዮጵያ ከሚገኙ ሐይቆች መካከል በስፋቱ የሚወዳደረው እንደሌለ በአፍሪካ ደግሞ አስረኛ እንደሆነ ይነገራል(Getnet,2005:7)። ርዝመቱ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ 80 ኪሎ ሜትር ከሰሜን ወደ ደቡብ 65 ኪሎ ሜትር ሲሆን ስፋቱ ደግሞ 3600 ካሬ ኪሎ ሜትር ነው። የጣና ሐይቅ ከባሕር ወለል በላይ በ2ሽህ 8መቶ 30 ሜትር (6ሽህ ጫማ) ይገኛል። የሐይቁ የውሃ ይዘት አራት ቢሊዮን ሜትር ኪዮብ ይደርሳል(ዘመድኩን፣ 1992:183)። ወደ ሐይቁ ከሚፈሱት ወንዞች መካከል ግልገል አባይ፣ ጉማራ፣ ርብ፣ ገልዳ እና መገጭ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ግልገል አባይ ከጣና ሐይቅ በደቡብ ምዕራብ፣ ገልዳ በደቡብ ምስራቅ፣ ጉማራና ርብ ወንዞች በምስራቅ፣ መገጭ ደግሞ በሰሜን አቅጣጫ ይገኛሉ። ከእነዚህ ወንዞች መካከል ግልገል አባይ ጣና ሐይቅን አቋርጦ ወደ ውጭ የሚፈስ ሲሆን በተለይ በክረምት ወቅት የወንዙ ቀለም ከሐይቁ የተለየ ሆኖ ጠቁሮ ይታያል( Getnet,2005:28)።

የጣና ሐይቅን በሰሜን የደንቢያ፣ በምዕራብ አላፋ ጣቁሳ፣ በደቡብ ምዕራብ አቸፈር፣ በምስራቅ ጎንደር ዙሪያ እና ፎገራ፣ በደቡባዊ ምስራቅ ደራ ወረዳዎች እና በደቡብ የባህርዳር ከተማ ያዋስኑታል።

ጣና ሐይቅ ከጥንት ጀምሮ የሚታወቅ ስለመሆኑ ኤራቶስቴነስ የተባለ የመልክዐ ምድር ሊቅ በ3ኛው ክፍለ ዘመን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እንደጻፈ፣ በጥንታዊ ግሪኮችም ዘንድ «ሴቦ» ወይም «ኮሌኤ» በመባል ይታወቅ እንደነበረና በኋላ ግን ጣና ተብሎ እንደተሰየመ ይገልፃል (ዳንኤል፣ 1999: 626)።

ጣና ተብሎ የተጠራበትን ምክንያት የተለያዩ ሰዎች የየራሳቸው አስተያየት ይሰጣሉ። (ዳንኤል፣ 1999:626) ድንግል ማርያም በስደት ዘመኗ በዳመና ተጭና በአካባቢው በመምጣቷ በዳመና ተጫነች /ተጽዕና በዳመና/ ከሚለው የመጣ እንደሆነ አለቃ አያሌው ታምሩን ዋቤ በመጥቀስ ይናገራል። ይህንን ሀሳብ በማጽናት ድንግል ማርያም

በጣና ደሴት 3ወር ከአስር ቀናት ከቆየች በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ ተገልጾ ሕጻኑን እና እናቱን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ ሲነገረው በወቅቱ ዮሴፍ ወደ ሕጻኑ ቀርቦ «ጻዕና በዳመና» በዳመና ጫናት በማለቱ በሂደት የሐይቁ ስም ጣና ተብሏል (አባ ባዬ፣ ካሴት 1A፣ ግንቦት 25ቀን 2002፣ ጣና ቂርቆስ)።

ከላይ ከተጠቀሱት አስተያየቶች ለየት ባለ መልኩ (ኪዳነ ወልድ፣1948:503) «ጠነይ፣ ዋሻ፣ ጎሬ፤ ባህር፣ኩሬ፤ ደሴት፣ የባህር ተሬ» ማለት እንደሆነና የጣና ስያሜ ም ባህርነትን፣ ርጥበትን ወይም ስፋትን የሚያሳይ መሆኑን ይጠቅሳሉ። እንደ ኪዳነ ወልድ ሁሉ ሀብተ ማርያምም ጣና የተባለው ቃል በትግርኛ ጥልቅ ማለት ሲሆን ጣነዓ ማለት ጠለቀ ወይም ወደ ባህሩ ጠልቆ ገባ ማለት እንደሆነ ይገልጻሉ (ሀብተ ማርያም፣ 1986:180)።

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት አስተያየቶች መካከል ከሐይቁ ተፈጥሯዊ ጠባይ አንጻር ይበልጥ ለሐይቁ ስያሜ የሚቀርበው በኪዳነወልድና በሀብተማርያም የተገለፁት ባህርነትን፣ ርጥበትን፣ ስፋትን እና ጥልቀትን የሚያሳዩትን ብያኔዎች መውሰዱ የተሻለ ይመስላል። የጣና አካባቢ በዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ከአክሱም ወደ ደቡብ ይካሄድ ለነበረው ንግድ ዋናው መስመር ሆኖ ማገልገሉንና አካባቢውም በ6ኛው መ.ክ.ዘ. አጋማሽ ከላስታ በመጡት የአገው ሕዝቦች ከመያዙ በፊት የጉሙዝ ሕዝቦች ይኖሩበት እንደነበር ይገለፃል(ዳንኤል፣ 1999: 627)። በሂደትም ዓምደ ፅዮን በ14ኛው ክፍለ ዘመን ወደዚህ አካባቢ ባደረገው ዘመቻ ማረፊያ ያደረገው በዚህ አካባቢ ስለነበር ክርስትናን በአካባቢው ለማስፋፋት ጥረት አድርጓል።

በተለይም በ16ኛው መ.ክ.ዘ.የመንግስቱ መናገሻ ከሸዋ ወደ ጎንደር ሲዞር የጣና ሐይቅ መንፈሳዊእና መንግስታዊ ማዕከልነቱ እያደገ እና እየጨመረ ከመሄዱ ባሻገር በደሴቶቹና በሐይቁ ዙሪያ ያሉት ገዳማትና አድባራት እየበዙ መጥተዋል (ዳንኤል፣1999:627-628)።

## 2.2 የገዳማቱ አጠቃላይ ገፅታ

በሀይቁ ውስጥ ከሚገኙት ከ37-39 ከሚደርሱት ደሴቶች እና በሀይቁ ዙሪያ ካሉት 4 የባህር ወሽመጦች(Peninsula) መካከል ከ29 በላይ አድባራት እና ገዳማት ይገኛሉ። ከደሴቶቹ መካከል ከሐይቁ በደቡብ አቅጣጫ ደብረ ማርያም፣ ክብራን ገብርኤል፣ እንጦስ ኢየሱስ፣ በደቡብ ምስራቅ ቤተ መንዞ ደሴት (ቤተክርስቲያን የሌለው)፣ ገንጃባ ሚካኤል፣ ሬማ መድኃኔዓለም፣ ሬማ ደሴት (ቤተክርስቲያን የሌለው)፣ በምስራቅ አቅጣጫ መፅሊ ፋሲለደስ፣ ወርቀቂት ደሴት (ቤተክርስቲያን የሌለው)፣ ጨቅላ መንዞ (ቤተክርስቲያን የሌለው)፣ በሰሜን ምዕራብ ደሴት ቤቴ (ቤተክርስቲያን የሌለው)፣ ፍቅር መጨረሻ(ቤተክርስቲያን የሌለው)፣ በሰሜን ምስራቅ መፅርሃ ማርያም፣ ፍቅር መፍጂያ አንድ እና ሁለት(ቤተክርስቲያን የሌላቸው)፣ በማዕከላዊ ጣና በደቅ ደሴት ላይ አርሴማ ማርያም፣ ኮታ ማርያም፣ ናርጋ ሥላሴ፣ ዝብድ መድኃኔአለም፣ ጀጋ ዮሐንስ፣ ጋዳና ዮሐንስ፣ (በዚህ ደሴት ከአቢያተ ክርስቲያናቱ በተጨማሪ ሕዝብ ይኖርበታል) ያሉ ሲሆን ዳጋ እስጢፋኖስ፣ ጎዝ አንድ እና ሁለት ደሴቶች(ቤተክርስቲያን የሌላቸው)ይገኛሉ።

በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ጎንተርጌ ቁጥር አንድ እና ሁለት(ቤተክርስቲያን የሌላቸው) ፣በሰሜናዊ አቅጣጫ በርግዳ ማርያም፣ አንጋራ ተክለሃይማኖት፣ ገሊላ ኢየሱስ፣ ደበራ ማርያም የሚባሉት ደሴቶች ቤተክርስቲያን ያላቸው ሲሆን አርባ ጉባ ደሴት፣ ደብረ ደሴት፣ ጉሉ ደሴት፣ ሊቀጉባኤ ደሴት፣ ወለተ ጴጥሮስ ደሴት፣ ገድሉ ደሴት፣ አባሳሙኤል ደሴት፣ ደሴት ጊዮርጊስ፣ ደሴት ሥላሴ፣ ተክለ ሚካኤል፣ ኢምበቴ መስቀ ል ደሴት፣ ስማኔ ደሴት፣ በቅደም ተከተል ቤተክርስተያን የሌላቸው ደሴቶች እንደሆኑ ይነገራል።

ከባህር ወሽመጦች መካከል ደግሞ በደቡብ ምዕራብ በዘጌ አዝዋ ማርያም፣ መሃል ዘጌ ጊዮርጊስ፣ ቤተ ማርያም፣ ዑራ ኪዳነ ምሕረት፣ ደብረ ሥላሴ፣ ይጋንዳ ተክለሃይማኖት እና ፎሪ ማርያም፣ በምስራቅ ደግሞ ክርስቶስ ሰምራ እና ጣና ቂርቆስ፣ በሰሜን ማንዳባ ገዳም ይገኛሉ (Getnet, 2005:18-26) ። አንዳንዶቹ ደሴቶች ድንጋያማ እና በደን የተሸፈኑ ሲሆኑ አድባራቱ እና ገዳማቱ ግን ከ700 ዓመት ዕድሜ በላይ ባላቸው ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ ቁሳዊ ባህሎች እና የመካከለኛው ዘመን

የኢትዮጵያ ነገሥታት አጽም የያዙ ናቸው (የአማራ ብሔራዊ ክልል ባሕል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣1991:63)።

በሐይቁ ክልል የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት በተመለከተ አብርሃም ሲገልፅ አንዳንዶቹን አብያተ ክርስቲያናት ገዳማት እና አድባራት ብሎ መከፋፈል የማይቻል መሆኑን፣ ይህም የሆነበት ምክንያት አብያተ ክርስቲያናቱ አስቀድመው ሲቋቋሙ በገዳም ስሪት የሚተዳደሩ የነበረ ሲሆን በሂደት ግን በኢኮኖሚ እና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች የገዳም ስሪታቸው እየጠፋ በመምጣቱ ነው ይላል (ካሴት ቁጥር 6A፣ ባህር ዳር፣ ሚያዝያ11 ቀን 2003)፤ ሆኖም ለዚህ ጥናት እስከ አሁን ድረስ የገዳም ስሪታቸውን አስከብረው ይገኛሉ ተብለው የሚታመንባቸውን ገዳማት ብቻ በመምረጥ ለማቅረብ ተሞክሯል።

በጣና ሐይቅ እና በዙሪያው ከሚገኙት ገዳማት መካከል ጣና ቂርቆስ፣ ሬማ መድኃኔዓለም፣ ዳጋ እስጢፋኖስ፣ ክብራን ገብርኤል፣ እንጦስ ኢየሱስ፣ ናርጋ ሥላሴ፣ ዑራ ኪዳነ ምሕረት፣ ምንዳባ መድኃኔዓለም እና ደብረ ገሊላ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

አብዛኞዎቹ ገዳማት «ሰባቱ ከዋክብት» በሚባል መጠሪያ ከሚታወቁት መነኮሳት ጋር የተሳሰረ ታሪክ እንዳላቸው ይነገራል። አባ ታዴዎስ ደብረ ማርያምን፣ አባ ዘዮሐንስ ክብራን ገብርኤልን፣ አባ በትረ ማርያም ዘጌን፣ አባ ኂሩተ አምላክ ዳጋ እስጢፋኖስን፣ አባ አሳይ ምንዳባን፣ አባ ዘካርያስ ደብረ ገሊላን፣ አባ ያፍቅረነ እግዚእ ደግሞ ጣና ቂርቆስን በገዳምነት እንዳፀኑ ይጠቀሳል (የአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ 1991:65)።

በኢትዮጵያ ካሉ ሐይቆች መካከል በተለይ ሰፊ ክልል ባላቸው ደሴቶች ገዳማት ወይም አድባራት ተቋቁመው ይገኛሉ ። ለዚህም ጣና ሐይቅ፣ ዝዋይ እና ሐይቅ እስጢፋኖስ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። በሐይቁ ደሴቶች ላይ ገዳማት አድባራት የሚሰሩት የየራሳቸው ምክንያት አላቸው። ከምክንያቶቹ መካከል ንዋየ ቅድሳቱን ከጠላት ለመከላከል እና ደሴቶቹ ከሰው ተገልሎ ለመኖር ወይም ለገዳማዊ ሕይወት አመች በመሆናቸው ይሆናል። በጣና ሐይቅ የሚገኙት ገዳማት የተወሰኑት ዙሪያውን በውኃ የተከበቡ ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ግማሽ አካላቸው ከየብስ ጋር የተያየዙ ናቸው። በውሃ ከተከበቡት መካከል ደብረ ገሊላ፣ ናርጋ ሥላሴ፣ ሬማ መድኃኔአለም፣ ዳጋ እስጢፋኖስ፣ ክብራን

ገብርኤል እና እንጦንስ ኢየሱስ ሲሆኑ፣ ግማሽ አካላቸው ከየብስ ጋር የተገናኙ ደግሞ ዑራኪዳነ ምሕረት፣ ምንዳባ መድኃኔአለም እና ጣና ቂርቆስ ናቸው።

ከገዳማቱ መካከል ከዳጋ እስጢፋኖስ እና ከጣና ቂርቆስ በስተቀር ሕንጻ ቤተክርስቲያናቸው ክብ ሲሆን፣ ዳጋ እስጢፋኖስና ጣና ቂርቆስ ደግሞ የመርከብና የሰቀላ(የምኩራብ) ቅርፅ አላቸው።

የጣና ቂርቆስ ገዳም ሕንፃ ቤተክርስቲያን የቫስላክ (የሰቀላ ወይም ምኩራብ) ቅርፅ ያለው ነው፤ የዚህ አይነት ቅርፅ ደግሞ በብሉይ ኪዳን ከሰሎሞን ቤተመቅደስ የተቀዳ እንደሆነ ይነገራል (ክንፈ ገብርኤል፣ 2002:49)። ምናልባት በዘመነ ኦሪት በአካባቢው ቤተ እስራኤላውያን ምኩራብ ሰርተው እና መስዋዕተ ኦሪት እየሰዉ ይኖሩ እንደነበር ከሚነገረው ጋር ተያይዞ የመጣ ሊሆን ይችላል።

የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ሕንፃ ቤተክርስቲያን መርከብ ቅርፅ የመሆኑ ምሳሌነት በኦሪት ዘፍጥረት እንደተጠቀሰው (ዘፍ.7፣1-24) በጥፋት ውሃ ዘመን የሰው ዘር በኖህ መርከብ አማካይነት መዳኑን ለማስታወስ እንደሆነ መነኮሳቱ ይናገራሉ።

የሌሎቹ በአፄ አምደፅዮን ዘመነ መንግስትእና ከዚያ ወዲህ እንደተቋቋሙ የሚነገርላቸው ገዳማት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ክብ (ቤተ ንጉሥ) ቅርፅ ያላቸው ናቸው። ክብ (ቤተ ንጉሥ)ቅርፅ ያለው ቤተ ክርስቲያን መቼ እና እንዴት እንደተጀመረ ባይታወቅም ጥንታዊ ከሆኑ አብያተ ክርስቲያናት አንድም ክብ ሆኖ የተሰራ ባለመኖሩ በሂደት የመጣ እንደሆነ ይጠቁማሉ (ክንፈ ገብርኤል፣2002:51)። ምናልባት ክብ ቤተክርስቲያን መሰራት የተጀመረው በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት ሆኖ እቅዱ የተወሰደውም በአካባቢው ከተለመደው የመኖሪያ ቤት አሰራር ይሆናል።

ሌላው በሐይቁ ባሉ አንዳንድ ገዳማት የነገሥታትን እና የገዳማቱ መስራቾች ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው መነኮሳት አፅም የተቀመጡ ሲሆን፣ በተለይም ሬማ መድኃኔዓለም፣ ዳጋ እስጢፋኖስ፣ ምንዳባ መድኃኔዓለም ገዳማት ለዚህ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። በእነዚህ ገዳማት የገዳሙ መስራች አፅም መቀመጡ ምዕመናን ወይም ገዳማውያኑ ከቅዱሱ በረከት ለማግኘት ወይም መስራቹ (ቅዱሱ ሰው) ከመሞታቸው

በፊት ለተከታዮቻቸው በቦታው እንዲቀብሯቸው በኑዛዜ ተናግረው ያንን በማክበር የተፈፀመ ይመስላል። የነገሥታቱ አፅም እና የክብር እቃ መቀመጡ ደግሞ ተክለፃድቅ(1951:182) እንደጠቀሱት በየጊዜው ለጉብኝት ከሚመጡት የሟቹ ቤተሰቦች ገዳሙ ስጦታ እንዲያገኝ አሊያም በኑዛዜ ወይም ነገሥታቱ ከመሞታቸው በፊት ለገዳሙ ያደረጉትን አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

በዚህ ጥናትም የገዳማቱን ታሪክ ተገደሙ ተብሎ በሚነገርላቸው ዘመን ቅደም ተከተል መሰረት በአጭሩ ለመጥቀስ ተሞክሯል።

በሐይቁ አካባቢ ካሉት ገዳማት መካከል ከዘመን ቅደም ተከተል አንጻር ቀዳሚ እንደሆነ የሚነገርለት ለዚህ ጥናት የተመረጠው ጣና ቂርቆስ የአባቶችና የእናቶች ገዳም ሲሆን ለጥናቱ እንዲያመች ሲባል ከሌሎች ገዳማት በስተመጨረሻ ለማቅረብ የሚሞከር ሲሆን ሌላዎቹ ግን ባላቸው ቅደም ተከተል ይቀርባሉ።

ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኘው በጣና ሀይቅ ማዕከላዊ ስፍራ ላይ ሲሆን በዐፄ ይኩኖአምላክ ዘመነ መንግስት በ1268 ዓም በአባሂሩተ አምላክ እንደተመሰረተ ይታመናል። በገዳሙ ውስጥ የዐፄ ዳዊት፣ የዐፄ ዘርያዕቆብ፣ የዐፄ ፋሲል እና የዐፄ ሱስንዮስ አፅሞች ሳይፈራርሱ ይገኛሉ። ከዚህ ባሻገር በቅፅሩ አንድ ሰፋ ያለ ጎድጓዳ ድንጋይ የሚገኝ ሲሆን የገዳሙ መስራች አባ ሂሩተ አምላክ ወደ ቦታው ሲመጡ ጣናን ለመሻገር በጀልባነት በላዩ ላይ ተቀምጠው የመጡበት ድንጋይ እንደሆነ ይታመናል። ገዳሙ ሴቶች አይገቡበትም (ዘመድኩን፣1992:205-210)።

ሌላኛው ገዳም ምንዳባ መድሃኔዓለም በጎርጎራ በኩል በሰሜናዊ የጣና ዳርቻ ላይ ከሚገኙት ገዳማት አንዱ ሲሆን ግማሽ ጎኑ በውሃ የተከበበ እና ቀሪው ክፍሉ ደግሞ ከየብስ ጋር የሚገናኝ ነው። ገዳሙን የመሰረቱት አባ አሳይ እንደሆኑ ይነገራል። አባ አሳይ ወደ ስፍራው ሲመጡ ሌሎች ባህሩን በታንኳ ሲሻገሩ እሳቸው ግን በጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ቆመው እየቀዘፉ በማለፋቸው «ማን እንደ አባ አሳይ» እንደተባለ እና ይህ አባባል በጊዜ ብዛት ተቀይሮ የቦታው መጠሪያ«ምንዳባ» ተብሎ እንደተሰየመ ይታመናል። በገዳሙ ውስጥ የአባ አሳይ ታንኳ እንደሆነ የሚታመንበት ድንጋይ እና አፅም በክብር ተቀምጦ ይገኛል። ገዳሙ ለሴቶች የተከለከለ ነው(የክልል ሦስት ቱሪዝም ቢሮ፣1986:14)።

ደብረ ገሊላ ገዳም የሚገኘው በሰሜን ጎንደር በአላፋ ጣቁሳ ወረዳ ሲሆን ገዳሙ የተመሰረተው በ14ኛው ምዕት አመት በዐፄ አምደ ፅዮን (1302-1336) ዘመነ መንግስት ነው። ገዳሙ የወንዶች ስለሆነ ሴት አይገባበትም (ዳንኤል፣1999:523)።

ክብራን ገብርኤል ገዳም በጣና ሐይቅ ደቡባዊ ዳርቻ ላይ በስተምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ  ሲሆን በዐፄ አምደ ፅዮን (1302-1336) ዘመነ መንግስት በአባ ዘዮሐንስ አማካይነት የተገደመ ነው። የገዳሙን አሰያየም  በተመለከተ የተለያዩ መላምቶች ይሰነዘራሉ። የመጀመሪያው ቅድስት ማርያምን መርቶ ወደ ጣና ደሴት ባመጣት በመልአኩ ገብርኤል እንደተጠራ የሚነገር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አባ ዘዮሐንስ ከመምጣታቸው በፊት የቦታው ባለቤቶች በነበሩት ባል እና ሚስት (ተክለ ገብርኤል እና መስቀለ ክብራ) ስም መጠራቱን፣ ሦስተኛው አባ ዘዮሐንስ ወደ ጣና ዳር ሲመጡ መጀመሪያ በተቀበሏቸው ገብርኤል እና ክብራን በተባሉ ባል እና ሚስት ተሰይሟል የሚሉት ናቸው። በገዳሙ ሴት እና ወንድ አብረው የማይኖሩ ሲሆን የዛሬው ሕንጻ ቤተክርስቲያን  እ.ኤ.አ.1682-1706 በነበሩት በእትጌ ምንትዋብ አማካይነት የተሰራ እንደሆነ ይገለፃል (የአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂ ቢሮ፣ 1991:6 5፤ዳንኤል፣1999:361)።

እንጦስ ኢየሱስ ገዳም በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት በአባ ዘዮሐንስ የተመሰረተ ሲሆን ከክብራን ገብርኤል አጠገብ የሚገኝ በጫካ የተከበበ ገዳም ነው። በዚህ ገዳም ጥንታዊ ሕንፃ የሚገኝ ሲሆን በድሮ ዘመን ነገሥታቱ ለእስራት ይጠቀሙበት እንደነበር ይታመናል። ይህ ገዳም በአሁኑ ጊዜ የሴቶች ገዳም ሆኖ ያገለግላል (Getnet, 2005:19)።

ሪማ ወይም ሬማ መድኀኔዓለም የሚገኘው በደራ ወረዳ፣ በጣና ሐይቅ ደቡባዊ አቅጣጫ ሲሆን የተመሰረተው በዐፄይስሐቅ ዘመነ መንግስት በ14ኛው ክፍለዘመን ከደብረ ሊባኖስ  በመጡ አባኖም በተባሉ መነኩሴ እንደሆነ ይጠቀሳል (ዘመድኩን፣ 1992: 236)።  ሪማ የሚባለው ስሙ የወጣው የገዳሙ መስራች አባኖም ዐፄ ይስሀቅን ቀርበው «ንጉሥ ሆይ የምንሰግድበትን ሪም ያህል መሬት ስጠኝ»በማለታቸው ምክንያት ሪም /ትንሽ/የሚለው ቃል ከጊዜ ብዛት ሪማ በመባል ገዳሙ እየተጠራ መሆኑን የገዳሙ

መነኮሳት ይናገራሉ። በሌላ መልኩ ዳንኤል ሬማ ማለት ራማ ማለት ሲሆን የሰየሙትም አባኖም መሆናቸውን ይገልጻል(1999:179)።

በገዳሙ የአባኖም፣ ታቦቱን ባርከው አስገብተዋል ተብለው የሚገመቱት የአባ በርቶሎሚዎስ፣ የዐፄ ሰርፀድንግል፣ የወለተጴጥሮስ እና የሌሎችም አፅም ሳይፈራርስ በቤተ መቅደሱ ይገኛል። በገዳሙ ካለቀፎ የሚኖር ንብ ያለ ሲሆን ገዳማውያኑ በመድህኒትነት እንደሚያገለግል ይናገራሉ (Getnet, 2005:20)።

ዑራ (ዉራ) ኪዳነ ምሕረት በዘጌ ደሴት የሚገኝ ገዳም ሲሆን የተመሰረተችው በ14ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን በገዳምነት የጸናችው በዐፄ አድያም ሰገድ እያሱ ዘመነ መንግስት (1674-1698) ነው ይባላል። ዑራ የሚለው ስያሜ የመጣው ስፍራው ገዳም ከመሆኑ በፊት በቦታው በነበረው ባላባት ስም እንደሆነ ይነገራል። ገዳሙ ለሴቶች የተፈቀደ ነው (ዘመድኩን፣1992:192-195)።

ናርጋ ሥላሴ ገዳም የሚገኘው በምዕራብ ጎጃም መስተዳድር በጣና ሀይቅ ማዕከላዊ ስፍራ በደቅ ደሴት ሲሆን የተመሰረተው (እ. ኤ. አ ከ1722-1747) በነገሠው የዐፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ እናት ንግሥት ምንትዋብ እንደሆነ ይገለፃል። ናርጋ ሥላሴ የወንዶችና የሴቶች የቁሪት ገዳም በመባል ይጠራል (የክልል ሦስት ቱሪዝም ቢሮ፣ 1986:9)።

በኢትዮጵያ በቀደምትነት ከሚጠቀሱት የአምልኮ ቦታዎች መካከል አንዱ ለዚህ ጥናት የተመረጠው ጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም ነው። የጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን በደራ ወረዳ በምስራቃዊው የጣና ጫፍ ይገኛል። ገዳሙ በክረምት ሙሉ በሙሉ በውሃ ተከቦ ደሴት ሲሆን በበጋ ወራት ግን በአንድ በኩል ከዋናው የመሬት አካል ጋር ይገናኛል። በስፍራው መስዋእተ ኦሪት መቅረብ የጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ982 ዓመት ገደማ ወይም በ4ሽህ 5 መቶ 18 ዓመተ ዓለም በቀዳማዊ ምኒልክ[3] ዘመነ መንግስት እንደሆነ ይነገራል (ዘመድኩን፣ 1992፡220)።

---

[3]. የንግሥተ ሳባና የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ በክብረ ነገሥት ላይ ስም 'በየነ ለሐኪም' ተብሏል። እዚህ ላይ... የሰሎሞን ልጅ 'ምኒልክ' የተባለበትን መመርመር የተገባ ነው። ሁሉም በሕብረት ምኒልክን፤ 'መኑ ይልህቅ' ብለው ከሁለት ላይ ይከፍሉታል። እንደዚሁም ማለት 'እንደርሱ ያለ ትልቅ ማን አለ' ማለት ነው። ይሁን እንጂ ይህ ስረ መሠረት እውነት ሊሆን አይችልም። ስለምን እንደዚህ ሩቅ በነበሩበት

የቦታውን ታሪክ ከእስራኤላዊው ንጉሥ ከሰሎሞንና ከኢትዮጵያዊቱ ንግሥት ከንግሥተ ሳባ ጋር ያቆራኙታል። በዚሁ ትረካ(ተረክ) መሰረት ንግሥተ ሳባ[4] ከእግዚብሔር የተሰጠውን የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ ሰምታ በአስቸጋሪ ጥያቄ (እንቆቅልሀ) ልትፈትነው ወደ ኢየሩሳሊም በሄደች ጊዜ ሰሎሞን በግብር ስላወቃት ምኒልክን ፀንሳ ወደ ሀገሯ ተመለሰች። ምኒልክም 22 ዓመት በሆነው ጊዜ ከኢትዮጵያዊው ነጋዴ ታምሪን ጋር ወደ አባቱ ሀገር ኢየሩሳሌም ሄደ። ሰሎሞንም ሥርዓተ መንግሥት አድርሶ ምኒልክን በኢትዮጵያ ላይ አንግሶና ከሄኖክ ጀምሮ ሰሎሞን እስከፃፋቸው ድረስ ያሉትን መጻሕፍት ሰብስቦ፣ መጻሕፍቱን ተርጉመው የሚያስተምሩ 318 ሌዋዊያን ካህናት ጨምሮ ሰጠው (የጣና ቂርቆስ  ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች የአንድነት ገዳም፣ 1992:15)።

በወቅቱም ከምኒልክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት ካህናትኦሪት እና አዛርያስ ታቦተ ፅዮንን በድብቅ ይዘው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ምኒልክም ታቦተ ፅዮንን በነገሥታቱ ቦታ በአክሱም ሊያስቀምጣት ቢፈልግም ከኢየሩሳሌም በመሰረቋ እስራኤላውያን መቃወማቸውንና መልሰውም ለመውሰድ መፈለጋቸውን በመስማቱ ለመከላከልና ለመጠበቅ ሲል ከጣና ሐይቅ መካከል ካሉት ደሴቶች የአሁኑ ጣና ቂርቆስ ገዳም ያለበትን ስፍራ በመምረጥ፣ አስቀድሞ በድንኳን በኋላም ምኩራብ ተሠርቶ መስዋዕተ ኦሪት ተጀመረ። የቦታውንም ስም "ሳፍ ፅዮን"[5] ብለው ሰየሙአት። አብሮ የመጣውንም ሕዝብ ከባህሩ ውጭ ባለው ሥፍራ አሰፈሩት። የሰፋሪዎቹ ዝርያም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በዚያው አካባቢ ነገደ እስራኤል እየተባሉ ይኖሩ ነበር።

---

ጊዜዎች አማርኛ አይነገርም ነበር። ግዕዝም ደግሞ ጥንታዊው አሁን ከሚነገረው ልዩ ነበር። እንደኛ ሐሳብ የዚህ የእውቁ ስም እውነተኛው ጥንተ መሠረት እነሆ። 'በይነ ለሐኪም፤ በዕብራይስጥ፡ የሚለውን ስም አረቦች እብን፡ ኤል፡ሐኪም፤ ያሉትን ናቸው 'የጥበብ ልጅ' የሆነውን ስም በእርግጥ ለውጠውታል። በብዙ ዘመናች ውስጥ በኢያሴዎች ጸሐፍት እጅ ሲተላለፍ ይህ ስም በይነ ለሐኪም- በን፡ ልሂክ- በን፡ሊክ- ምኒልክ ሆኖአል (ጋስፓሪኒ፣ 1948፣ 55)።

[4] .ንጉሥ ሰሎሞንን የጐበኘችው የኢትዮጵያ ንግስት ማክዳናት (ዝኒከማሁ፣ገጽ54)

[5]. ሳፍ፤(ዕብራ)፤ መድረክ። ቅድመ ሳፍ(ሕዝ41-16)። (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣ 899)።

ታቦተ ፅዮን ለስድስት መቶ አመታት በጣና ደሴት ሲቀደስባትና መስዋዕተ ኦሪት ሲቀርብባት ከኖረች በኋላ ወደ አክሱም ፅዮን ተዛውራለች (መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 3(A) ፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም፣ ግንቦት 26 ቀን 2002)።

ስፍራው በዘመነ ብሉይ ብቻ ሳይሆን በዘመነ ሐዲስም የጐላ ታሪክ እንዳለው ይነገራል። በሄሮድስ ዘመን ድንግል ማርያም፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ፣ ከሰሎሜና ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብፅ በሸሹበት በመጨረሻው የስደት ዘመናቸው ወደ ጣና የባህር ዳርቻ እንደደረሱና በደሴቲቱ የሚኖሩ ሰዎችም በደስታ ከተቀበሏቸው በኋላ ወደዚህ ለምን እንደመጡ ሲጠይቃቸው ዮሴፍም ሰማይና ምድርን የፈጠረ የእግዚአብሔርን ልዩ ሥራ እናይ ዘንድ ከኢየሩሳሌም የመጣን የገሊላ ሰዎች ነን ማለቱን፣ የደሴቶቹ አስተዳዳሪም በአሁኑ የጣና ቂርቆስ ገዳም ማረፊያ ቦታ እንደሰጣቸው ይገልፃል(ድርሳነ ኡራኤል፣ 1991:33-38)። በዚህ ቦታም3 ወር ከአስር ቀናት ከቆዩ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ሀገራችሁ ሂዱ ብሎ ስለነገረው ዮሴፍ ወደ ሕፃኑ በመቅረብ "ፀአና በደመና" በደመና ጫናት በማለቱ በሂደት የሐይቁ ስም ጣና ተብሎ እንደተጠራ ይገልጻል (ዘመድኩን፣ 1992፡224)።

በኋላም ኢዛና እና ሳይዛና (አብርሃ እና አፅብሐ) በነገሡበት ዘመን ከ325-335 ዓ.ም ጣና ደሴት ከፍተኛ የክርስትና ማስፋፊያ ማዕከል ሆኖ ነበር። አባ ሠላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬምናጦስ) በኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ ተሹሞ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከሆነው በኋላ ከአብርሃና አፅብሐ ጋር በመሆን ወደ ጣና ደሴት ሄደው በሐይቁ ላይ የሥርዓተ ጥምቀት ፀሎት ተደርሶ አብርሃና አፅብሃን፣ እንዲሁም በአካባቢው ይኖሩ የነበሩትን 10,000 ነገደ እስራኤላውያን  ወንዱን በአሁኑ በጣና ቂርቆስ ገዳም፣ ሴቱን በደምበዛ ቁስቋም የእናቶች ገዳም፣ ሕፃናቱን ደግሞ "ጨቅላ መንዞ"(የሕፃናት መርጫ ማለት ነው) ላይ አጠመቋቸው። በዚያው ቁርባኑን ሠርተውና መስዋዕቱን አዘጋጅተው የክርስቶስን ሥጋና ደም አቀበሏቸው። አብርሃና አፅብሐም የኦሪቱን ቤተ መቅደስ አፍርሰው በቦታው ላይ ቤተ ክርስቲያን እንዳሳነፁ ይነገራል። ቦታውንም አቡነ ሠላማ "ደብረ ሣህል" (የምሕረት ወይም የይቅርታ ተራራ) ብለው ሰይመውታል።

በአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግሥት ደግሞ በድንግል ማርያም አሳሳቢነት ንጉሱ፣ ቅዱስ ያሬድ፣ አባ አረጋዊና አባ ሠላማ መተርጕም መጥተው ንጉስ ለሁለተኛ

ጊዜ ቤተክርስቲያኑን ሲያሳንፅ አባ አረጋዊም በወቅቱ ለነበሩት መናንያን የምንኩስና ሥርዓት ፈፅመው ቦታውን ገዳም ማድረጋቸውን፣ ቅዱስ ያሬድም በዚያው ቦታ ለሁለት ዓመት ከስድስት ወራት ተቀምጦ የተለያዩ ፅዕዋትን በመጭመቅና በመቀመም ምልክት አልባውን የድጓ መጽሐፍ በብራና ላይ መፃፉን፣ ድጓውን ሲፅፍ ለጥቁርና ቀይ ቀለማት መበጥበጫነት ይጠቀምባቸው ነበር የሚባሉ ከድንጋይ ተቦርቡረው የተሠሩ ጉድጓዶችም በሥፍራው ይገኛሉ (ዘመድኩን፣ 1992:225) በተጨማሪም የአፄ ገ/መስቀል ካባ፣ ዙፋን እና የቅዱስ ያሬድ ካባ የሚባሉ በዕቃ ቤቱ ውስጥ በክብር ተቀምጠዋል።

አፄገብረመስቀል በጣና ደብረ ሣህል ደሴት በነበሩበት ወቅት በሀገሩ ላይ የላም በሽታ፣ የአውሬ ልክፍት፣ በረድና ንዳድ (ወባ) በርትቶ ስለነበር ቅዱስ ቂርቆስ ለእነዚህ ቸነፈሮች ቃል ኪዳን ስላለው በማለት ታቦተ ሕጉን አስገብተውታል (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡20)።

በዘመኑ ንግሥና ሲሰጥ ለንጉሱ አክሱም ፅዮን ዘውድ፣ ተድባበ ማርያም አሕዛብ የሚቀጠቀጥበትን ሰይፍ፣ መርጡለ ማርያም የንጉሡን አልባስ፣ ጣና ቂርቆስ ደግሞ በትረ መንግስቱን ይሠጡ ነበር (መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 3(B) ፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም፣ግንቦት 26፣ 2002)።

ቤተክርስቲያኑ በአፄ ካሌብ፣ በአፄ ዘርያቆብ እና በአፄ በከፋ በተደጋጋሚ የተሠራ ሲሆን በደርግ ዘመን የሳር ክዳኑ ወደ ቆርቆሮ ከመቀየሩ በስተቀር ሌላው እንዳለ የምኩራብ ቅርፅነቱን እንደያዘ ይገኛል፤ የጣና ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ከአሁን በፊት በየጊዜው በስድስት ነገሥታት ስድስት ጊዜ እንደተሠራ ይነገራል። ወደፊት ለሰባተኛ እና ለመጨረሻ ጊዜ በንጉሥ ይሠራል ተብሎ ይታመናል (ሐመር፣ 16ኛ ዓመት፣ ቁጥር 6፣ 27-28፤ አባ ባዬ፣ ካሴት 1A፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም፣ ግንቦት25፣ 2002)።

ጽላት የተቀረፀላቸው ቤተክርስቲያን በስማቸው የታነፀላቸው፣ ገድል የተጻፈላቸው እንደ ክርስቶስ ሠምራ፣ ወለተ ጴጥሮስ እና ፍቅርተ ክርስቶስ ክብር የተቀበሉት በዚህ ባለው የሴቶች ገዳም በደምበዛ ቁስቋም እነደሆነ ይገልፃል (ዘመድኩን፣ 1992፡226)።

ጣና ቂርቆስ በአፄ አምደፅዮን ዘመነ መንግስት በሐይቁ ዙሪያ ላሉ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የክርስትና ተግባራት የሚፈፀምበት ዋና ማዕከል ሆኖ አገልግሏል (Taddesse, 1972:193)።

ገዳሙ በኋለኛው ዘመን የነበረውን ክብር እያጣ የመጣ ሲሆን በተለይ በደርግ ዘመነ መንግስት መሬቱ በሙሉ በመወረሱ ምክንያት መነኰሳቱ ጥለው ወደ ሌላ ቦታ እንዲሰደዱ ሆኗል። ቀስ በቀስ ግን እንደገና እየተጠናከረ መጥቶ በአሁኑ ጊዜ ከመቶ ሰላሣ በላይ መነኰሳት በጣና ቂርቆስና በደምበዛ ቁስቋም የእናቶች ገዳም ይገኛሉ። ገዳሙ በአሁኑ ጊዜ የሚተዳደረው በሽመና፣ በጥልፍና በግብርና በሚያገኘው ገቢ ነው።

በገዳሙ ውስጥ የቅዱስ ቂርቆስ፣ የፅዮን ማርያም፣ የቅዱስያሬድ እና የቁስቋም ማርያም አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በስፍራው መሰራታቸው ፅዮን ማርያም ታቦተ ፅዮንን ለማስታወስ፣ የቅዱስ ያሬድ ደግሞ ቅዱስ ያሬድ ወደዚህ ቦታ መጥቶ ለሁለት ዓመት ኖሯል ለመባሉ፣ ቁስቋም ማርያምም ድንግል ማርያም በስደቷ ወቅት በግብፅ በደብረ ቁስቋም ቆይታለች የሚባለውን ለማዘከር ይመስላል። ከአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል የጣና ቂርቆስ ሕንጻ አሠራር የምኩራብ ቅርጽ ያለው ነው። የምኩራብ መሆኑ አንድም ጥንታዊ የኦሪት መሰዊያ እንደነበር ለመጠቆም ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ የኖህ መርከብን ለማስታወስ እንደሆነ መነኮሳቱ ይናገራሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በገዳሙ ብዙ ቁሳዊ ባህሎችም አሉ። ከነዚህም ውስጥ የኦሪት መስዋዕት ይሰዋበት የነበረ ድንጓን ችካሎች ተተክለውበት የነበሩ ጉድጓዶችና መወጠሪያ ድንጋዮች፣ የአዛሪያስ ልጅ የካህኑ የሳዶቅ መቃብር፣ የኦሪት መስዋዕት ይሰዋበት የነበረ የእንስሳቱ የደም መቀበያ ጎሞር፣ የኦሪት መስዊያ የድንጋይ መንበር፣ የሥጋው ማንጠልጠያ ሜንጦ፣ ሰባቱ መቅረዞች፣ መስዋዕቱን የሚያቀርበው ሊቀ ካህን ይለብሰው የነበረው እንደወገቡ ስፋትና ጥበት የሚስተካከል የብረት ልብስ፣ ታቦቱ የሚቀመጥበት መንበር፣ የወይፈንና የበጉን ሥጋ የሚቀበሉበት ምጣድ፣ ደሙን የሚያንጠፈጥፉበት ዕዋ፣ ሰሎሞን ለምኒልክ የሰጠው ከብርጭቆ የተሠራ የእጅ መታጠቢያ፣ በቋጥኙም ላይ የቅድስት ማርያም፣ የልጇና የአህያዋ ዱካ እና የመላዕክት አክናፍ የአረፈበት ነው

ተብሎ የሚታመንበት ቦታ፣ የቅድስት ማርያምን የስደት ጉዞ የሚያሳዩ የብራና ስዕሎች፣ ቅዱስያሬድ ድጓውን ሲፅፍ ለጥቁርና ቀይ ቀለማት መበጥበጫነት ይጠቀምባቸው ነበር የሚባሉ ከድንጋይ ተቦርቡረው የተሠሩ ጉድጓዶች፣ የቅዱስያሬድ የመጀመሪያው ምልክት አልባው ድጓ፣ የአፄ ገ/መስቀል ካባ ና ዘፋን እና የቅዱስ ያሬድ ካባ፣ ነገሥታት ሲነግሱ ይመታ የነበረ ከነሐስ የተሠራ ነጋሪትና ቀንደመለከት፣ የአፄ ገ/መስቀል አልጋ፣ ተጣጣፊ የሆነ (የአሁኑን አልበም የሚመስል) ከ30 ስዕል በላይ የያዘ የጥንት የብራና ስዕሎች፤ ነገሥታትና ካህናት ይገለገሉባቸው የነበሩ ዘውዶች፣ የአፄ አድያም ሰገድ እያሱ ካባና ዘውድ፣ የፍቅርተ ክርስቶስ መስቀል፣ የተለያዩ ጥንታዊያት ንዋያተ ቅድሳት ዋና ዋናዎቹ ናቸው(የአማራ ብሔራዊ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ፣1991:77፤ ሐመር 16ኛ አመት ቁጥር 6፡ 27-28፤ ዘመድኩን፣ 1992፡ 226-227፤ የጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992:24-25)።

## ምዕራፍ ሦስት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ከተረክ እና ከቁሳዊ ባህል ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሙያዊ ቃላት፣ ቲዮሪዎችና ጽንሰ ሀሳቦች ይብራሩበታል። በተጨማሪም ከጥናት ርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች ተዳስሰው ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው አንድነት እና ልዩነት ይቀርብበታል።

### 3.1. የመሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦችና ሙያዊ ቃላት ብያኔ

#### 3.1.1.ተረክ

ተረክ ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶችና ሁነቶች ሲፈጸሙ የሚያሳይ፣ በዝርው ወይም ግጥማዊ ባልሆነ ቋንቋ የሚቀርብ ታሪክ ነው። በትረካው ውስጥ ተለጣጣቂነትና ተያያዥነት ያላቸው ልዩ ልዩ ድርጊቶች፣ ድርጊቶቹን የሚፈጽሙ ገጸ ባህሪያት፣ ድርጊቱ የሚፈጸምበትን ቦታና ጊዜ ያሳያል። ተረክ ሲባል በእንግሊዝኛ Oral narrative የተባለውን ቃል ለመተካት ታስቦ ነው።

በሌላ መልኩ ተረክ የሰው ልጅ የጽሁፍ ጥበብ ከመጀመሩ በፊት የነበረ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ጎሳ ስለአለም አፈጣጠር (The creation of the world)፣ ስለነገሮች አመጣጥ (the origin of the things)፣ ስለእምነቱ፣ ስለባህሉ፣ ስለማንነቱ፣ ወዘተ. ለመግለጽ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው። Degh የተረክን ጥንታዊነት እና ለሰው አዕምሮ ያለውን ቀረቤታ አስመልክቶ ሲገልፅ «ተረክ ረጅም ዘመን ያለው፣ ለሰው ስሜት ቅርብ የሆነ ፣ተደማጭነት ያለው እና ከስልጣኔ ጋር አብሮ የሚጓዝ ነው» በማለት ይናገራል (1972:66)። በተመሳሳይ (ፈቃደ፣1992:52) ተረክ በማንኛውም ማህበረሰብ ያለ እና በዕለት ከዕለት ሕይወቱ የሚከውነው እንደሆነ ይገልጻል።

ተረክ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፈው በቃል ሲሆን የቆይታ ጊዜውም ረጅም ዘመናትን ሊያስቆጥር ይችላል። ይህን በተመለከተ (Vansina,1999:3) ተረክ ከሰው ወደ ሰው በቃል የሚተላለፍ ሲሆን ዕድሜውም ከአንድ ትውልድ በላይ የሚዘልቅ ሊሆን

እንደሚችል ትገልጻለች። ከአገልግሎት አንጻርም ተረክ የራሱ የሆነ አገልግሎት ያለው የፎክሎር ዘርፍ ሲሆን ተግባሩም ከፈለቀበት ማህበረሰብ ጋር የተቆራኘ ሆኖ ይታያል (Vansina,1999:101)።

አንድ ማህበረሰብ በዕለት ከዕለት ህይወቱ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱ እምነት ነው። በመሆኑም በማንኛውም የማህበራዊ ሳይንስ በተለይም በፎክሎር ጥናት መስክ የተሰማሩ ተመራማሪዎች የሰውን ልጅ አጠቃላይ ጠባይ ለመረዳት ሐይማኖትን እንደ አማራጭ ሲያዩት ቆይተዋል። የዚህ ጥናትም ትኩረት ሃይማኖታዊ ተረኮችን እና ሃይማኖታዊ ቁሳዊ ባህሎች በመተንተን ያለውን ፋይዳ ማሳየት ይሆናል።

### 3.1.2 ሃይማኖታዊ ተረክ

ሃይማኖታዊ ተረክ መፅሐፍ ቅዱስ ወደ ፅሁፍ ቋንቋነት ከመቀየሩ በፊት የነበረ እና በአማንያኑ ዘንድ ቃል በቃል ሲተላለፍ የቆየ ጥንታዊ የስነ ቃል ዘውግ እንደሆነ ሲናገር (አባይነህ፣1992:25) ፤ Degh በበኩሉ ደግሞ ሐይማኖታዊ ተረክ የመነጨው በመካከለኛው የሥነፅሁፍ ዘመን፣ በመካከለኛው ዘመን በነበረች ቤተክርስቲያን አማካይነት መሆኑን፣ ዓላማቸውም ለሀይማኖታዊ ሥነምግባር ማስተማሪያነት ማዋል ነበር። ሰባኪያን እነዚህን ተረኮች በአውደ ምህረት፣ ለተገኙት ምዕመናን ክብረ በዓላትን ለማድመቅ ሲሉ ያድሏቸው የነበረ ሲሆን የተረኮቹም ይዘት የሚያተኩረው በቅዱሳን ገድሎችና በሌሎች የሥነ ምግባር ጉዳዮች ላይ እንደነበር ይገልጻል (1972:77)።

ሃይማኖታዊ ተረኮችን ም በአንድ በኩል የክፉ አድራጊ እ ና የደግ አድራጊ፣ በሌላ መልኩ ደግሞ የመለኮታዊ ሃይልን ባህሪያትን ከፋፍሎ ለማሳየት ይጠቀሙባቸው የነበረ ሲሆን አቀራረባቸውም ፈጣሪ እና ቅዱሳኑ የጨለማውን ኃይላት ተቃዋሚ ሆነው ማቅረብ ነበር በማለት ይጠቅሳል (Degh, 1972:66)።

### 3.1.3. ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል ማህበረሰቡ በዕለት ከዕለት ሕይወቱ ውስጥ ይገለገልባቸው ዘንድ የሰራቸው ወይም ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ አሻሽሎ የሚጠቀምባቸው እንደሆኑ ይጠቅሳል(Prown ,1982:2)። ይህን ሐሳብ በማፅናት(Sims,1963:13) ቁሳዊ ባህል የተለያዩ ቅርጽ ያላቸውን ቋሚ ቁሶች ማለትም የህንጻ መሳሪያዎችን እና የመገልገያ መሳሪያዎችን፣ አላፊ ጠፊ የሆኑትን የምግብ አዘገጃጀቶችን፣ የሰውነት ማስዋቢያዎችን ወይም የወረቀት ላይ ቅቦችን የሚያካትት ነው በማለት ትጠቅሳለች። ሆኖም ከላይ ከተጠቀሱት ብያኔዎች በተለየ ሁኔታ ቁሳዊ ባህል እንደተጠኝ ቁስ ሳይሆን ራሱን የቻለ የጥናት ዘርፍ መቆጠር እንዳለበት ፈቃደ(1992:15)

> <ቁሳዊ ባህል> በዓይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሰሰውን፣ከዘመናዊ ኢንዱስት ሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰ ሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩልዩ ምግቦች አሰራርን፣ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራ ዎችን የሚከናወኑባቸውን መሳሪያዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል።

በማለት ይገልጻል። እነዚህን ሁለት ብያኔዎች በአጣጣመ መልኩ ቁሳዊ ባህል እንደ ተጠኚ ቁስ ብቻ ሳይሆን እንደ ጥናት ዘርፍም መቆጠር እንደሚገባው Prown (1982:1) ቁሳዊ ባህል ማለት ማህበረሰቡ በዕለት ከዕለት ሕይወቱ የሚጠቀምባቸውን ቁሶች የሚመለከት ብቻ ሳይሆን በቁሶቹ አማካይነት የአንድን የተወሰነ ሕብረተሰብ ወይም ማህበረሰብ የእምነት እሴቶች፣ ሐሳቦች፣ ዝንባሌዎችን እና አመለካከቶችን የሚያጠና የጥናት ዘርፍ እንደሆነ ይገልፃል።

### 3.1.4. ቁሳዊ ባህል እና እምነት

ቁሳዊ ባህል እምነትን ለመግለፅ ያገለግላሉ። ይህን በተመለከተ Jones (2000:9) ቁሳዊ ባህል የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን እምነት ያንጸባርቃል በማለት ይጠቅሳል። በተመሳሳይ መልኩ Oring (1986, 207) ቁሶች ከእምነት ጋር ሊያያዙ እና ሐይማኖታዊ ተሞክሮዎችንም ሊያሳዩ ይችላሉ በማለት ቁሶች እና እምነቶች ያላቸውን ተዛምዶ ይናገራል።

ከዚህ በተጨማሪ ሃይማኖታዊ ትውፊቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ ቁሳዊ ባህል እንደሆነ ይገለፃል (ማህበረ ቅዱሳን፣1986:15)።

በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት ትኩረትም ከሃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቁሳዊ ባህሎች በመተርጎም በገዳማውያኑ ዘንድ ያላቸውን ፋይዳ መመልከት ይሆናል።

### 3.1.5. የቁሳዊ ባህል የመተንተኛ ደረጃዎች

የቁሳዊ ባህል የመተንተኛ ደረጃዎችን በተመለከተ Prown ቁሳዊ ባህልንን ለመተንተን ሦስት ደረጃዎች ያስፈልጋሉ በማለት ይናገራል። የመጀመሪያው ገለጻ (Description) ሲሆን አጥኚው በገለፃው የቁሱን አጠቃላይ ገፅታ በአካል ተገኝቶ ለአልተመለከተ ሰው በምስል ከሳች ቃላት አማካይነት እንደሚያየው አድርጎ ማቅረብ ነው። ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ ትርጓሜ (Deduction) ነው። ተመራማሪው በቁሱ ተገልጋይ እና በቁሱ መካከል ያለውን መስተጋብር መፈከር ይሆናል ሦስተኛው እና የመጨረሻው ደረጃ ግምታ (speculation) ሲሆን ቁሳዊ ባህሉን የሚያጠናው አካል ከላይ በተጠቀሱት ደረጃዎች ያገኘውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ቁሱን በውጫዊ መረጃዎች ወይም ትወራዎች መመርመር ይሆናል በማለት ይገልጻል(Prown,1982:7)።

### 3.1.6. የቁሳዊ ባህል መከፋፈያ መንገዶች

ቁሳዊ ባህልን በየምድባቸው ከፋፍሎ ማጥናት አስፈላጊ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ቢስማሙም ከፋፍሎ ለማጥናት ግን አስቸጋሪ እንደሆነ ይናገራሉ(Prown,1982:2 ;Ames,1982:20)። እንደ Prown አባባል ቁሳዊ ባህልን ለማጥናት ቁሱ የተሰራበትን መሰረት በማድረግ፣ የአሰራር ጥበቡን በመመርኮዝ፣ አገልግሎቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ማጥናት እንደሚቻል ገልፆ ከሶስቱ የመከፋፈያ ዘዴዎች የተሻለ የሚሆነው አገልግሎቱን በመመርኮዝ የሚደረግ ክፍፍል እንደሆነ ይጠቁማል(Prown,1982:2)። Ames በበኩሉ ቁሳዊ ባህልን በቅርጽ፣ በአገልግሎት፣ በተሰራበት ነገር፣ በዘመን፣ በባለሙያውና በአሰራር ጥበቡ ከፋፍሎ ማጥናት እንደሚቻል ጠቅሶ የተሻለው ግን ከአንድ በላይ የመከፋፈያ ስልቶችን መጠቀም እንደሆነ ይመክራል (1978:20)። ምሁራኑ እንደ ተናገሩት ቁሶቹን ከፋፍሎ ለማጥናት ሲሞከር አንዱ ቁስ ለብዙ

አገልግሎቶች መዋሉ፣ ከተለያዩ ነገሮች መሰራቱ፣ የአሰራር ጥበቡን ለያይቶ ማስቀመጥ ማስቸገሩ፣ በዘመን ከፋፍሎ ለማሳየትም ቁሱ በእርግጥ የተሰራበትን ጊዜ ለማወቅ ማዳገቱ፣ በባለሙያ ለመከፋፈል ቢታሰብም ባለሙያው ከሌላ ሰው ጋር በጋራ የሚሰሯቸው ቁሶች ሊኖሩ መቻላቸው፣ በቅርፅ ለመከፋፈል ቢሞከርም ብዙዎቹ ቁሶች ተመሳሳይ ቅርፅ ባለመኖራቸው በምድብ በምድብ ማስቀመጥ የማይቻል መሆኑ አስቸጋሪ ቢያደርገውም ይህ ጥናት ግን ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ቁሶች ዙሪያ በመስክ መረጃ በምሰበሰብበት ወቅት በአገልግሎት ከፋፍሎ ቢያጠና አንዱ ቁስ ለብዙ አገልግሎት እንደማይውል በመረዳቱ ቁሶቹን ከአገልግሎት አንፃር ከፋፍሎ ለማሳየት ይሞክራል።

ጥናቱ ተረኮችን ወይም ቁሳዊ ባህሎቹን አያይዞ የተነሳበት ዋናው ምክንያት ቁሳዊ ባህሎቹ በተረኮቹ የሚገለፁ በመሆናቸው አንዱን ከሌላው ለያይቶ ለማጥናት ጥናቱ ጎደሎ ይሆናል ከሚል ስጋት ነው (Sims, 1953:17-18)።

## 3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በ«የጣና ቂርቆስ ገዳም አመሠራረት፣ ከአመሰራረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች» ላይ የተደረገ ጥናት አልተገኘም። ሆኖም በመነሻነት ያገለግሉኝ ዘንድ አስራ አምስት የመጀመሪያ ዲግሪ እና አራት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች በድምሩ አስራ ዘጠኝ ተዛማጅ ጥናቶች ተቃኝተዋል። በቅኝቱ የተካተቱት ጥናቶች በተለይ ከገዳማት አመሰራረት ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ላይ የተጠኑትን ብቻ በመምረጥ ነው። በጥናቱ ከተካተቱት አስራ ዘጠኝ ተዛማጅ ጥናቶችም መካከል አስራ አንዱ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ አምስቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በታሪክ የትምህርት ክፍል፣ ሦስቱ ደግሞ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የትምህርት ክፍል ለድህረ ምረቃ የተሠሩ ናቸው።

ሁሉንም ጥናቶች በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተመሳሳይነት መሠረት ለጥናቱ በሚያመች መልኩ ለመመደብ ተሞክሮአል። በዚህም መሠረት የገዳማትን አመሠራረትና ፎክሎራዊ ገፅታዎቻቸው ላይ ትኩረት ያደረጉ፤ በገዳማት አመሠራረት ላይ ብቻ የተጠኑ፤ በገዳማት አመሠራረት፣ እየሰጡ ካለው ጠቀሜታና የገቢ ምንጫቸውን

ከማሳደግ አንፃር የተሠሩ እና በኢትዮጵያ ገዳማዊ ሕይወት አጀማመርና በአሁኑ ወቅት ያለባቸውን ተያያዥ ችግሮች የተመለከቱ በማለት ለማቅረብ ተሞክሮአል። በተመሳሳይ ዘመን ከተጠኑት በስተቀር አቀራረባቸው እንደተጠኑበት ዘመን ቅደም ተከተል ነው።

### 3.2.1 በገዳማትን አመሠራረትና ፎክሎራዊ ገፅታዎቻቸው ላይ ትኩረት ያደረጉ

ታደሰ አይችሉህም (1999)፣ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ስርዓት እና የገዳማዊያኑ የዕለት ከዕለት ሕይወት ከትምዕርታዊነቱ አንፃር በዝቋላ አቡነ በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ኃይማኖት እና ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳማት" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ አቅርቧል። ጥናቱ "የተቋሙን አስተዳደራዊ አደረጃጀት፣ የገዳማውያኑን የስራ ክፍልና አይነት፣ የአለባበስ እና የፆም ስርዓት ምን እንደሚመስል በመመልከት ከትምዕርታዊነቱ አንፃር አገናዝቦ ማቅረብ" የሚሉ ነጥቦችን በአላማነት ይዟል። ታደሰ በሥራው የእንግዶችና የአዳዲስ አባላት አቀባበል፣ የምንኩስና አቀባበል ስርዓት፣ የግጭት አፈታት፣ የገዳማውያኑ አለባበስ፣ የመነኰሳቱ ጡረታና ዕረፍት፣ የመነኰሳቱ ግንዘት፣ ፀሎተፍትሀት እና ግብአተመሬት የሚሉትን ርዕሰ ጉዳዮች አካቷል።

አጥኚው የምንኩስና አቀባበል ስርዓት፣ የገዳማውያኑን አለባበስ፣ የስራ ክፍፍል እና አይነት ቢገልፅም በተለይ ከገዳማቱ አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች ባለማየቱ ከእኔ ጥናት ይለያል፤ ሆኖም ከገዳማዊያኑ አለባበስ ጋር የተያያዙ ቁሳዊ ባህሎችን ከትዕምርታዊነታቸው አንፃር በመመልከቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም የእኔ ትኩረት ከገዳማዊያኑ አለባበስ ጋር በተያያዙ ቁሳዊ ባህሎች ላይ ባለመሆኑ በጥናት ዘዴው ላይ እንጂ ከቁሶቹ አንጻር አይመሳሰልም።

ፍሬሕይወት ባዩ (2000)፣ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ አቅርባለች። ጥናቱ "የንዋያተ ቅድሳቱን ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ ለመመልከት" የሚል አላማ ይዞ ተነስቷል። ፍሬ ሕይወት ለጥናቷ በናሙናነት የመረጠቻቸው ከአርሲ ሀገረ ስብከት የሊሙና ቢል ቢሎ ወረዳ በቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስና ሊሙ ማርያም፣ ከአዲስ አበባ ደግሞ

ርዕስ አድባራት እንጦጦ ማርያምና ገነተ ፅጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ናቸው። በጥናቱ "ንዋየ ቅድሳት" የሚለው ስያሜ የተሠጠበት ምክንያትና ከሌሎች መሰል ዕቃዎች በምን እንደሚለይ፣ የንዋየ ቅድሳቱ የሚሰሩበት ጥሬ ዕቃና አሠራራቸው፣ መስራት የተጀመሩበት ዘመን፣ አሁን የያዙትን ቅርፅ ለምን እንደያዙ፣ ቀለማቸው ለምን የተወሰነ እንደሆነ፣ የቀለማቸው ተምሳሌትና አሁን ያሉበትን ሁኔታ ለመተንተን ተሞክሯል። በተጨማሪም የንዋያተ ቅድሳቱ የቁሳዊ ባህል፣ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ሀገረሰባዊ ልማድ ገፅታዎች በዝርዝር ቀርበዋል።

በጥናቱ ምንም እንኳን የንዋያተ ቅድሳቱን ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታዎችን ለመመልከት ቢሞከርም ለናሙና የተመረጡትን አብያተ ክርስቲያናት ብቻ መርጦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ ብሎ ማቅረቡ አግባብነት ያለው አይመስለኝም። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ጥናት በተረክ እና በቁሳዊ ባህል ላይ ያተኮረ ባለመሆኑ ከእኔ ጥናት ይለያል። በሌላ መልኩ ለጥናቱ ናሙናነት የተመረጡትም አቢያተ ክርስቲያናት ከገዳም ይልቅ የደብር ስሪት ያላቸው ናቸው።

ወርቁ ከተማ (2000) "የሌሙና ቢል ቢሎ ወረዳ፣ የጨፋ መድሃኔዓለም፣ ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም አመሠራረት ፎክሎራዊ ገጽታ" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ አቅርቧል። ጥናቱ "የገዳሙን አመሠራረት በገዳሙ ውስጥ በፈለቀው ፀበል የማጥመቅ ሥነ ሥርዓትና በገዳሙ የሚኖሩት መነኰሳት የሚፈፅሙአቸውን ፎክሎራዊ ገፅታዎች ማሳየት" የሚል ዓላማ የያዘ ነው።

ወርቁ በሥራው በገዳሙ አመሠራረት ሂደት የተከናወኑ ድርጊቶች፣ ለገዳሙ መመሥረት ምክንያት የሆኑ ነገሮች፣ ገዳሙ በአካባቢው በመመሥረቱ እያበረከተ ያለው ማህበራዊና ልማታዊ አስተዋጽኦ፣ ገዳሙ በተመሠረተበት አካባቢ ከአህመድ ግራኝ ወረራ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ሥነ ቃሎች በገዳሙ ፀበል በማጥመቅ ሥነ ሥርዓትና መነኰሳቱ በገዳማዊ ኑሯቸው የሚፈፅሟቸው ፎክሎራዊ ክንዋኔዎችን ዘርዝሯል።

አጥኚው ከላይ የተጠቀሱትን ርዕሰ ጉዳዮች ለመተንተን ቢሞክርም ትኩረቱ በገዳሙ ጠበል፣ ጠበል በሚያጠምቁትና በሚጠመቁ ሰዎች የሚፈፀሙ ፎክሎራዊ ገጽታዎች ላይ እንጂ ከገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ያላቸውን ፍካሬያዊ ፍች እና በገዳሙ ያሉ ቁሳዊ ባህሎች የሚኖራቸውን ተምሳሌታዊ ትርጉም ስላላየ ከእኔ ጥናት ይለየዋል።

### 3.2.2 በገዳማት አመሠራረት ላይ ብቻ ያተኮሩ

ኃይለማርያም አሰፋ (1991) ፣ "The Addis Ababa GenataIyasus Monastry" በሚል ርዕስ በታሪክ ክፍለ ትምህርት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። ጥናቱ ገዳሙ ከመመሥረቱ በፊት ዕለቱ የነበረበት ቦታ፣ ራስ ካሣ አሁን ባለበት ቦታ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ያነሳሳቸው ምክንያት፣ ቤተክርስቲያኑ ወደ ገዳም እንዴት እንደተቀየረ፣ በጣሊያን ወረራ ወቅት ስለደረሰበት አደጋ እና ስለገቢ ምንጩ በስፋት ያትታል።

አጥኚው በሥራው ስለገዳሙ አመሠራረት፣ ገዳም ከመሆኑ አስቀድሞ ስለነበረው ሁኔታ እና ስለገቢ ምንጩ ቢገልፅም ገዳሙ የሕግ ገዳም በመሆኑ ከአንድነት (ንፍሮ) ገዳም የተለየ ነው። በተጨማሪም አጥኚው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ያላቸውን ፋይዳ አላየም።

ሀብታሙ መንግስቴ (1998) "Ahistory of Monastery of Martula –Mariam (C1500-1974)" በሚል ርዕስ በታሪክ የትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ጥናት አድርጓል። በጥናቱ መርጡለማርያም ቤተ ክርስቲያን ከመመስረቷ በፊት የነበረው አካባቢያዊ ሁኔታ፣ ቤተ ክርስቲያኑ የተቋቋመበት ዘመን፣ ቤተ ክርስቲያኑ ወደ ገዳምነት ያደገበት ሁኔታና በግራኝ አህመድ ወረራ በገዳሙ ላይ የደረሰው ጥፋት ተተንትኗል።

አጥኚው በሥራው የገዳሙን አመሠራረትና በግራኝ አህመድ ወረራ የደረሰበትን ጉዳት ቢገልፅም በገዳም አመሠራረት ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች እና የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች የሚኖራቸውን ፋይዳ አልዳሰሰም።

ስለሽ መንግስቱ (1998)፣ "A history of Dima Giyorgis Monastery from foundation to 1976" በሚል ርዕስ በታሪክ የትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። በጥናቱ አባ ተክስተ ብርሃንና አባ ቶማስ ለገዳሙ ያደረጉትን አስተዋጽኦ፣ ገዳሙ በግራኝ አህመድ ወረራ ከጠላት ራሱን እንዴት እንደተከላከለና በጣሊያን ወረራ ጊዜ ስለደረሰበት ጥፋት ይተነትናል። የገዳሙን ታሪክ በመግለጹ ከዚህ ጥናት የሚያመሳስለው ሲሆን በተረኮች እና በቁሳዊ ባህሎች ዙሪያ ያለው ነገር ባለመኖሩ ግን ይለያል።

ጌቱ አምባዬ (1999) ፣ "A short History of the Monastery of Walate Pteros 1901-1974" በሚል ርዕስ በታሪክ ክፍለ ትምህርት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አካሂዷል።

በጥናቱ ወለተ ጴጥሮስ በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት ያደረገችው መንፈሳዊ ተጋድሎ፣ በገዳምነት ስለአፀናቻቸው ቦታዎች እና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዘንድ ስለተቀዳጀችው ክብር ተንትኗል። ጌቱ በጥናቱ ስለ ወለተ ጴጥሮስ መንፈሳዊ ተጋድሎና ስላገኘችው የቅድስና ክብር መግለጹ በተወሰነ መልኩ ከእኔ ጥናት ጋር ግንኙነት አለው ፤ሆኖም በወለተ ጴጥሮስ ገዳም አመሠራረት ዙሪያ የገለፀው ነገር ባለመኖሩ ጥናቱ በቀጥታ ከመረጠው ርዕስ ጋር ዝምድና አለው ለማለት አያስደፍርም። በተረኮችና በቁሳዊ ባህሎች ዙሪያም ያለው ነገር ባለመኖሩ ከእኔ ጥናት የተለዩ ያደርገዋል።

ጥጋብ በዜ (2001) "The Ethiopian Clain on the Monastery Deir Es-Sultan In Jerusalem, 1850-1994" በሚል ርዕስ በታሪክ የትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። በጥናቱ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በኢትዮጵያ እና በእስራኤል የተጀመረው ግንኙነት (በተለይ የንግስት ሳባና ንጉሥ ሰሎሞን) አድጐ ኢትዮጵያውያን በየጊዜው ወደ ኢየሩሳሌም እንዴት መንፈሳዊ ጉዞ ሲያደርጉ እንደቆዩ፣ በኋላም ኢትዮጵያውን መነኰሳት በኢየሩሳሌም በቋሚነት መኖር እንዴት እንደጀመሩ፣ የዴር ሱልጣን ገዳም አመሰራረት እና የኢትዮጵያ ባለይዞታነት፣ የኢትዮጵያውያኑ የኢኮኖሚ መዳከምና ዴር ሱልጣን በግብፃውያን የመነጠቁ ምስጢር፣ የግብፅና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የመቋረጡ ምክንያት፣ በአፄ

ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት የእንግሊዝ ሰዎች መታሰራቸውና ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኙነት መቋረጥ በዴርሱልጣን ገዳም ላይ የፈጠረው ተፅዕኖ፣ አፄ ዮሐንስ አራተኛ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውንን ችግር ለመፍታት ያደረጉት ጥረት፣ ዳግማዊ ምኒልክ የዴር ሱልጣንን የባለቤትነት ጥያቄ የማንሳታቸው እና ለአጭር ጊዜም ቢሆን ገዳሙን የማስመለስ ስኬታቸው፣ በዴርሱልጣን ላይ የኢትዮጵያ እና የግብፆች የይገባኛል ጥያቄ ዋና ትኩረቶች የሚሉትን ነጥቦች በስፋት ለመዳሰስ ሞክሯል።

ጥጋብ በሥራው ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች አንስቶ ለመተንተን ቢሞክርም ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ካለማድረጉም በተጨማሪ በዴርሱልጣን ገዳም ያሉ ተረኮች ና እና ቁሳዊ ባህሎች ለማሳየት ባለመሞከሩ ከእኔ ጥናት የተለየ ያደርገዋል።

### 3.2.3 በገዳማት አመሠራረት፣ እየሰጡት ካለው ጠቀሜታና የገቢ ምንጫቸውን ከማሳደግ አንፃር የተጠኑ

መንግስቱ ከበደ (1999) "The Role of Dabra Libanos Monastery In the Ethiopian Orthodox Tewhaido Church" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። የጥናቱ ዓላማ "ገዳም ሰዎች በመንፈስ፣ በሞራል፣ በአካልና በአዕምሮ እየጐለበቱ የሚኖሩበት እንጂ ሥራ ፈትተው የሚቀመጡበት ስፍራ አለመሆኑን ለማሳየት" እንደሆነ ይገልጻል። መንግስቱ በጥናቱ ስለደብረ ሊባኖስ ገዳም አመሠራረት፣ በግራኝ አህመድና በጣሊያን ወረራዎች ስላጋጠሙት ችግሮች፣ ገዳሙ በልማት፣ በትምህርትና በቅርስ አጠባበቅ ያደረገውንና እያደረገ ያለውን አስተዋጽኦ ተንትኗል።

መንግስቱ በሥራው ደብረ ሊባኖስ ገዳም ከመንፈሳዊ አገልግሎት ባሻገር ሌሎች የትምህርትና የልማት ተግባራት የሚፈፀሙበት ቦታ እንደሆነ ቢገልፅም የገዳሙ አመሰራረት ከሌሎች ገዳማት ልዩ የሚያደርገው ምን እንደሆነ፣ ገዳሙን ለጥናቱ የመረጠበትን አነሳሽ ምክንያት ለማሳየት አልሞከረም። ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የገዳሙን አመሰራረት በመግለጹ ብቻ ይሆናል።

መርዓዊ እንቻለው (2000) "A Brief History of Mahibere Selassie Monastery" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። የጥናቱ ዓላማ የማኅበረ ሥላሴ ገዳም የመኪና መንገድ፣ የእህል ወፍጮ፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ የህክምና ማዕከልና ዘመናዊ የከብት ርባታ ሊኖረው የሚችልበትን ስልት መጠቆም እንደሆነ ተጠቅሷል። መርዓዊ በሥራው የማህበረ ሥላሴ ገዳም አመሠራረት፣ የገዳሙ የመተዳደሪያ ደንብና መመሪያ ከአፈፃፀም ሂደቱ እና የገዳሙ የገቢ ምንጭ ምን እንደሆነ ገልጿል።

አጥኚው ስለገዳሙ አመሠራረት፣ ስለ አስተዳደራዊ መዋቅሩ እና ስለገቢ ምንጩ ቢገልፅም በጥናቱ ርዕስ እና በዓላማው መካከል ያለው ዝምድና ጐልቶ አልተገለፀም፣ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የገዳሙን አመሰራረት በመግለጹ ብቻ ይሆናል።

ዘላለም አሰፋ (2001)፣ "A Brief History and Activities of Zeway Debre Tsion Monastery" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። በጥናቱ በኢትዮጵያ የገዳምና የምንኩስና ሕይወት አጀማመር፣ የዝዋይ መልክዐምድራዊ አቀማመጥ፣ የደብረ ፅዮን ገዳም አመሠራረትና በገዳሙ ያሉ ቅርሶች ለቱሪዝም ያላቸው ጠቀሜታ ተተንትኗል።

አጥኚው በሥራው የዝዋይ ደብረጽዮንን አመሠራረት፣ በውስጡ ስላሉት ቅርሶች እና ቅርሶቹ ተጠብቀው ለቱሪዝም ስላላቸው ፋይዳ ለመጠቆም ቢሞክርም ገዳሙን ከሌሎች ገዳማት በተለየ ለጥናቱ ለምን እንደመረጠውና ዓላማውን በተመለከተ የጠቀሰው ነገር የለም። ከዚህ በተጨማሪ በገዳም አመሠራረት ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች እ ና ቁ ሳዊ ባህሎች ተምሳሌታዊነት  አልተመለከተም። ሆኖም የገዳሙን አመሰራረት እና መልካ ምድራዊ አቀማመጥን በመግለፁ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል።

ዘላለም ንጉሴ (2002)፣ " A Brief History of Zuramba Aregawi Monastry" በሚል ርዕስ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። በጥናቱ "የገዳሙን ታሪክ ለማስተዋወቅና

ገዳሙ በዝማሬና መዋሲት ስልጠና በመስጠት በኩል ያለው አስተዋጽኦ ለማሳየት ነው" የሚሉ ነጥቦች በዓላማው ላይ ተነስተዋል። ዘላለም በሥራው የዙር አምባ ገዳም መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የገዳሙ አመሠራረት ታሪካዊ ዳራ፣ አፄ ገብረ መስቀል ለገዳሙ ያደረጉት አስተዋጽኦ፣ የግራኝ አህመድ ወረራ በገዳሙ ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ እና በአሁኑ ጊዜ የገዳሙ የገቢ ምንጭ እንዲያድግ ሊደረጉ የሚገባቸውን የትኩረት አቅጣጫዎች ለማሳየት ሞክሯል።

አጥኚው የገዳሙን ታሪክ፣ እየወጣቸው ያሉትን ሃይማኖታዊ የትምህርት አይነቶችና በኢኮኖሚ እንዲያድግ ሊደረጉ የሚገባቸውን ተግባራት ቢጠቁምም በተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ዙሪያ ያለው ነገር ባለመኖሩ ከእኔ ጥናት ይለያል።

ተግባሩ አዳነ (2002)፣ A Brief History of Dima Giyorgis Monasterey" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አካሂዷል። ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሳው "በገዳሙ ውስጥ ያሉ ቅርሶች በአግባቡ እንዲጠበቁ ለማስቻል የሚረዱ ስልቶችን ለመጠቆም፣ አባ ተክስተ ብርሃንና አባ ቶማስ ለገዳሙ ዕድገት የፈፀሙትን መልካም ተግባር ለታሪክ ምሁራንና ለክርስቲያን ምዕመናን ለማሳወቅ፣ ገዳሙ በኢኮኖሚ የሚያድግበትን መንገድ ለገዳሙ አስተዳዳሪዎች ለማሳየትና መነኰሳቱ ከገዳሙ ወደ ከተማ እንዳይፈልሱ ለማድረግ የሚያስችሉ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለመጠቀም" የሚሉ ነጥቦችን የያዘ ነው።

አጥኚው በሥራው የገዳሙን አመሰራረትና በገዳሙ ታሪክ የአብነት ትምህርት መምህራን ሆነው ያገለገሉ 69 ሰዎችን ዘርዝሯል። በተጨማሪም ገዳሙ በጣሊያን ወረራ ጊዜ የፈፀመው መልካም ተግባር፣ በአሁኑ ጊዜ ያለው የገዳሙ የአስተዳደር መዋቅር፣ የገቢ ምንጭና በዝማሬ እና በመዋዕሲት ስልጠና በኩል እያደረገ ያለው አስተዋጽኦ ለማሳየት ሞክሯል። ተግባሩ እንደስለሽ መንግስቴ (1998) ዲማ ጊዮርጊስ ገዳምን ለጥናቱ የመረጠ ሲሆን በተለይ አባ ተክስተ ብርሃንና አባ ቶማስ ለገዳሙ ያደረጉትን አስተዋፅኦ በተመለከተ የሁለቱም ጥናት ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል። ሆኖም ተግባሩ በሥራው ስለተረክና ስለገዳሙ ቁሳዊ ባህል ያለው ነገር የለም።

ኃይለ ሚካኤል ወልደ ተክለ ሃይማኖት (2005)፣ "A Brief History of Debra Hayq Saint Stephen Abuna Iyesus Moa communal Monastery in Southern Wollo" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። በጥናቱ "የሐይቅ ደብረ እግዚአብሔርና ቅዱስ እስጢፋኖስን ገዳም ታሪክ ለማስተዋወቅ፣ አባ ኢየሱስ ሞአ ለገዳሙ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ለማሳየት፣ የገዳሙን አስተዳደራዊ ሁኔታ ለማስቃኘት፣ ገዳሙ በመንፈሳዊ ትምህርት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴና በገዳሙ ውስጥ ያሉት ችግሮች የሚፈቱበትን መንገድ ለመጠቆም" የሚሉ ነጥቦችን ዓላማ አድርጓል።

አጥኚው በሥራው የምንኩስና ሕይወት በኢትዮጵያ፣ የደብረ ሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስና ደብረ እግዚአብሔር ገዳምን አመሠራረት፣ የገዳሙን መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የገዳሙ አስተዳደራዊ መዋቅር ዘርዝሯል። በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በገዳሙ ያለው ዘመናዊ የቀሳውስት ማሰልጠኛ ተቋም ገዕታና ቀሳውስቱን አስገብቶ ለማስተማር የሚጠቀምበት የመመልመያ መስፈርት ተንትኗል።

ኃይለ ሚካኤል የሐይቅ እስጢፋኖስን ገዳም አመሠራረትና ገዳሙ በአሁኑ ወቅት እያከናወነ ያለውን መንፈሳዊ ተግባር ቢጠቀስም በገዳሙ ያሉ ተረኮችንና ቱሳዊ ባህሎችን ስላለተመለከተ ከእኔ ጥናት የተለዩ ያደርገዋል።

ገብረ ሥላሴ መርሻ (2006)፣ "A Brief History of MartulaMaryam Monastery Since 14th century Focusing on its Educational and Developmental activities" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። ጥናቱ "በገዳሙ ያሉ ቅርሶች በተገቢው የሚጠበቁበትን ስልት ለመጠቆም፣ ኢሌኒ፣ በዕደ ማርያም እና ሌሎች መነኮሳት ለገዳሙ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ለታሪክ ተመራማሪዎችና ለክርስትና እምነት ተከታዮች ለማስተዋወቅ እና የገዳሙ መነኰሳት ከገዳም ወደ ከተማ የሚያደርጉትን ፍልሰት ለመከላከል የሚረዱ ስልቶችን ለመጠቆም" የሚሉ ዓላማዎች ተቀምጠዋል።

አጥኚው በሥራው በኢሌኒ ዘመን(ከ14ኛው ክፍለ ዘመን በፊት) ቤተክርስቲያኗ የነበረችበት ሁኔታ፣ የቤተክርስቲያኗ አመሠራረት ታሪካዊ ዳራ እና በገዳሙ የሚሰጡ የአብነት ትምህርቶች በደረጃ ተጠቅሰዋል። በተጨማሪም በገዳሙ ያሉ የልማት ሥራዎች ተተንትነዋል።

ገብረ ሥላሴ እንደ ሀብታሙ መንግስቴ (1998) ጥናቱን በመርጡለ ማርያም ላይ ቢያደርግም የገዳሙን አመሠራረት በተመለከተ በሁለቱም አጥኚዎች የተጠቀሱት ነጥቦች ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆን በሌሎቹ የጥናት ትኩረቶቻቸው ላይ ግን ልዩነት ይታያል።

አጥኚው በጥናቱ  በገዳም አመሠራረት ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችንእና ቁሳዊ ባህሎች ስላልተመለከተ ከእኔ ጥናት ጋር ግንኙነት የለውም።

ለይኩን ግፋወሰን (2006)፣ "History of Abuna Habte Mariam and His Monastery" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። በጥናቱ የገዳምና የምንኩስና ሕይወት አጀማመር በኢትዮጵያ፣ የአባ ሀብተ ማርያም ገለታሪክና መንፈሳዊ ተጋድሎ ዘርዝሯል። በተጨማሪም የገዳሙ መመስረት ለአገሪቱ ያለው አስተዋጽኦ ተጠቅሷል።

በጥናቱ የገዳሙ መስራች የአባ ሀብተማርያም ገለ ታሪክና ገዳሙ ለአገሪቱ እያደረገ ያለውን አስተዋጽኦ ቢገልፅም የጥናቱ ዓላማ በግልፅ አልተጠቀሰም። ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የገዳሙን ታሪክ በመግለጹ ብቻ ነው።

ሰሎሞን ገብረ ሚካኤል (2007)፣ "The Brief History Entoto Hamere Noah Kidane Mihret Monastery of Addis Ababa" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አካሂዷል። ጥናቱ "የገዳማትን ታሪክ ማወቅ ያለው ጠቀሜታ ምን እንደሆነ፣ የመነኰሳቱ የአኗኗር ሥርዓት ምን እንደሚመስልና የገዳሙ ችግሮች ምን አይነት ገፅታ እንዳላቸው ማሳየት" የሚሉ ነጥቦችን ዓላማ አድርጓል።

ሰሎሞን በሥራው የገዳሙ መልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ የገዳሙ አመሠራረት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር እና የገቢ ምንጮቹ ተንትኗል።

አጥኚው በጥናቱ የገዳሙን አመሠራረት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር እና የገቢ ምንጮቹን ቢገልፅም ገዳሙ ምን አይነት የገዳም ሥሪት እንደሚከተል አልጠቀሰም፣፣ ገዳሙን ከሌሎች ገዳማት በተለየ ለጥናቱ የመረጠበት አነሳሽ ምክንያትንም ለማሳየት አልሞከረም። ከዚህ በተጨማሪ የገዳሙን ቁሳዊባህልና ተረክ ባመመልከቱ ከእኔ ጥናት የተለዬ ያደርገዋል።

### 3.2.4 በኢትዮጵያ ገዳማዊ ሕይወት አጀማመርና በአሁኑ ወቅት ያሉባቸውን ተያያዥ ችግሮች የተመለከቱ

ዳንኤል ኃይሉ (1999)፣ "Founders of Ethiopian Monasticism" በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አካሂዷል። ጥናቱ "በኢትዮጵያ የገዳማዊ ሕይወትን አጀማመር በተመለከተ የተሠጡትን ልዩ ልዩ አስተያየቶች በመዳሰስ እና በአስተማማኝ ምንጮች በመመሥረት አንድ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ" የሚለውን ነጥብ ዓላማ አድርጎ ተነስቷል። ዳንኤል በጥናቱ የቅድመ ክርስትና የብሕትውና ሕይወት አጀማመር፣ የክርስትና ሃይማኖት የገዳምና የምንኩስና ኑሮ አጀማመር በአለም አቀፍና በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ሞክሯል። በተጨማሪም ዘጠኙ ቅዱሳን ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ያደረጉትን አስተዋጽኦ ተንትኗል።

አጥኚው የገዳማዊና የምንኩስና ሕይወት በኢትዮጵያ እንዴት እንደተመሠረተና መስራቾቹ ዘጠኙ ቅድሳን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያደረጉትን አስተዋጽኦ ቢጠቅስም ዘጠኙ ቅድሳን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ገዳማዊ ሕይወት በጀመረበት ወቅት በተለይ በኤርትራ አካባቢ ሲንቀሳቀሱ የነበረ "ጻድቃን" የተባሉትን የመነኰሳት ሌላ ክፍል አስተዋጽኦ አልገለፀም። ጥናቱም ፎክሎራዊ ገፅታዎችን ባለመዳሰሱ ከእኔ ጥናት የተለዬ ያደርገዋል።

ሚካኤል ገብሩ (2002)፣ “Monastic life and related problems in the 20th century” በሚል ርዕስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሥነ መለኮት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል። ጥናቱ የምንኩስና እና የገዳም ሕይወት በአለም ዙሪያ ባሉ ሌሎች የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና በኢትዮጵያም እንዴት እንደተጀመረ ተተንትኗል። በተጨማሪም የገዳማት አስተዋጽኦ በትምህርት፣ በሥነጽሑፍ፣ በቅርስ አያያዝ፣ በጤና አጠባበቅና በወንጌል ስርጭት ምን እንደሚመስል ለማስቃኘት ተሞክሯል። በተጨማሪም በገዳማት ላይ እየደረሱ ያሉትን ችግሮች ለማሳየት ጣና ቂርቆስን፣ ናርጋ ሥላሴን፣ አዝልዋ ማርያምን፣ ክብራን ገብርኤልን፣ ዝዋይ ደብረፅዮንን፣ ዝቋላንና ደብረሊባኖስ ገዳማትን በናሙና መርጦ ገዳማውያኑ በገዳም ከማይኖረው የማህበረሰብ ክፍል ያላቸው ግንኙነትና በጊዜ ሂደት በመነኮሳቱ የአኗኗር ሥርዓት ላይ እየታየ ያለውን ለውጥ፣ ወጣት መናንያን የገዳም ኑሮን ለመቀላቀል የሚመርጡበት አነሳሽ ምክንያት፣ በደርግ ጊዜ ሥራ ላይ የዋለው የመሬት አዋጅ እና በገዳማቱ ኢኮኖሚ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ለማሳየት ሞክሯል። ሆኖም በጥናቱ ከላይ የተጠቀሱትን ገዳማት ወስዶ ለመመልከት ቢሞክርም ገዳማቱን ከሌሎች ገዳማት በተለየ የመረጠበት ምክንያት ምን እንደሆነ፣ የገዳሙ ቁሳዊ ባህልና ተረኮች ያላቸውን ፋይዳ አልተመለከተም። ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የጣና ቂርቆስ ገዳም ታሪክን በመጠኑ በመጠቃቀሱ ነው።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ቅኝት በተደረገባቸው ተዛማጅ ጥናቶች በጉልህ የታዩትን ድክመቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ። በተለይ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡት የብዙዎቹ ጽሑፎች ርዕስ በገዳማት አጭር ታሪክ ላይ ብቻ ሆኖ እያለ በውስጣቸው ግን የጥናታቸው ዋና ትኩረት ሆኖ የምናየው የገዳሙን የኢኮኖሚ ችግር ለማስወገድና የገቢ ምንጩን ለማሳደግ የሚያስችሉ ስልቶች፣ ቅርሶችን ለመጠበቅ መወሰድ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች እና ለገዳሙ አስተዋጽኦ ስላደረጉ ነገሥታት፣ ታዋቂ ሰዎችና ግለሰቦች ታሪክና የመሳሰሉት ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ሌላው ድክመት ርዕስን አጥብቦ የመነሳቱ ልምድ አለመኖር ነው። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በፍሬ ሕይወት ባዩ የቀረበ አንድ ጥናት አራት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ በናሙናነት ተወስደው እያለ ርዕሱ ግን

"በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ" በማለት ሰፍቶ ተቀምጡአል። ከዚህ ይልቅ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ፡ በበቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅድስ ጊዮርጊስ እና ሊሙ ማርያም፤ በአዲስ አበባ ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያምና ገነተ ፅጌ ቅድስ ጊዮርጊስ" ተብሎ ርዕሱ ጠብቦ ቢቀመጥ የተሻለ ይመስላል።

ከላይ ከተጠቀሱት ድክመቶች በተለየ ሁኔታ የሚታይ መሠረታዊ ድክመት ደግሞ በጥናቱ መግቢያ ዓላማን ያለማስተዋወቅ ነው። ለምሳሌ ዘላለም አሰፋ "Abrief History and activities of zeway Debre Tsion Monastery" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናቱ ላይ የጥናቱን ዓላማ ለይቶ አላስቀመጠም። ከዚህ በላይ ድክመቶች ብዬ የጠቀስኳቸው በጥናቱ ክፍል በአግባቡ ባለመቀመጣቸውና ባለመጠቀሳቸው የጥናቱን ቅርፅና ይዘት ከመሠረቱ ሊያዛቡ ይችላሉ ከሚል መነሻነት የጠቀስኳቸው ናቸው።

ከዚህ በመቀጠል ይህ ጥናት ከሌሎች ጥናቶች ጋር ያለውን ዝምድና እና ልዩነት አቀርባለሁ።

ከላይ የተጠቀሱት ቀደምት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ከሚመሳሰሉበት ነጥቦች መካከል የመጀመሪያው በገዳማት አመሠራረት ላይ በማተኮራቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የገዳማዊ ሕይወት አጀማመርን ለማሳየት በመሞከራቸው ነው። በተጨማሪም አንዳንዶቹ (በተለይም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የተሠሩት) በገዳማትና በአብያተ ክርስቲያናት ላይ በሚታዩ ፎክሎራዊ ገፅታዎች ላይ በማነፃፀራቸው ነው።

ከዚህ በተለየ ይህ ጥናት ከሌሎች ተዛማጅ ጥናቶች የተለየ የሚያደርገው ከጣና ቂርቆስ ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ለመመርመር በመሞከሩ ነው።

## ምዕራፍ አራት

## ከጣና ቂርቆስ ገዳም አመሠራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች

ስለ ጣና ቂርቆስ አመሠራረት ሲወሳ ተያይዘው የሚነሱ ስምንት ዋና ዋና ተረኮች አሉ። የመጀመሪያው ጣና ቂርቆስ በቀዳሚነት መስዋዕተ ኦሪት የቀረበበት መሆኑን ለመግለፅ ከታቦተ ፅዮን መምጣት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ነው። ሁለተኛው ተረክ ከቅድስት ማርያም ስደት ጋር የሚገናኘው ነው። ሦስተኛው ደግሞ ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከአባ ሰላማ ጋር የሚያያዘው ሲሆን አራተኛው ደግሞ ወለተ ጴጥሮስ በጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም ስር በሚተዳደረው ደምበዛ ቁስቋም የእናቶች ገዳም ከነበራት ተጋድሎ ጋር የተሳሰረ ነው። ቀሪዎቹ ሦስቱ ተረኮች የቂርቆስን ፈጣን ተራዳይነት እና ቅርስ ጠባቂነት ያመለክታሉ። ተረኮቹ እንደሚያነሱት የርዕስ ጉዳይ ተመሳሳይነት አንዱን ከሌላው ጋር በማቀናጀት ለማየት ይሞከራል።

### 4.1 ጥንታዊ፣ ቀዳሚና ከኢየሩሳሌም የመጣ መሆኑን ለማሳየት መሞከር

ከጣና ቂርቆስ የአባቶችና የእናቶች የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዞ በሚነሱ ት ተረኮች ውስጥ ጥንታዊ፣ ቀዳሚና ከእየሩሳሌም የመጣ የሚሉት ሀይለ ቃሎች ጎልተው ይታያሉ።

በተራ ቁጥር አንድ ውስጥ የቀረበውን ተረክ ለአብነት ወስደን ብንመለከት ተረኩ የሚያተኩረው ከእስራኤል ንጉሥ ከሰሎሞን እና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ የተወለደው ቀዳማዊ ምኒልክ እየሩሳሌም ቆይቶ ወደ አገሩ የእስራኤልን በኩራትና መጽሐፈ ብሉያትን ይዞ ሊመለስ ሲል ታቦተ ፅዮንን ይዞ ለማምጣት ያስባል። አባቱንም ቀርቦ ቢለምነው ፈቃደኛ አልሆነለትም። ከዚያም ከሊቀ ካህናቱ የበኩር ልጅ ከሳዶቅ ጋር በመመሳጠር እና ታቦተ ፅዮንን አስመስሎ በማስቀረፅ በመንበሩ ላይ እንድትቀመጥ ያደርጋል። ዋናውንም ታቦት አሰርቆ ወደ ኢትዮጵያ ይዞ ይገዛል። ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ በጣና ደሴት ድንኳን ተክሎ መስዋዕተ ኦሪትን እና አምልኮተ እግዚአብሔርን መፈፀም ይጀምራል። በሂደትም ከቦታው ፅላት እየተቀረጸ ለተድባበ ማርያም፣ ለአክሱም ፅዮንና ለመርጡለ ማርያም እንደተላከ ይተርካል። ስፍራውም ሴቶች የማይገቡበት የነብያት ገዳም እንደነበር ይገልጻል(አባ ባዬፍስሐ፣ ካሴት ቁጥር

1A፣ ግንቦት 25 ቀን 2002፤ መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 3-4፣ ግንቦት26 ቀን 2002፣ጣና ቂርቆስ ገዳም)።

በዚህ ተረክ የዘመኑ ጥንታዊነት የተመዘዘው ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሽህ አመት አለም አካባቢ ነው። ከኢየሩሳሌምም መጡ የተባሉት እግዚአብሔርና እስራኤላዊያን የሚገናኙባት የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ የእስራኤል ሕዝብ በኩራትና መጽሐፈ ብሉያት ናቸው። እነዚህ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ በቀዳሚነት ያረፉት ደግሞ በአሁኑ ጣና ቂርቆስ ገዳም ነው።

ተረኩ በስፍራው መስዋዕተ ኦሪት ከመቅረቡም በሻገር ፅላት ቀርፆ መላኩን ይገልጻል። ይህ ደግሞ ቦታው ፅላት ተቀርፆ ተላከላቸው ከተባሉት ቦታዎች ይልቅ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ጥንታዊነትና ቀዳሚነት እንዳለው ያሳያል። ሌላው ተረኩ ቦታው በኢትዮጵያ ቀዳሚ የነቢያት ገዳም መሆኑን ሲገልፅ«ስፍራው የኦሪትና የነቢያት ገዳም ነው። በኦሪትም ሴት አይገባበትም ሌዋዊያን 46ቱን መጻሕፍት እየተማሩ ለድጓነት የበቁበት በዚህ ገዳም ነው» (መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 4፣ ግንቦት 26 ቀን2002፣ጣናቂርቆስ ገዳም) በማለት ስፍራው በዘመነ ኦሪትም የገዳም ሕይወት የተጀመረ እንደነበር ያሳያል።

ይህ ደግሞ ለገዳማውያኑ ስፍራው ለመጀመሪያ ጊዜ «ከኢየሩሳሌም የመጣችው» ታቦተ ፅዮን ያረፈችበትና መስዋዕተ ኦሪት የተሰዋበት፣ ቀዳሚውና ጥንታዊው የነቢያት ገዳም የተገደመበት ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል።

ይህ የስፍራውን ታሪክ «ጥንታዊ» የማድረግ እና ቅዱሱን ነገር «ከኢየሩሳሌም የመጣ» የሚለው ጉዳይ በተራ ቁጥር ሁለት በተጠቀሰው ተረክ ላይም እንመለከታለን። ተረኩ ድንግል ማርያም ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሆነው ከኢየሩሳሌም በግብፅ አድርገው ወደ ጣና ደሴት መምጣታቸውን፣ በቦታውም ሦስት ወር ከአምስት ቀናት መቆየታቸውን፣ በአረፉበትም ቋጥኝ ስር ለብዙ ዘመናት ተሰውሮ የሚኖር ቤተ መቅደስ መከፈቱንና በውስጡ ካሉት በነቢዩ ኤልያስ ዘመን ተሰደው ከሚኖሩ ስውር ቅዱሳን ጋር መነጋገራቸውን፣ በቋጥኙ ላይም ድንግል ማርያም፣ የሕፃኑ የኢየሱስ ክርስቶስና የአህያዋ ዱካ ታትሞ መቅረቱን፣ አሳደጁ ንጉሥ ሄሮድስ መሞቱንም ሰምተው ወደ ኢየሩሳሌም ሊመለሱ በመዘጋጀት ላይ እያሉ በዚሁ ቦታ ሕፃኑ ኢየሱስ ለእናቱ ኢትዮጵያን አስራት

አድርጎ መስጠቱን፣ ከዚያን ጊዜም ጀምሮ ድንግል ማርያም ጣና ደሴትንና መነኮሳቱን በ24 ሰዓት አንድ ጊዜ ተገኝታ የምትባርክ መሆኑን ነው (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992 ፡ 17-21፤ መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 4B፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም)።

በዚህ ተረክ «ከኢየሩሳሌም የመጣ» የሚለው የእነ ድንግል ማርያምን የጉዞ መነሻ ወይም የትውልድ ቦታ የሚወክል ሲሆን፣ ታሪኩ ተፈጸመ የተባለው ከ2 ሺህ ዓመተ ምሕረት በፊት መሆኑ እና የኤልያስ ዘመን ቅዱሳን በዚያ ተሰውረው መገኘታቸው ደግሞ የስፍራውን «ጥንታዊ»ነት ያሳያል። በሌላ መልኩ ድንግል ማርያምና ተከታዮቿን ሦስት ወር ከአምስት ቀን በእንግድነት በማስቀመጥ ስፍራውን «ቀዳሚ»ያደርገዋል።

በተረክ አራትም ወለተ ጴጥሮስ በድንግል ማርያም ትዕዛዝ ከዋልድባ ጣና ደሴት ከመጣች በኋላ ወደ ወንዶች ገዳም ገብታ ለመጸለይ ስትሞክር ድንግል ማርያም ተገልጻ ቦታው ሴቶች እንዳይገቡ የተወገዘ እንደሆነ ከነገረቻት በኋላ ወደ እናቶች ገዳም ገብታ ስትጸልይ በኢየሩሳሌም ሉቃስ በቀይ፣ በቢጫ፣ በአረንጓዴና በጥቁር ቀለሞች የሳላትና በጣና ቂርቆስ ቤተ መቅደስ የነበረችው የድንግል ማርያም ስዕል ከፊቷ ላይ መጥታ እንደበት አውጥታ እንዳናገረቻት ተገልጿል(ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡2-10)። በተረኩ በኢየሩሳሌም መሳሏ ከኢየሩሳሌም የመጣ የሚለውን ሀሳብ የሚያጠናክርልን ሲሆን ሉቃስ የሳላት የድንግል ማርያም ስዕል ደግሞ የመጀመሪያዋ ናት ተብሎ ስለሚታመን ቦታው የድንግል ማርያምን ስዕለ አድህኖ በመያዝ «ቀዳሚ»ት እንዳለው ለማሳየት የተነገረ ይመስላል።

የገዳሙን ጥንታዊነትና ቀዳሚነት በገዳማዊያኑ ዘንድ ለማስረጽ ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች መካከል አንዱ ዋኖችን የራስ ማድረግና ለዋኖቹ መስጠት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

### 4.1.1 ዋኖችን የራስ ማድረግ

ከገዳሙ አመሰራረት ጋር በተያያዘ ከተነገሩት አምስት ተረኮች መካከል በአራቱ ላይ ዋኖች[6] ተጠቅሰው ይገኛሉ። በቅድሚያ በተራ ቁጥር አንድ በተጠቀሰው ተረክ ላይ ታቦተ ፅዮን እስራኤላውያንን ከእግዚአብሔር ጋር በማገናኘትና ከጠላታቸው በመታደግ ረገድ በዘመኑ ለእስራኤላዊያን ከፈጣሪያቸው በታች ክብር የሚሰጧት«ዋና» እንደነበረች በመፅሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ ይገኛል።

በተረክ ሁለት የተገለፀው ድንግል ማርያምና ኢየሱስ በተለይ ለክርስትናው አለም «ዋኖች» ናቸው። በተመሳሳይ በተራ ቁጥር ሦስት በቀረበው ተረክ አባ ሰላማ ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት እና በማስፋፋት«ከሳቴ ብርሃን» እስከ መባል የደረሰ በመሆኑ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በ«ዋና»ነት ይጠቀሳል። ቅዱስ ያሬድም የኢትዮጵያ «የዜማ አባት» በመባል የሚታወቅ እና በቤተክርስቲያኗ የዝማሬ ታሪክ «ዋና» ሆኖ የሚጠቀስ ነው። በተረክ አራት ወለተ ጴጥሮስ በተጋድሎዋ ከቤተክርስቲያኗ ቅዱሳት አንስት በቀዳሚነት የምትታወቅ እና እምነ(እናታችን) በመባል የምትጠራ «ዋና» ናት።

እነዚህ ሁሉ ዋኖች በጣና ደሴት በተለያዩ ጊዜያት እንደመጡ እና በስፍራው ላይ የየራሳቸውን አሻራ እንዳሳረፉ በተረኮቹ ላይ ተጠቅሷል።

### 4.1.2 በስፍራው የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎችንና የሚነገሩ ተረኮችን ለዋኖቹ መስጠት

በተረኩ ውስጥ ዋኖችን ከስፍራው ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳላቸው ከመገለጹም ባሻገር በገዳሙ ውስጥ ለሚገኙ ቁሶች፣ ተፈፀሙ ለሚባሉ ተግባራት፣ ለተሰሩ ስርዓቶች፣ ለተጻፉ መጻሕፍት ወዘተ. ባለቤቶቹ እነርሱ እንደሆኑ ማሳየት ነው። ይህ ለዋኖቹ የመስጠቱ ጉዳይ ሊከሰት የቻለው ደግሞ ምናልባት መጽሐፍ የጻፈው ወይም ገዳም

[6] በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ለከፍተኛ መንፈሳዊ አገልግሎት እንደተመረጡ የሚታመኑ ወይም አርኣያ ሆነው የሚቆጠሩ ሲሆኑ እንዲህ አይነቶቹን መጽሐፍ ቅዱስ «ዋኖች» ብሎ ይጠራቸዋል(ዕብ.13:6) ።

የመሰረተው ሰው ለትህትና ወይም ከንቱ ውዳሴ በመፍራት ራሱን ሳይገልፅ በማለፉ ምክንያት ይሆናል።

ተረኮቹ በዋኖቹ ስም መቅረባቸው ደግሞ ተረኮቹን ለሚሰሟቸው ገዳማውያን በቦታው ፀንተው እንዲኖሩና ይበልጥ መንፈሳዊ ፍሬ አፍርተን ዋኖቻችን ከደረሱበት የቅድስና ደረጃ መድረስ አለብን ብለው እንዲነሳሱ ያበረታታቸዋል። ይህን በተመለከተ ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በላከው መልዕክቱ «...ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሯቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው» (ዕብ.13:6) በማለት ዋኖች የፈፀሙትን ተጋድሎ፣ ያሳለፉትን መከራና በተጋድሏቸው ወይም በመከራቸው ፀንተው በመገኘታቸው ያፈሩትን የመንፈስ ፍሬ ማሰብና መምሰል እንደሚገባ ይናገራል።

## 4.2 ለዋኖች መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት፣

### 4.2.1 የቦታውን ክብር ወይም ቅድስና ለማጉላት፣

በአለማችን ላይ የነበሩ «ዋኖች» የተወለዱበት፣ ተጋድሎ የፈፀሙበትና የአረፉበት ስፍራ የራሱ የሆነ ከበሬታ ተሰጥቶት እናገኛለን። «ቤተልሔም»በኢየሱስ ክርስቶስ፣ «መካ» በነብዩ መሐመድ፣ «አክሱም» በታቦተ ፅዮን፣ «ደብረ ሊባኖስ» በተክለ ሃይማኖት፣ «ግሸን ማርያም» በግማደ መስቀሉ ምክንያት የሚሰጠው ክብር ከፍተኛ ነው።

ከጣና ቂርቆስ ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዞ በሚነሱት ተረኮች ውስጥ ስፍራው ታቦተ ፅዮን ለመጀመሪያ ጊዜ ነበረችበት መባሉ፣ ድንግል ማርያም በስደቷ ጊዜ ከልጇ ጋር ቆይታበታለች ተብሎ መነገሩ፣ አባ ሰላማ ቦታውን ባርከውት በዚያው አርፈዋል ተብሎ መተረኩ፣ ቅዱስ ያሬድ የመጀመሪያውን ምልክት አልባ ድጓ በዚህ ቦታ እንደጻፈው መጠቀሱ፣ ወለተ ጴጥሮስ በስፍራው በገድልና በትሩፋት እመምኔት ሆና ቆይታለች መባሉ ለገዳማውያኑ የቦታው ክብር ከፍ ያለ መሆኑንና የቅዱሳን መናኸሪያ እንደሆነ እንዲያምኑ፣ ዋኖቻቸውንም እያሰቡና የኑሯቸውን ፍሬ እየተመለከቱ በእምነት እንዲመስሏቸው ያግዛል።

### 4.2.2 የተረኩን ተአማኒነት ለመጨመር፣

በተረኮቹ ስለዋኖቹ ሲተረክ በቦታው ስለመኖራቸው ብቻ ተነግሮ የሚያበቃ አይደለም። በቦታው ነበሩ በተባሉበት ዘመን ፈፀሙት ተብሎ የሚታመኑ ገድሎች፣ ተገኙ ተብለው የሚነገሩ ትሩፋቶች፣ ተገብቶላቸዋል ተብለው የሚነገሩ ቃልኪዳኖች፣ አፈለቋቸው ተብለው የሚታመንባቸው ጠበሎች፣ ሰሯቸው ተብለው ለአገልግሎት የሚውሉት ስርዓቶች፣ አውግዘዋቸዋል የተባሉ ውግዘቶች፣ ተቀበሩባቸው የተባሉ መቃብሮች ወዘተ. ሁሉ በዝርዝር ይቀርባሉ።

እነዚህ ድርጊቶች በዋናዎቹ ስም መቅረባቸው ገዳማውያኑ ዋኖቹ ተናገሯቸው ወይም ፈፀሟቸው ተብለው የተተረኩትን ተረኮች በቀላሉ አምነው ስለሚቀበሏቸው ነው። በመሆኑም ውግዘቱ፣ ቃልኪዳኑ፣ ስርዓቱ፣ ጠበሉ፣ ወዘተ. በዋኖች ስም ሆነው ይገኛሉ። በተረኮቹም የዋኖቹ ነው ተብሎ የሚነገረው ውግዘት፣ ቃልኪዳን፣ ስርዓት፣ ጠበል፣ ወዘተ.ሲቀርብ ጎን ለጎን ዋኖቹ በቦታው ለመኖራቸው ማስረጃ በማቅረብ ለማሳመን ይሞከራል።

## 4.3 ተረኩን የበለጠ ተአማኒ ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው ስልቶች፣

### 4.3.1 ከዋኖቹ ጋር ተያያዥነት አላቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን ቁሳዊ ባህሎችና በዋኖቹ ተሰየሙ የተባሉትን ቦታዎች በማሳየት፣

በተረክ አንድ ታቦተ ፅዮን በጣና ደሴት እንደነበረች ለማስረዳት የአዛሪያስ ልጅ የካህኑ የሳዶቅ መቃብር፣ የኦሪት መስዋዕት ይሰዋበት የነበረ የእንስሳቱ የደም መቀበያ ጎሞር፣ የኦሪት መስዊያ የድንጋይ መንበር፣ የሥጋው ማንጠልጠያ ሜንጦ፣ ሰባቱ መቅረዞች፣ መስዋዕቱን የሚያቀርበው ሊቀ ካህን ይለብሰው የነበረው እንደወገቡ ስፋትና ጥበት የሚስተካከል የብረት ልብስ፣ ታቦቱ የሚቀመጥበት መንበር፣ የወይፈንና የበጉን ሥጋ የሚቀበሉበት ምጣድ፣ ደሙን የሚያንጠፈጥፉበት ፅዋ፣ ሰሎሞን ለምኒልክ የሰጠው ከብርጭቆ የተሠራ የእጅ መታጠቢያና የድንኳኑ መትከያ ጉድጓድ፣መጽሐፈ ሄኖክ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን ቁሶች፣ ድንግል ማርያምና ተከታዮቿ በቦታው ለመቆየታቸው ደግሞ በቀዳሚነት ከጣና ቂርቆስ ቤተክርስቲያን በስተምስራቅ በኩል

በግምት ከሰባት እስከ አስር ሜትር ርቀት ካለው ትልቅ ቋጥኝ አናት ላይ የድንግል ማርያም፣ የኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም ተጭናባት የነበረችው አህያ ነው ተብሎ የሚታመንባቸው ከቋጥኙ ላይ የተቀረፁ ዱካ የሚመስሉ ነገሮች፣ ከቋጥኙ ላይ አርፋበታለች ተብሎ የሚታመንበት ቦታ ( በአሁኑ ጊዜ ብረት በብረት ሆኖ በተሠራ፣ ግማሽ ሜትር በግማሽ ሜትር በሆነች መጠለያ ውስጥ ስዕለማርያም ተቀምጣበት ይገኛል)፣ ጣና ለሚለው ስያሜ መነሻው ዮሴፍ ወደ ሕፃኑ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በመቅረብ "ፀአና በደመና" በደመና ጫናት በማለቱ በሂደት የሐይቁ ስም ጣና መባሉን በመንገር፣ ወደ አገራቸው ሊመለሱ በደመና ላይ እያሉ ድንግል ማርያም የሴቶችን ገዳም ደብረ ቁስቋም፣ ያረፉበትን ደሴት ዳግማዊት ኢየሩሳሌም፣ ከደሴቲቱ በስተምስራቅ አቅጣጫ ያሉትን ሁለት ትንንሽ ኮረብታዎች ደግሞ "ኤፍራታና ኢያሪኮ" ብላ መሰየሟን በመተረክ፣ አባ ሰላማን በተመለከተ ደግሞ የኦሪቱን ቤተ መቅደስ አፍርሰው በቦታው ላይ ቤተ ክርስቲያን ማሳነፃቸውን፣ ቦታውንም ስም "ደብረ ሣህል" (የምሕረት ወይም የይቅርታ ተራራ)ብለው መሰየማቸውን፣ በዕቃ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሁለት የእጅ መስቀሎች፣ ካባ እና ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ግዕዝ የተተረጎመ ነው የሚባልለትን የህዲስ ኪዳን መጽሐፍን በማሳየት፣ ቅዱስ ያሬድም ጋር በተያያዘ ለመጀመሪያ ጊዜ የፃፈው ነው የተባለለትን ምልክት አልባው የድጓ መጽሐፍ፣ ድጓውንም ሲፅፍ ለቀለም መበጥበጫነት ተጠቅሞባቸዋል የሚባሉትን ከድንጋይ ተቦርቡረው የተሠሩ ጉድጓዶችን፣ የእርሱ ነው የሚባለውን ካባና ለወለተ ጴጥሮስም በአካባቢው ባለው ሬማ መድኃኔአለም ቤተክር ስቲያን መቃብሯ መኖሩን በማሳየት ዋናዎቹ በቦታው በትክክል እንደነበሩ ለማሳመን ይሞክራል(ዘመድኩን፣ 1992፡ 226-227)።

### 4.3.2 በዋኖች አማካይነት በስፍራው ተፈፀሙ የተባሉ ተአምራትን ወይም ተግባራትን በመንገር፣

በሃይማኖት አስተምህሮ«ተአምር» የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ ነው። የዚህ ምክንያቱ አንድም ተአምር የሚሰራው ወይም የሚሰራለትን አካል የቅድስና ወይም የክብር ደረጃ ያሳያል ተብሎ ስለሚታሰብ፣ አሊያም ደግሞ ተአምር የተፈጸመበትን ቦታ ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ እንዲታመን ስለሚያደርግ ነው። አንድም ተአምር የሚፈጸመው በሚታይ አካል አማካይነት ቢሆንም በተአምር ሰሪው ወይም በሚሰራለት አካል ላይ አድሮ

የሚሰራው ሌላ ልዕለ አካል እንዳለ ስለሚታመንና የልዕለ አካሉን ኃያልነት ስለሚያሳይ ነው። የተአምር ዋና አላማውም ተአምሩን የሚመለከቱት ወይም የሚሰሙት አካላት የተአምር ሰሪው ደጋፊ ከሆኑ በእምነታቸው ፀንተው እንዲኖሩ ሲያደርግ ከተአምር ሰሪው በተቃራኒው የቆሙ ከሆነ ደግሞ አደብ ገዝተው እንዲኖሩ ወይም ተአምሩን አይተው አቋማቸውን እንዲያስተካክሉ ማድረግ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ተአምር ሰሚው ወይም አንባቢው ተአምሩን በመስማቱና በማንበቡ ከቅዱሱ በረከት ያገኛል ተብሎ ስለሚታመን ያንን ተልዕኮ ማስፈፀም ነው።

ለምሳሌ በመፅሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት እስራኤላዊያንን በብዙ ተአምራት ከግብፅ ባርነት አላቆ፣ የኤርትራን ባህር እንዲሻገሩ ከአደረገ በኋላ እስራኤላዊያኑ «እግዚአብሔር በግብፃዊያን ላይ ያደረጋትን ታላቂቱን እጅ አዩ ሕዝቡም እግዚአብሔርን ፈሩ፣ በእግዚአብሔርም በባሪያውም በሙሴ አመኑ» (ዘፀ.14 :31) በማለት በተአምር ሰሪውና በተአምር አሰሪው ላይ እምነት እንዳሳድሩ እንመለከታለን። በተመሳሳይ መልኩ ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላ ቃና ሰርግ ላይ ተገኝቶ የመጀመሪያው የሆነውን ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ በተአምር በመቀየሩ «ደቀመዛሙርቱም በእርሱ አመኑ»(ዮሐ.2:11) ተብሎ ተጠቅሷል። እንዲሁም ኢየሱስ ተአምራቱን የፈፀመባቸው ቦታዎች ሁሉ በአሁኑ ጊዜ ቅዱስ ስፍራ፣ ሀገሪቱም ቅድስት ሀገር እየተባለች ትጠራለች(አማከለ፣1992:1)።

በጣና ቂርቆስ ገዳምም በተረኮቹ በተጠቀሱት ዋኖች አማካይነት ተአምራት እንደተፈፀሙ ተጠቅሷል። ለአብነት ያህል በተረክ ሁለት ድንግል ማርያም በደሴቷ ባለው ቋጥኝ ላይ ሳለች የቆመችበት ድንጋይ በተአምራት እርጥብ ጭቃ እንደረገጠች ሆኖ ጫማዋ በቋጥኙ ላይ መቀረፁን፣ ወደ ደሴቷ ስትደርስ በኤልያስ ዘመን ተሰውሮ የነበረ ዘጠኝ ቤተመቅደስ ተከፍቶ ከውስጧ ከነበሩት ቅዱሳን ጋር መነጋገሯን፣ ወደ አገራቸው ሊሄዱ ሲሉም ደመና ጠቅሰው እንደነበር ተጠቅሷል(ገዳማውያኑ በዋኖቹ አማካይነት በተአምራት የተከሰቱ ናቸው በሚሏቸው ላይ የሚፈፅሟቸውን የአምልኮ ስርዓት የገዳሙ ቁሳዊ ባህል በተተነተነበት ክፍል ለማሳየት ይሞከራል)።

በተረክ ሦስት በአባ ሰላማ ጠያቂነት ከኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ የማጥመቂያ መስቀል፣ በማዕጠንት ጊዜ የሚያዝ መስቀል፣ቅብዐ ሜሮን፣ መፅሐፈ ክርስትና፣ መፅሐፈ

ቅዳሴ፣ መፅሐፈ 4ቱ ወንጌላት፣ 5 አልባሳትና ወርቀ ዘቦ መስጠቱን፣ ከሐይቁ በምስራቅ በኩል አሐዱ አብ ቅዱስ ብሎ ሲባርክ 7ቱ ሰማያት ተከፍተው መላዕክት ረበው እንደታዩ ተገልጿል።

ተረክ አራት ደግሞ ወለተ ጴጥሮስ ጸሎት ካደረሰች በኋላ በጣና ቂርቆስ ቤተ መቅደስ ላይ 3 ብርሃናት ተተክሎበት መላዕክት ሲወጡበትና ሲወርዱበት ማየቷ፣ በኢየሩሳሌም በሉቃስ እጅ የተሳለች የማርያም ስዕል ከፊቷ ላይ መጥታ መቀመጧ እና አንደበት አውጥታ ማናገሯ ተተርኳል (መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 4B፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ ጣናቂርቆስ ገዳም)።

በተረክ አምስት በቂርቆስ አማካይነት ገዳሙን ሊያቃጥሉት የነበረውን የግራኝ አህመድ ጦር በጣና ሐይቅ ላይ ማስጠሙን፣ በተረክ ስድስት በአንድ መነኩሴ የተወሰደውን የአባ ሰላማን መስቀል ማስመለሱን (መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር4 A፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ ጣናቂርቆስ ገዳም) ና በተረክ ስምንት ዘመናዊ የሆነው ሞተር በገዳሙ ውስጥ እንዳይሰራ ማድረጉ ተጠቅሷል (አባ ወልደ ተንሳይ፣ሚያዝያ 22 ቀን 2003፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም)።

### 4.4 በተረኮቹ ውስጥ የዋኖቹ ተግባር፣

በተረኩ ውስጥ የተጠቀሱት ዋኖች በስፍራው የተለያዩ ተግባራት ሲፈጽሙ ይታያሉ። ከነዚህም መካከል ስለቦታው ቅድስና መናገር፣ የገዳሙን መተዳደሪያ ስርዓት ማበጀት፣ ገዳሙን በተደጋጋሚ በአካለ ነፍስ መጎብኘት፣ እንደ ስልጣን ተዋረዳቸው አንዱ ለሌላኛው መታዘዝና በስልጣን ከእነርሱ በታች ላሉት ጥበቃና ድጋፍ ማድረግ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

#### 4.4.1 ዋኖቹ እንደ ስልጣን ተዋረዳቸው አንዱ ለሌላኛው መታዘዝ ፣

ሌላው በተረኮቹ የምንመለከተው ዋኖቹ በስልጣን የሚለያዩ መሆኑን ነው። በተረክ ሁለት ኢየሱስ ክርስቶስ በጣና ደሴት በዳመና ላይ ሆኖ ኢትዮጵያን አስራት ጣና ደሴትን (ጣና ቂርቆስን) ደግሞ በ24 ሰዓት እንድትጎበኛት እና መነኮሳቱን እንድትባርክ፣ ደሴቷንም የተሳለመ እየሩሳሌምን እንደጎበኘ እንደ ሚቆጠርለትና እስከ

መቶ ትውልድ እንደሚምርላት ቃል ኪዳን ይሰጣታል። በዚህ ተረክ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ሰጭ ሲሆን ቃል ኪዳን ተቀባይዋ ደግሞ ቅድስት ማርያም ሆና ተጠቅሳለች (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡ 21)።

በተረክ ሦስት ደግሞ ድንግል ማርያም ከሳቴ ብርሃን አባ ሰላማን ወደ ጣና ደሴት ሄዶ ሕዝቡን እንዲያጠምቅ ታዘዋለች። ከዚህ ላይ ትዕዛዝ ሰጭ ድንግል ማርያም ስትሆን ትዕዛዝ ተቀባይ ደግሞ አባ ሰላማ ነው(ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡ 10)። በተረክ አራትም በተመሳሳይ ወለተ ጴጥሮስ ከዋልድባ ወደ ጣና ቂርቆስ የምትሄደው በድንግል ማርያም ጥሪ እና መሪነት ነው(ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 3)። ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በስልጣን ከሁሉም የሚበልጠው ኢየሱስ ክርስቶስ በደረጃ ከእርሱ ዝቅ ብላ ለምትገኘው ለድንግል ማርያም በቦታዋ ላይ ቃል ኪዳን ከሰጣት በኋላ የቦታው አዛዥ ድንግል ማርያም ትሆናለች። በቃልኪዳኗ ስፍራ ላይም ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስትና ጥምቀት እንዲፈጸም፣ ክርስትና እንዲሰበክና ስርዓት እንዲበጅ ማስደረጓን በተረክ ሦስት እና አራት እንመለከታለን። ይህ ደግሞ በስፍራው ላይ ላሉ ገዳማውያን የታችኛው ለላይኛው በትህትና መታዘዝ እንደሚገባ ለማሳየት የተነገረ ይመስላል።

### 4.4.2 ዋኖቹ ስለቦታው ቅድስና እንዲናገሩ ማድረግ

በተረክ ሁለት ድንግል ማርያም መልአከ እግዚአብሔር መጥቶ ንጉስ ሄሮድስ እንደሞተና ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ሲነግራቸው ድንግል ማርያም «አይ አልሄድም የኢየሩሳሌም የአገሬ ሰዎች ክፉ ናቸው፣ ከርሃብ ከጥም፣ በቀር ያገኘሁት ነገር የለም ይህችን የመሰለች አገርማ እኔ ትቼ አልሄድም፤ እነዚህን ቅዱሳን አልለይም» (መምህር ክፍለ ማርያም፣ካሴት ቁጥር4B፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ጣና ቂርቆስ ገዳም)። በማለት የቦታውን ጥሩነት ከኢየሩሳሌም ጋር በማነጻጸር ትናገራለች። በተመሳሳይ በተረክ አራት ድንግል ማርያም ከወለተ ጴጥሮስ ጋር ስትነጋገር በነበረበት ወቅት«የእኔ ፈቃድ ሆኖ ውሃዎች ከተባረኩበት፣ እንጨቶች ከማይደርቁበት ከዚህች ከተቀደሰች ቦታ አድርሼሻለሁ፤ ደስ ይበልሽ ብዙ ገዳማት አሉ። ከእነዚህ ሁሉ መርጬ ፀአና አድርሼሻለሁ» (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣

1992፡ 3)በማለት የስፍራውን ቅድስና እና ክብር ከሌሎች ገዳማት ከፍ ያለ መሆኑን ትናገራለች።

በተረክ አራት ደግሞ ወለተ ጴጥሮስ ስለቦታው ቅድስና አስቀድማ ነበረችበት ከተባለው ዋልድባ ጋር አነፃፅራ ስትናገር ዋልድባንና ጣና ገዳምን በማነጻጸር ዋልድባ ቃልኪዳኑ እስከ 70 ትውልድ ጣና ቂርቆስ ደግሞ እስከ 100 ትውልድ የሚማርባት መሆኑን (ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 9) በመግለጽ ጣና ቂርቆስ ከዋልድባ ገዳም በላይ ክብርና ቃል ኪዳን እንዳለው ለማሳየት ተሞክሯል።

### 4.4.3 በዋኖቹ ስም የገዳሙን መተዳደሪያ ስርዓት ማበጀት፣

ለዚህ አብነት የሚሆነው በገዳሙ ለመጠጥነት የሚያገለግለው ከጣና የተቀዳ ውሃ ነው። ማንኛውም ገዳማዊ ከጣና ውሃ ውጭ ሌላ አይጠጣም። የዚህ ምክንያቱ ጣና ሐይቅ ጠበል ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ አባ ሰላማ ከጣና ውጭ ውሃ እንዳይጠጣ ስርዓት እንደመሰረቱ ይነገራል። ይህንንም በተመለከተ በተረክ ሦስት አባ ሰላማ ሲባርኩት «መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል በጣና ባሕር ላይ ወርዶ ስለቀደሳት የጣና ባህር ልክ እንደ ዮርዳኖስ ባህር የተቀደሰች ሆነች» (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡ 10) በማለት ውሃው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተጠመቀበት ዮርዳኖስ ውሃ የተቀደሰና የቅድስና ደረጃውም ከዮርዳኖስ ወንዝ ጋር በአቻነት የሚታይ እንደሆነ ለማሳየት ተሞክሯል።

ሌላው ስርዓት ወደጣና ቂርቆስ ገዳም ሴቶች እንዳይገቡ የሚከለክለው ሕግ ነው። ሴቶች ወደ ጣና ቂርቆስ ገዳም እንዳይገቡ ስለሚከለከሉ በምዕራብ በኩል ባለችው ደምበዛ ቁስቋም ቤተክርስቲያን ይኖራሉ። ገዳሙ ለሴቶች መከልከሉን በተመለከተ በተረክ ሦስት አባ ሰላማ ሴቶች እንዳይገቡ ሥርዐት መደንገጋቸውንና ይህንንም የጣሰ እስከ አስራ ሁለት ትውልድ የተረገመ ይሁን ብለው ማውገዛቸው ተጠቅሷል(ዝኒ ከማሁ ገፅ 10)። በተመሳሳይ በተረክ አራት ድንግል ማርያም ለወለተ ጴጥሮስ «ልጄ በስልጣኑ በአቡነ ሰላማ አድሮ እናቶች ወደ ደሴተ ፀአና እንዳይገቡ አውግዟል» (ዝኒ ከማሁ ገፅ 3) በማለት ለሴቶች የተከለከለው በኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዝ እንደሆነ ተጠቅሶ ይገኛል።

ይህን ስርዓት ለመጠበቅ ይመስላል በአሁኑ ጊዜ በገዳሙ ሴት ፆታ ያለው ሰውም ሆነ እንስሳ የማይገቡ ሲሆን በገዳሙ ቅጥር ግቢ እንዲያድሩ የሚፈቀድላቸው የተቀጠቀጡ በሬዎች ብቻ መሆኑን አጥኚው መረጃ ለመሰብሰብ በሄደበት ጊዜ መመልከት ችሏል። የዚህ ምክንያት አንድም ገዳማውያኑ ለእግዚአብሔር ራሳቸውን ስልብ (ጃንደረባ) አድርገው (ማቴ.19፣12) ወደ ገዳም እንደገቡት ሁሉ በሬዎችም ያንን ሥርዓት እንዲያከብሩ ወይም ፈቃደ ሥጋውን ያልገደለ ወደ ገዳሙ ገብቶ ለመኖር እንደማይች ል ለማሳየት ታስቦ ይሆናል፤ ይህን የበለጠ የሚያጎላው ደግሞ የገዳሙ የርቢ በጐች ከበሬዎቹ ተለይተው ከገዳሙ ቅጥር ግቢ ውጭ እንዲያድሩ መደረጉን ስንመለከት ነው።

በሌላ መልኩ በተረክ አራት ወለተጴጥሮስ ከደምበዛ ቁስቋም ወደ ሬማ መድኃኔአለም ለመሄድ የእመምኔትነቱን ስልጣን ለፍቅርተ ክርስቶስ ከአሸጋገረች በኋላ እንዴት ገዳማዊያኑን ልትመራ እንደምትችል በምትመክርበት ክፍል በደምበዛ ቁስቋም ቅዳሴ በአመት 4 ጊዜ መሆኑን፣ የሚቀድሱትም ድንግሎች፣ ከእናትና አባታቸው በአስራ ሁለት አመታቸው የተለዩ መሆን እንዳለባቸው ገልጻ ይህንን ስርዓትም በመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ በአባ ሰላማ የወጣ እንደሆነ ትናገራለች (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባ ቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡8)።

በአጠቃላይ በተረኮቹ የተለያዩ ክፍሎች የገዳሙ ስርዓት አስቀድሞ ነበሩ በተባሉት ቀኖች አማካይነት የወጣ እንደሆነ ለማሳየት ይሞከራል፤ ይህ ደግሞ ገዳማውያኑ የገዳሙ ስርዓት ከቀደም ጀምሮ ሲሰራበት የቆየ፣ ብዙ ገዳማዊያንን ለቅድስና ያበቃና አስቀድመው የነበሩ ቅዱሳን በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ያወጡት እንደሆነ እንዲያምኑና እንዲጠብቁት ለማድረግ ተብሎ የተነገረ ይመስላል።

### 4.4.4 ቀኖች ገዳሙን በተደጋጋሚ እንደሚጎበኙት በመተረክ፣

በተረክ ሁለት እንደተጠቀሰው ድንግል ማርያም አገሯን አስራት፣ ስፍራዋን ደግሞ በቀን አንድ ጊዜ እንድትጎበኝ ቃልኪዳን ተቀበለች ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ከሌሎች ጋር በመሆንና በስዕለ አድህኖዋ ወይም ሌሎችን በመላክ ስትጎበኝ እንደነበር ተገልጿል።

ሌሎችን መላክን በተመለከተ አባ ሰላማን እና አብርሃ ወ አፅብሐን ወደ ጣና ቂርቆስ ሄደው የአዘዘቻቸውን እንዲፈፅሙ ማድረጓን በተረክ ሦስት ተገልጹአል፤ አባ ሠላማም ትዕዛዟን አክብረው ነገሥታቱን እና ሕዝቡን ሰብስበው ለመጀመሪያ ጊዜ በጣና ሐይቅ አጥመቀዋል፤ የጥምቀትንም ስርዓት መስርተዋል (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባ ቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡ 10) ፤ በኋላም በተረክ አራት ወለተ ጴጥሮስን ከዋልድባ ገዳም ወደ ጣና ቂርቆስ ገዳም በድንግል ማርያም መሪነት መጥታ በታዘዘችው መሰረት ከሴቶች ገዳም ያለችውን ቤተክርስቲያን አፍርሳ ሰርታታለች (ዝኒ ከማሁ ገፅ 3)።

ይህ ደግሞ ስለአባ ሰላማ የተነገረው ተረክ በገዳሙ ለሚኖሩ ወንድ ገዳማውያን፣ የወለተ ጴጥሮስ ደግሞ በሴቶች ገዳም ለሚኖሩ ሴት ገዳማውያት አብነት ሆኗቸው በእምነታቸው ጸንተው እንደኖሩ የተነገረ ይመስላል። ከተረኩ እንደምንገነዘበው ሁለቱም ሰዎች ወደዚህ ገዳም የመጡት በራሳቸው ፈቃድ ሳይሆን በድንግል ማርያም አማካይነት ነው። ይህም ደግሞ ገዳማውያኑ ለምንና ጣና ቂርቆስ ገዳም የመጡት የእነርሱ ፍላጎት ሳይሆን የድንግል ማርያም ምርጫ መሆኑን እንዲያምኑ የተነገረ ይመስላል።

ከሌሎች ጋር በመሆን በተመለከተ በተረክ አራት ሰሎሜን፣ ኤልሳቤጥን እናቷን ሀናን፣ ከአጋንንት ጋር ተዋግተው ድል የነሱትን ደናግልና መነኰሳትን በማስከተልና ከመላዕክት ጋር በመሆን እንደመጣች ተጠቅሷል(ዝኒ ከማሁ ገፅ 11)። ይህ ደግሞ በተለይ ድንግል ማርያ ም በቀን ለአንድ ሰዓት ት ባርከን ዘንድ ትመጣለች ብለው ለሚያምኑት ገዳማውያን፣ የምትመጣው ከብዙ ቅዱሳን ጋር እንደሆነና የእነርሱን በረከት ጭምር እናገኛለን ብለው እንዲያመኑ የሚያደርግ ይመስላል። በተለይ ደግሞ ደምበዛ የሴቶች ገዳም ላይ ድንግል ማርያም ለወለተ ጴጥሮስ ተገልጣ ስታነጋግራት ከቅድሳት አንስት ጋር መምጣቷ የገዳሙ መነኮሳዪያት ከድንግል ማርያም ጋር አብረው መጥተዋል የተባሉትን ቅዱሳት አንስት መንፈሳዊ ተጋድሎ እንዲከተሉ ያበረታታቸዋል (ዕብ.13፣7) አንድም እናንተም አጋንንትን ድል ከነሣችሁ በአፀደ ነፍስ ከድንግል ማርያም ሕብረት ይኖራችኋል ለማለት ወይም ቅዱሳን በአፀደ ሥጋ ከአለም ቢለዩም በአፀደ ነፍስ በታላቅ ክብር ሕያው ሆነው ይኖራሉ ለማለት ይሆናል

(ራእ.6፣9-11)። በሌላ መልኩ ደግሞ ተከትለዋት የመጡት ሴቶች ናቸውና ደምበዛ[7] ቁስቋም የተፈቀደው ለሴት ብቻ መሆኑን ለማሳየት ይመስላል።

በስዕለ አድህኖ አማካይነት ደግሞ በተረክ አራት ወለተ ጴጥሮስ በደምበዛ ቁስቋም ገዳም ሆና ስትፀልይ በኢየሩሳሌም በወንጌላዊው ሉቃስ እጅ ተስላ በጣና ቂርቆስ መቅደስ የነበረች ስዕለ ማርያም በተአምር ወደ ደምበዛ ቁስቋም መጥታ ለወለተ ጴጥሮስ እንደበት አውጥታ እንዳነጋገረቻት ተጠቅሷል (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡3)። ይህ ለገዳማውያኑ ድንግል ማርያም በአንድምበሌላ መንገድ ተገልፃ እንደምታነጋግር፣ ወይም የወለተ ጴጥሮስን የመንፈሳዊ ብቃት ደረጃ ለማሳየት የቀረበ ይመስላል። አንድም በገዳሙ ሴት ገዳማውያን ምንም እንኳ አበው ወደ ተቀበሩበት ገዳም ለመግባት ባይፈቀድላቸውም በደምበዛ ቁስቋም ሆነው ተግተው ቢፀልዩ በጣና ቂርቆስ ያለው በረከት ሁሉ ለእነርሱም ባሉበት እንደሚደርስ ለመጠቆም የገባ ይሆናል።

### 4.4.5 ዋኖቹ ከእነርሱ በታች ላሉት ጥበቃ እና ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ማሳየት፣

በተረክ ሦስት አባ ሰላማ ኢየሱስ ክርስቶስን ሕዝቡን በምን ላጥምቅ? ብሎ ሲጠይቅ ማጥመቂያ መስቀል፣ በማዕጠንት ጊዜ የሚያዝ መስቀል፣ ቅብአ ሜሮን፣ ፀሎተ እጣን፣ መጽሐፈ ክርስትና፣ መጽሐፈ ቅዳሴ፣ መጽሐፈ 4ቱ ወንጌላት 5 የአልባሳት እና ወርቀ ዘቦ እንደተሰጣቸው ተጠቅሷል (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992:10)፤ በተረክ አራት ደግሞ ወለተ ጴጥሮስ "አበው የተቀበሩበት መቅደስ ፀአና 3 ብርሃን ተተክሎበት አየዋለሁና መላዕክት ሲወጡባት

---

[7] ደምበዛ- አንድም ቅድስት ማርያም ወደ ኢትዮጵያ ተሰዳ ጣና ደሴት ስትደርስ በአካባቢው ያለውን ሰላም በኢየሩሳሌም በሄሮድስ ትዕዛዝ ከፈሰሰው ደም ጋር አነፃፅራ እንዴት በሃገሬ ደምበዛ በማለቷ ቦታው ደምበዛ መባሉን፤ አንድም በጣና ቂርቆስ ገዳም የነበሩት ንቡረ ዕድና ሊቃውንቱ የቦታውን ሥርዓት አጥብቀው ከመያዛቸው የተነሳ የተማረሩት መነኰሳት ኧረ ደንብ በዛ ብለው ባሉት መሠረት በጊዜ ሂደት የቦታው ስም ደምበዛ ተብሎ መጠራቱን፣ አንድም የአፄ ኢያሱ እናት ንግስት ምንትዋብ የወርቅ መስቀል እስከ ጉልላቱ አስይዛ ጣና ቂርቆስ ልትሰጥ ስትመጣ ከዚህ ገዳም ሴት አይገባም ቢሏት ሴት ምድሩን የማይረግጠው ከሆነ በላይ ግምጃ እያስነጠፍኩ በዚያ ላይ እሄዳለሁ በማለት ግምጃዋን እያስነጠፈች ወደገዳሙ ስትሄድ የወር አበባ መታት። ከኋላ ሆኖ የሚያጅባት ሰውም ኧረ ንግስት ኧረ ደምበዛ ይመለሱ በማለቱ የወጣ ስያሜ ነው። (መምህር ክፍለ ማርያም፤ ካሴት ቁጥር 4(B)፣ ጣና ቂርቆስ፣ ግንቦት 26፣2002)።

ሲወርዱባት አየዋለሁና ከዚህ መቅደስ ገብቼ ልሳለም እልሻለሁ" ብላ ስትጠይቅ ድንግል ማርያምም "ልጄ በስልጣኑ በአቡነ ሰላማ ከሳቴ አድሮ ከዚህ ደሴት ፀአና እናቶች እንዳይገቡ አውግዟል። ለአንቺ ለወዳጄ ወለተ ጴጥሮስ ግን የልጄ ፈቃድ ሆኖ ወደ ደምበዛ ቊስቋም እንድትገቢ ተፈቅዶልሻል" በማለት ከመለሰችላት በኋላ ወለተጴጥሮስን ሚካኤልና ገብርኤል በክንፋቸው ወስደው አስቀምጠዋት እንደተሰወሩ ተነግሯል።(ዝኒ ከማሁ ገፅ 3) ይህ ደግሞ ለገዳማውያኑ ፈተና ሲገጥማቸው የቅዱሳን ረዳትነት አይለያችሁም ለማለት የተነገረ ይመስላል።

### 4.4.6 ዋናው ፈጸመው ተብሎ በሚነገረው ገድል ስፍራውን ማስከበር፣

በተረክ አምስት ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን በጣና ደሴት ያሉትን ገዳማት ቅርስ ለመዝረፍ ሰባት መቶ ታንኳ ሠራዊት መላኩን፣ በደሴቶቹ ካሉት ገዳማት መካከልም የተወሰኑትን ዘርፈው ወደ ጣና ቂርቆስ ሲጓዙ ቅዱስ ቂርቆስ በነፋስ ሃይል ማዕበል አስነስቶ ሰባት መቶውንም ታንኳ ከነሠራዊቱ ማስመጡንና በገዳሙ ያለውን ቅርስም አለማዘረፉን ነው (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡ 26)።

ይህን ተረክ የሚሠማ ማንኛውም ሰው ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ይገነዘባል ተብሎ ይታመናል። የመጀመሪያው የቂርቆስን ፈጥኖ ተራዳኢነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዓለመ ምንኩስናን መርጠው በገዳሙ የተጠጉትን መነኰሳትና የተቀመጡትን ቅርሶች (ንዋየ ቅድሳት) ሊደርስባቸው ከታሰበው ጥቃት የሚታደግ መሆኑን ነው። ይህንን የበለጠ ለማጉላት ሌሎች በገዳሙ ተፈፅመዋል ተብሎ የሚነገሩትን ተረኮች ማንሳቱ ተገቢ ይመስላል።

በቅድሚያ በተረክ ስድስት አባ ሰላማ የአካባቢውን ሕዝብ እንዲያጠምቅ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተሠጠው የተባለው መስቀል በገዳሙ ውስጥ መስዋዕተ ሀዲስ ይሠዋበት ነበር ተብሎ በሚታመንበት ድንጋይ አጠገብ ምልክት ይሆን ዘንድ ተተክሎ ይኖር የነበረ ሲሆን አንድ ዕለት አንድ መነኩሴ ሠርቆ መውሰዱን፣ ቅዱስ ቂርቆስም ለመነኩሴው በሕፃን ልጅ ተመስሎ ሳላጠፋህ ዕቃዬን መልስ እያለ በሕልሙ የታየው መሆኑን፣ መነኩሴውም በነገሩ ፈርቶ ከገዳሙ በግምት ሦስት ኪሎ ሜትር ላይ በምትገኘው

ክርስቶስ ሰምራ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ አምጥቶ ተክሎት መሄዱን፣ በዚያም ቦታ ለረጅም ጊዜያት ተተክላ ከኖረች በኋላ ሌባ እንዳይወስዳት ተብሎ ወደ ጣና ቂርቆስ ገዳም ዕቃ ቤት እንድትገባ መደረጉን ይገልጻል።

በሌላ መልኩ ደግሞ በተረክ ሰባት አፄ አምደ ፅዮን ጦርነት ሲገጥሙ የቂርቆስን ታቦት ይዘው ስለሚሄዱ በተደጋጋሚ ድል ይቀናቸው የነበረ መሆኑን፣ በአንድ ወቅት በዘመቻው ድል አድርገው ሲመለሱ ታቦቱን ከቤተ መንግሥቱ ወደ ገዳሙ ላለመመለስ መወሰናቸውን፣ መኳንንቱም ይህን ታቦት ወደ ቦታው ካልመለሱ ሃይለኛ ስለሆነ በሠራዊቱ ላይ አንድ ነገር ያስመጣበዎታል ወይም ጦር ያስነሳበዎታል ማለታቸውን፣ ንጉሱም ሁኔታውን ለማወቅ በገዳሙ መነኮሳት ሱባኤ ማስያዛቸውን፣ ቅዱስ ቂርቆስም ወደ ቦታው መመለስ እንደሚፈልግ ለመነኮሳቱ በራዕይ ማሳየቱን፣ ንጉሱ ታቦቱን ወደ ገዳሙ ሲመልሱ በመኳንንቱ ምክር ተነሳስተው መጐናፀፊያውን ማስቀረታቸውን ቂርቆስም በሕልም ተገልፆ ሃይል ብሰጥህ እንዴት ይህን ታደርጋለህ? በማለት ንጉሱን መውቀሱንና ንጉሱም መልዕክተኞቹን ልኮ መጐናፀፊያውን እንዲመለሱ ማድረጉን ይጠቅሳል (መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 4A፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ ጣናቂርቆስ ገዳም)።

እንዲሁም በተረክ ስምንት በጣና ቂርቆስ ቅጥር ግቢ የተተከለው የእህል ወፍጮ ምክንያቱን ለማወቅ በሚያስቸግር ሁኔታ አልሰራ ማለቱና ከሴቶች ገዳም ሲወስዱት መስራቱን፣ በዚህ ምክንያት ቂርቆስ ሞተር አልፈቀደም ተብሎ ከጄኔቴተር መብራት ይልቅ በፀሐይ የሚሰራ መብራት መግባቱ ተገልጿል (አባ ወልደ ተንሳይ፣ሚያዝያ 22 ቀን 2003፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም)።

ከላይ ስለቂርቆስ የተነገሩት ተረኮች የቂርቆስን ቅርስ ጠባቂነትና ቅጥሩን ከማይፈልገው ነገር የሚከላከል መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህን ተረኮች ገዳማውያኑም ሆነ ሌላው ምዕመን ሲሰማ የቂርቆስን ፈጥኖ ተራዳኢነት፣ የገዳሙን ቅርስ (ንዋየ ቅድሳት)ና ክብ ር ጠባቂነት ስለሚገነዘቡ በአጋጣሚ ተሳስቶ ቅርስ ሊዘርፍ ወይም የተበጀውን ስርዓት ሊዳፈር ለሚሞክር ቅጣት እንደሚደርስበት ለማስጠንቀቅ የተነገረ ይመስላል።

## ምዕራፍ አምስት

## የጣና ቂርቆስ ገዳም ቁሳዊ ባህሎች

በዚህ ምዕራፍ ለትንታኔ የተመረጡትን ቁሳዊ ባህሎች ከሚሰጡት አገልግሎት አንፃር ከፋፍሎ ለማሳየት የተሞከረ ሲሆን፣ ቁሳዊ ባህሎቹ ያላቸው ተምሳሌታዊ ትርጉም ይዳሰሳል።

### 5.1 የኦሪት መስዋዕት ማቅረቢያ ቁሶች

#### 5.1.1 የድንጋይ መንበር

ይህ የድንጋይ መንበር የተባለው ከቂርቆስ ቤተክርስቲያን በስተደቡብ አቅጣጫ በግምት ሰባት ሜትር ርቀት ላይ ከአንድ ቋጥኝ ሥር መጠለያ ተሰርቶለት ይገኛል። መንበሩ ያለው አለታማ በሆነ ቦታ ላይ ሲሆን በርቀት ሲያዩት ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተፈልፍሎ ወይም ተጠርቦ የተሠራ እና አራት ማዕዘን ያለው ሲመስል ሲቀርቡ ግን የሦስት ድንጋዮች ንብርብር ሆኖ ይታያል። በዚህ የድንጋይ መንበር በዘመነ ብሉይ ለስድስት መቶ ዓመት ያህል መስዋዕተ ኦሪት እንደቀረበበት እና ይህ ቦታ ከእስራኤል ቀጥሎ አምልኮተ እግዚአብሔር የተፈፀመበት ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ ገዳማውያኑ ይናገራሉ(አባ ፍስሀ፣ ካሴት ቁጥር 1A፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም፣ግንቦት 25ቀን 2002 ዓም)። በመንበሩ መሃል ያለው ከፍታ አንድ ሜትር ተኩል ሲሆን ወለሉ አራት ማዕዘን የሆነና ከላይ ከአናቱ እንደ ስኒ የጎደጎደ ነው። ሌላዎቹ ሁለት ምሰሶ መሳይ ድንጋዮች ከፍታ ደግሞ አንድ ሜትር ሆኖ የሙቀጫ ቅርጽ ያላቸው እና ከአናታቸው ላይ ወደ አስር ሣንቲ ሜትር የጎደጎዱ ናቸው። ድንጋዮቹ አናት ላይ ያሉት ጉድጓዶች የመስዋዕቱን ደም ለማጠራቀም ያገለግላሉ። የመስዋዕቱ አቀራረብ ለመስዋዕት ከቀረበው ዕርድ ጥቂት ደም ድንጋዮቹ ላይ ከተረጨ በኋላ ቀሪው ደግሞ ታቦቱ ባለበት ድንኳን ላይ እና በጎድጓዳ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ ይተዋል (ጌታቸው፣ 1993:116)። የሦስቱ ድንጋዮች መነባበር የምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ ነው በማለት ይጠቅሳሉ (አባ ወልደ ገብርኤል፣ ካሴት ቁጥር 2A፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም፣ ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓም)። ይኸውም ስለኢየሱስ ክርስቶስ በድንጋይ መመሰል በመጽሐፍ

ቅዱስ ነብዩ ኢሳይያስ ሲናገር «እነሆ የተመረጠ እና የከበረን የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ»ብሏልና(ኢሳ.28፣ 16)። እንዲሁም ቅዱስ ዳዊት «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማይዘን ራስ ሆነ»ብሎ እንደተናገረ (መዝ.117፣22)እና በሀዲስ ኪዳን ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ «የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው»(ኤፌ.2፣ 21-22)ብሎ መስሎ ከተናገረው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ይመስላል።




ፎቶ ግራፍ 1፦ የመስዋተ ኦሪት ማቅረቢያ ነበር የሚባል የድንጋይ መንበር

### 5.1.2 ጎሞር

ጎሞር ከነሐስ ወይም ከሌላ ብረታብረት የሚሰራ ቁናመሳይ የእህል መስፈሪያ ዕቃ ነው። ይህ ዕቃ እስራኤላውያን ከግብፅ ተነስተው ወደ ከንዓን ባደረጉት የአርባ አመት የበርሀ ጉዞ እግዚአብሔር በዕየለቱ ለሚሰጣቸው መና ወይም ምግብ እያንዳንዱ ነፍስ(ሰው) የሚበላውን ያህል ይለቅምበት የነበረ እንደሆነ ይጠቀሳል(ዘጸ.16፣13-36)፤ በኋላም የጎሞር አገልግሎት ለመስዋዕተ ኦሪት የዋለ ሲሆን፣ በገዳሙ ያለው ጎሞር ከብረት የተሰራ ነው። ጎሞር እና ሌሎች በጣና ቂርቆስ ያሉት መሰዊያዎች በሲና በርሀ እና በፍልስጤም ውስጥ የሚታወቁት«ማሰቦት» በመባል እንደሆነ ይነገራል።

አገልግሎቱም የኦሪት ካህን ደም የያዘውን ጎሞር በግራ እጁ በመያዝ ቀኝ ጣቱን እቃው ውስጥ ነክሮ ለኃጢአቱ ማስተሰሪያ መስዋዕት እንዲሆነው በመሰውያው ግድግዳ ላይ እና ከዚያም በእግዚአብሄር ፊት ወይም በመቅደሱ መጋረጃ ፊት ሰባት ጊዜ ይረጫል፤ የተረፈውንም ደም ከመሰዊያው በታች እንዲንጠፈጠፍ ያደረጋል። (ጌታቸው፣ 1993:117)።



ፎቶ ግራፍ 2፦ መካከል ላይ ያለው ሳህን መሳይ ቁስ ጎሞር

ጎሞር በሙሴ እጅ ሦስት እፍኝ ነው (መጻሕፍተ ብሉያት አንድምታ ትርጓሜ 1999፣104)። ምናልባት አንድ ጎሞር ሦስት እፍኝ መና መያዙ የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ፣ የመናው መያዣ ጎሞር ደግሞ ምሳሌነቱ የድንግል ማርያም፣ መናው የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌ፣ መናው በጎሞሩ ላይ መቀመጡ እግዚአብሔር ወልድ በድንግል ማርያም ማህፀን ለማደሩ፣ በጎሞሩ የነበረው መና እስራኤላውያንን ምግበ ሥጋ እንደሆናቸው ሁሉ ከድንግል ማርያም የተገኘው እግዚአብሔር ወልድ በዚህ ዓለም ሲኖሩ የሕይወት እንጀራ ለመሆኑ ምሳሌ ሊሆን ይችላል(ዮሐ.6፣48-51)።

## 5.2 ከሥርዓተ አምልኮ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁሶች

### 5.2.1 ስውሩ ቤተ መቅደስ

ድንግል ማርያም በስደቷ ዘመን ወደ ጣና ደሴት ስትመጣ ደብተራ ኦሪቱ ነበረበት ከሚባልበት በስተምስራቅ በኩል ሃያ ሜትር አካባቢ ትልቅ ቋጥኝ ይገኛል። የዚህ ቋጥኝ ቁመቱ አራት ሜትር አካባቢ የሚደርስ ሲሆን ርዝመት ደግሞ ሃያ ሜትር ይደርሳል። በምዕራብ አቅጣጫ በቋጥኙ ላይ የመስቀል ምልክት ተቀርፆበታል። ድንግል ማርያምና ተከታዮቿ በስደት ዘመናቸው ወደዚህ ቦታ ለመጠለል ሲመጡ ይህ ቋጥኝ ተከፍቶ በውስጡ ዘጠኝ ስውር ቤተ መ ቅደስ መታየታቸውንና ድንግል ማርያምም ወደ ውስጠኛዎቹ ክፍሎች መግባቷን፣ በውስጡም ብዙ ስውር ቅዱሳን ማግኘቷን፣ ከየት እንደመጡ ስትጠይቃቸውም በነቢዩ ኤልያስ ዘመን እግዚአብሔር ለበዓል ያልሰገዱ 7 ሺህ ሰዎችን ደግሞ ከአንተ ጋር ትቻለህ(1ነገሥ.19፣10) ከተባሉት መካከል መሆናቸውን፣ ድንግል ማርያም ከስደት ወደ ኢየሩሳሌም ስትመለስ ቤተ መቅደሱ ተመልሶ መሰወሩን እና ወደ ፊት እንደሚከፈት ተስፋ እንደሚያደርጉ ገዳማውያኑ ይናገራሉ።

ይህ ስውር ቤተ መቅደስ የተባለው በመጽሐፍ ቅዱስ (ሕዝ.44÷1-2) ከተጠቀሰው ሀይለ ቃል ጋር ይመሳሰላል። ሀይለቃሉ "ወደ ምስራቅም ወደሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" በሚል ተጠቅሷል።

ይህን ሀይለ ቃል እሸቱና ደጀኔ (1987፡70) ሲተረጉሙ ምስራቅ የድንግል ማርያም፣ መቅደስ የማኅፀንዋ፣ የተዘጋው በር የማኅተመ ድንግልናዋ ምሳሌ መሆኑን፣ "ተዘግቶ ነበር" የሚለው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን ከመወለዱ በፊት ድንግል እንደነበረች፣ "ተዘግቶ ይኖራል። አይከፈትም" የሚለው ቃል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ከወለደች በኋላ ለዘላለም ድንግል ሆና እንደምትኖር የሚያሳይ ሲሆን ሰውም አይገባበትም መባሉ ድንግል ማርያም ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ሌላ ልጅ እንደሌላት የሚያመለክት ነው ይላሉ።

ይህች በቤተ መቅደስ የተመሰለችው ድንግል ማርያም ጣና ደሴት ስትደርስ የገባችው ተሠውሮ ይኖር ነበር ተብሎ በሚታመን ሌላ ቤተመቅደስ ሲሆን ነቢዩ ሕዝቅኤል ያየው ቤተ መቅደስ ተዘግቶ የነበረና ወደ ፊትም ተዘግቶ የሚኖር ነው እንደተባለው ሁሉ ድንግል ማርያምም ገብታበታለች ተብሎ የነበረና አሁንም ተዘግቶ የሚገኝ (በስዕል ይህ ነው ተብሎ ከመታየቱ በስተቀር አንድ ትልቅ ቋጥኝ ሆኖ የሚታይ) ነው።


የሕዝቅኤል ቤተመቅደስ በምስራቅ አቅጣጫ ነበር ተብሏል። በተመሳሳይ ድንግል ማርያም ገብታበታለች የተባለውም ቤተ መቅደስ (ቋጥኝ) ደብተራ ኦሪቱ ነበረበት ከተባለው ወይም ከጣና ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን በስተምስራቅ በኩል ይገኛል። የዚህ ቤተ መቅደስ አለ መባሉ አንድም ድንግል ማርያም በስደት ጣና ደሴት ስትቆይ የእርሷም ክብር ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ስለሆነ፣ በሌላ በኩል ከሦስቱ አካል አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በእቅፏ ስለነበር፣ አንድም በቀንም በሌሊትም የሚያመሰግኑና ለተልዕኮ የሚፋጠኑ መላዕክተ ሰማይ እና ቅዱሳን (ሰሎሜና ዮሴፍ) ስለሚገኙ በደሴቲቱ ሲኖሩ በአንድ ስፍራ ቦታ ተሰጥቷቸው ተቀመጡ መባሉ ለክብራቸው የሚመጥንና ለሰው ጆሮ የሚጥም ባለመሆኑ ስውር ቤተመቅደስ ነበር መባሉ ለጊዜው ለክብራቸው፤ በኋላም ለትውልዱ የአረፉበት ቦታ ትልቅነት ለማሳወቅ የተነገረ ይመስላል።

አንድም ድንግል ማርያም ዕድገቷ በቤተ መቅደስ ነበርና (ነገረ ማርያም፣1985:13) ያለ ዕድገቷ በስደት ኖረች መባሉ አግባብ ስላልሆነ፣ አንድም ድንግል ማርያም ወደ ግብፅ ተሰዳ ደብረ ቁስቋም ላይ የሄሮድስ ሠራዊት ሲደርሱበት በአካባቢው ያለች አንድ ውስጧ ክፍት በሆነች የሾላ ግንድ ተደብቀዋል ይባላልና (ተአምረ ማሪያም፣ 1998:35) ሠራዊቱ ወደ ጣና ደሴት ቢመጣ እንዴት ያመልጡ ነበር ለሚለው ምላሽ ለመስጠት ስውሩ ቤተመቅደስ ታስቦ ሊሆን ይችላል።

ድንግል ማርያም ከደሴቱ ስትደርስ ስውሩ ቤተመቅደስ ተከፍቶ ስትገባ በውስጡ በነቢዩ ኤልያስ ዘመን የነበሩ ቅዱሳን ማግኘቷን ተጠቅሷል። በመጽሐፈ ነገሥት በኤልዛቤልና በአክዓብ ዘመነ መንግሥት ለበዓል (ለጣኦቱ) ያልሰገዱ ሁሉ ይገደሉ፣ ነቢያቱም ይሳደዱ ስለነበር ነቢዩ ኤልያስ ለፈጣሪው ብቻየን ቀርቻለሁና ውሰደኝ ብሎ እስከመለመን ደርሶ ነበር። እግዚአብሔርም ኤልያስን ብቻህን አይደለም ለበዓል

ያልሰገዱ 7 ሺህ ሰዎች አሉ በማለት መልሶለታል (1ነገሥ.19፣ 10-18፤ ሮሜ.11፣ 3-5)። እነዚህ በስውሩ ቤተመቅደስ ተገኙ የተባሉትም በኤልያስ ዘመን ኤልዛቤል ስታሳድዳቸው ወደ ኢትዮጵያ የመጡና በዚህ በስውር የሚኖሩ መሆናቸው ነው የተጠቀሰው(መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 4A፣ ግንቦት 26 ቀን 2002፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም)።

ይህ መባሉ አንድም ስፍራው አስቀድሞ ታቦተ ፅዮንን እና የእስራኤል በኩራትን፣ በኋላም ድንግል ማርያምና ተከታዮቿን እንዳስጠጋ ሁሉ አሁንም ከአለም ርቀው ወደዚህ ገዳም የሚመጡትን ገዳማውያን የምታስጠጋ (ምስካየ ኅዙናን) መሆኗን ለማጠየቅ ይሆናል። ወይም ቦታው ድንግል ማርያምና ተከታዮቿ መጥተው በስደት ከማረፋቸው በፊት ለሌሎች ቅዱሳንም ማረፊያ መሆኑን ለማሳየት፣ አንድም አሁን በገዳሙ ለሚኖሩ መነኰሳት የሚራዱቸው በዙሪያቸው ስውር ቅዱሳን መኖራቸውን እንዲያምኑ ለማድረግ ሊሆን ይችላል።



ፎቶ ግራፍ 3 ፦ስውር ዘጠኝ ቤተ መቅደስ የሚባለው


ይህ ደግሞ በቦታው ለሚኖሩ ገዳማውያን ዝናውን ቦታው ታላቅ ክብር ያለውና ከአለም ተሰደው ለሚመጡ መጠጊያ መሆኑን እንዲያምኑ የሚያደርግ ሲሆን ዝናውን ሰምተው ለሚመጡ ምዕመናን ደግሞ በረከት እናገኛለን ብለው እንዲያስቡ በማድረግ በኩል አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

### 5.2.2 ድንግል ማርያም አርፋበታለች የሚባለው ቦታ፣ ስዕለ አድህኖ እና ዱካዎቹ፣

ድንግል ማርያም አርፋባታለች የሚባለው ቦታ ስውሩ ቤተመቅደስ ከሚባለው ቋጥኝ አናት ላይ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በግምት ከ8-10 ሜትር ይደርሳል፤ወደ ስፍራው ለመሄድ ቋጥኙ ላይ እንደተወጣ የቅድስት ማርያም፣ የሕጻኑ የኢየሱስ ክርስቶስ እና የአህያዋ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው ዱካዎች ይታያሉ። ከስፍራው እንደተደረሰ ከላሜራ በተሰራች፣ ርዝመቷ አንድ ሜትር በምትሆን፣ የጎኗ ስፋት ሃምሳ በሃምሳ ሳንቲ ሜትር በሚገመት አራት ማዕዘን ያላት መጠለያ ትገኛለች። በውስጧ ድንግል ማርያም ሕጻኑን ኢየሱስ ክርስቶስን ታቅፋ የሚያሳይ ስዕለ አድህኖ ተቀምጦባታል። መጠለያዋ የተሰራችው ከሦስት አመት ወዲህ አባ ገብረ ሥላሴ በሚባሉ ነጋዴ ሲሆን ያሰሩበት ዋናው ምክንያት የቦታውን ክብር ለማስጠበቅና በረከት ለማግኘት በማሰብ ነው። ከዚያም ማህበረ መነኮሳቱ በውስጧ ስዕለ አድህኖ እንዲቀመጥ አድርገዋል። የመጠለያዋ አሰራር በአዲስ አበባ ካሉ አንዳንድ አድባራት ቅጥር ጊቢ ውስጥ በላሜራ ብረት ከሚሰሩት መጠነኛ የስሕለ አድህኖ ማስቀመጫ መጠለያዎች ጋር ይመሳሰላል።



ፎቶግራፍ 4፦ የድንግል ማርያም ያረፈችበት የሚባለው ቦታ



ፎቶግራፍ 5፦ የድንግል ማርያም እግሯ ዱካ የሚባለው

ወደ ገዳሙ የሚመጡ የእምነቱ ተከታዮች ቦታው ላይ ተገኝተው ሰግደው እና ጸልየው ይመለሳሉ። በቦታው ስህለ አድህኖው መቀመጡ ከዘመናት በፊት ድንግል ማርያም በስፍራው ልጇን አቅፋ ለመቀመጧ ምሳሌ መሆኑን፣ አማንያኑም በስህለ አድህኖው

አማካይነት በዚህ ቦታ በዚህ መልኩ ተቀምጣ እንደነበር እንዲያስታውሱ ለማድረግ ተብሎ መቀመጡን፣ በመጠለያ መከለሉ የቦታውን ክብር ለመጠበቅ እና ሰዎች ቦታውን ረግጠው እንዳያረክሱት ለመከላከል እንደሆነ ይናገራሉ (አባ ወልደ ገብርኤል፣ ካሴት ቁጥር 2A ግንቦት 25 ቀን 2002)።

የሕጻኑ ኢየሱስ ክርስቶስ እና የድንግል ማርያም ዱካዎች ናቸው ተብሎ በሚታመንባቸው ቦታዎች ላይ ምዕመናኑ ሲደርሱ ወድቀው የሚሰግዱ እና ፊታቸውንም ዱካ በሚመስለው ነገር ላይ እየጠራረጉ ያባብሳሉ። ከዚያም ባሻገር ገዳማውያኑ ድንግል ማርያም ቦታው ድረስ መምጣቷን ሲተርኩ እነዚህን ዱካ መሳይ ነገሮች ለመምጣቷ እንደማረጋገጫነት ይጠቀሙበታል።

### 5.2.3. የአህያዋ ሽኮና ያረፈበት ነው ተብሎ የሚታመንበት ዱካ፣

በገዳሙ ቅጥር ጊቢ የአህያዋ ሽኮና ያረፈበት ነው ተብሎ የሚታመንበት ዱካ የሚገኘው ስውሩ ቤተመቅደስ ተብሎ ከሚታመንበት ቋጥኝ አናት ላይ ነው። በጥናቱ ለማየት የተሞከረው ዱካ ነው ተብሎ በሚታመነው ጎድጓዳ ነገር ላይ ሳይሆን ስለዱካው ሲታሰብ በዋናነት በሚታወሰው አህያ ላይ ይሆናል። አህያ፤ የቤት እንስሳ፣ ዐመደ በል፣ ጭነት ተሸካሚ እና የጋማ ከብት እንደሆነች ይጠቀሳል (ደስታ፣1962:88) ። አህያ ሥጋቸው ከማይበላ የእንስሳት ወገን ስትሆን እንደፈረስ በቅሎ እና ግመል የጭነት አገልግሎት በመስጠት ታገለግላለች። በመጽሐፍ ቅዱስ«እነርሱም እህሉን በአህዮቻቸው ላይ ጫኑ» (ዘፍ.42፣26) በማለት አህያ ከኦሪት ጀምሮ የሸክም ስራ እንደምትሰራ ተገልጿል።

ከዚህ በተጨማሪ ለሰው ማጓጓዣ ስለማገልገሏ «ወደ እግዚአብሔር ሰው በፍጥነት ደርሼ እመለስ ዘንድ አንድ ሎሌ እና አንድ አህያ ላክልኝ» (2ነገ.4፣22) ። እና «አህያውን ጫኑልኝ አላቸው፤ አህያውን በጫኑለት ጊዜ ተቀመጠበት» (1ነገ.13፣ 13) ተብሎ ተጽፏል።

በአንዳንድ የአገራችን ባህል አህያ ለእቃ መጫኛነት እና ለሰው ማጓጓዣነት ከሚሰጠው አገልግሎት ይልቅ ላላዋቂ ወይም ለማያስብ ሰው መገለጫ ሆና ታገለግላለች። በአማርኛ ከተነገሩት ምሳሌያዊ አባባሎችም መካከል ስለ አህያ የተነገሩትን ስንመለከት የአህያ

ባል ከጅብ አያስጥልም፤ ጅብ ሊወጉ ከአህያ ይጠጉ፤ የአህያ ሥጋ አልጋ ሲሉት አመድ እና የመሳሰሉት ከቤት እንስሳት መካከል አህያ የተናቀች መሆኗን የሚያሳዩ ናቸው።

በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ አህያ ከሰው ማጓጓዣነት እና ከጭነት አገልግሎት ባሻገር ከሰው የተሻለ ተፈጥሮአዊ ባህርይ እንዳላት ይጠቅሳል። በ ለዓም የተባለው ሀብተመርገም የተሠጠው ሰው ባላቅ ከተባለው የሞዓብ ንጉሥ በመስማማት እስራኤልን ሊረግም አህያውን ጭኖ ወደ ሞዓብ ምድር ሲጓዝ ከበለዓም ይልቅ አህያዋ የእግዚአብሔርን መልአክ አይታ መቆሟን እና አንደበትም አውጥታ ከበለዓም ጋር ተከራክራለች (ዘኁ.22፣21_35)። ነብዩ ኢሳይያስም «በሬም የገዥውን አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ እስራኤል ግን አላወቀኝም ሕዝቤም አላስተዋለም» (ኢ.ሳ.1፣3)። በማለት ከሰው ይልቅ አህያ አስተዋይ እንደሆነች ይጠቅሳል።

በሀዲስ ኪዳንም አህያ ትልቅ ቦታ እንደተሰጣት ይነገራል።ይኸውም በሆሳዕና ዕለት ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ፋጌ ታስረው የነበሩትን እናት እና ልጅ አህዮች አስፈትቶ ወደ ኢየሩሳሌም በምስጋና መግባቱ ነው (ሉ.ቃ.18፣28-40) ። ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተቀምጦ መጓዙ እና የታሰሩትን ማስፈታቱ ምሳሌነት እንዳለው ይጠቀሳል።

የመጀመሪያው አህያዎቹ የምዕመናን ምሳሌ ተደርገው ይታያሉ፤ ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ አህያዎቹን ፈትታችሁ አምጡልኝ ማለቱ ሰው ሁሉ ከማዕሰረ ኃጥአቱ የሚፈታበት ጊዜ ለመድረሱ፤ አህያዎቹም ተሠርቀው የታሰሩ ነበሩ መባሉ ዲያብሎስ ሰርቆ በሲኦል ያሰራቸው ነፍሳት ነፃ ለመውጣታቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ባልተቀመጠበት ውርንጫ ላይ መቀመጡ በንፁሐን መሃይማን (አማንያን) አድሮባቸው ለመኖሩ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያዎቹ በመቀመጡ አህያዎቹ በተነጠፈ ልብስ ላይ መጓዛቸው፤ ሰዎችም የእግዚአብሔር መንፈስ ካደረባቸው እንዲሁ ይከብራሉ ለማለቱ ምሳሌ ነው ይባላል (አባይነህ፣ 1994፣ 132)።

ሁለተኛው አህያ የሠላም ምልክት ተደርጋ ትወሰዳለች። በዘመነ ብሉይ ነቢያት የጠብ ዘመን ሲመጣ በፈረስ ተቀምጠው ዘገር ነጥቀው ይታያሉ፤ ዘመነ ሠላም ሲመጣ ዳግም በአህያ ተቀምጠው መነሳነስ ይዘው ይዞራሉ። አየሱስም በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ ሰላምሽ እኔ ነኝ ማለቱ ነው (ሉ.ቃ.19፣42)። አንድም ለሰው ልጅ

ሁሉ ሠላም እና ደስታ የሚሆንበት ጊዜ ደርሷል ሲል ነው (ዮሐ.20፣19-26 ፤ ቆላ.1፣ 20)።

ሦስተኛው አህያዎቹ የእስራኤል እና የአሕዛብ ምሳሌ ሆነው ይታያሉ የሚለው ነው። እናቲቱ አህያ የእስራኤል፣ ውርንጫዋ ደግሞ የአሕዛብ ምሳሌ ስትሆን፤ እናት አህያ የሠረገላ ቀንበር መሸከም የለመደች እንደሆነች ሁሉ እስራኤልም ሕግን (ኦሪትን) መጠበቅ ለምደዋልና፤ ውርንጫዋ የሠረገላ ቀንበር ገና ያልለመደች እንደሆነች ሁሉ አሕዛብም ሕግ መጠበቅ ያለመዱ ናቸውና። ኢየሱስ በውረንጫ ላይ መቀመጡ አሕዛብ በእርሱ ከአመኑ እና ልቡናቸውን ለማደሪያነት ከቀደሱ እርሱም በእነርሱ አድራለሁ ለማለቱ ምሳሌ ነው።

አራተኛ እናቷ አህያ የኦሪት ውርንጫዋ ደግሞ የሀዲስ (የወንጌል) ምሳሌዎች ናቸው። እናት አህያ ቀንበር መሸከም የለመደች እንደሆነች ሁሉ ኦሪትም የተለመደች ሕግ ናትና፤ ውርንጫዋ ቀንበር መሸከም ያለመደች እንደሆነች ሁሉ ወንጌልም በዚያ ወቅት ያልተለመደች አዲስ ሕግ ናትና (አባይነህ፣ 1994፣ 131-134)።

ከዚህ በመነሳት ድንግል ማርያምን እና ህጻኑን ይዛ ወደ ጣና ቂርቆስ መጥታለች የተባለችውን አህያ ለመፈከር ይሞከራል። አስቀድሞ ሀብተ መርገም የተሰጠው ተብሎ የተጠቀሰው በለዓም በሞዓብ (በአሕዛብ) ንጉሥ ታዞ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነውን እስራኤልን ለመርገም ሲጓዝ የእግዚአብሔርን መልአክ ከበልዓም ይልቅ አህያዋ እንደተመለከተችው ሁሉ የመርገም ፀጋ የተሰጠው በለዓም የንግሥና ፀጋ ለተሰጠው ሄሮድስ ምሳሌ፣ ንጉሥ ሞዓብ በለዓምን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እርገምልኝ ማለቱ፣ ሰይጣን በሄሮድስ አድሮ እግዚአብሔርን ልጅ የሆነውን ኢየሱስን ለመግደል ለመነሳሳቱ፣ የበለዓም አህያ መልአኩን ስታይ በለዓም ግን አለማየቱ ንጉስ ሄሮድስ የኢየሱስን አምላክነት ሳያውቅ ለማሳደዱ፣ አህያዋ ከበለዓም ይልቅ መልአኩን ለማየት ለመታዘዝ እንደቻለች ሁሉ የኢየሱስን አምላክነት አውቃ በተሰጣት ፀጋ ለማገልገሏን (ተሸክማ ለመሰደዷ) ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

በሌላ መልኩ አህያዋ የሰላም ምልክት ልትሆን ትችላለች። በዘመነ ብሉይ ነብያት ዘመነ ሰላም ሲመጣ በአህያ ላይ ተቀምጠው መነሳነስ ይዘው እንደሚታዩት ሁሉ፣ በዘመነ ሀዲስም ኢየሱስ በአህያዋና በውርንጫዋ ላይ ተቀምጦ ሰላምን ሰብኳል

(አባይነህ፣1994:134)። ኢየሱስ እና እናቱን ተሸክማ ወደ ጣና ደሴት የመጣችው አህያም ለደረሰችበት ስፍራ ለኢትዮጵያ የሰላም (የወንጌል) ጊዜ መድረሱን የምታመላክት፣ የተሸከመችው ኢየሱስ ደግሞ የሰላም ባለቤት ነው ለማለት ይመስላል።

አንድም አስቀድሞ በምሳሌያዊ አባባሎቹ ለመግለጽ እንደተሞከረው አህያ በኢትዮጵያ አንዳንድ አካባቢዎች ከእንስሳት ሁሉ በተለየ ሁኔታ የአላዋቂ ሰው መገለጫ እና የተናቀችም ናት። ኢየሱስ በእርሷ ላይ መቀመጡ የተናቁትን የሚያከብር፣ ፍጥረታት ሁሉ በእርሱ ዘንድ እኩል መሆናቸውን ለማሳየት ይመስላል።

አንድም በፈረስ ወይም በበቅሎ የተጫነን ሰው በሩቅ ሲያዩት አመጣጡ ለሰላም ይሁን ለጦር አይታወቅም። በአህያ የሚጫን ግን እንደ ድሃ ስለሚቆጠር በሚጓዝበት ሁሉ እንብዛም መሰናክል አያጋጥመውም። ኢየሱስ እና እናቱ ከእስራኤል ሲነሱ በበቅሎ ወይም በፈረስ ቢጓዙ በመንገዳቸው ችግር እንዳያጋጥማቸው የሰጉ ይመስላል።

አንድም አህያ ከበቅሎና ከፈረስ ጋር ስትነፃፃር ፍጥነት ስለሌላት የተጫነባት ሰው በድንገት ደርሶ አደጋ ጥሎ ያልፋል ተብሎ ስለማይገመት አህያ የሰላማዊ ሰው መጫኛ ተደርጋ ትቆጠራለች፤ አልያም አህያ የምትገዛው በርካሽ ዋጋ ስለሆነ የተሸከመችው ሰው ድሃ እንደሆነ ይገመታል። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላማዊ እና በምድር ላይ ምንም ሀብት እና ንብረት የሌለው መሆኑን ለማሳየት ለጉዞው አህያ የተመረጠች ይመስላል።

አንድም በመጽሐፍ ቅዱስ አህያ ከእንስሳት ወገን ስጋዋ የማይበላ እንደ ርኩስ ትቆጠራለች፤ ሆኖም በሀዲስ ኪዳን ሁሉም ነገር ቅዱስ መሆኑን ለማሳየት ቅዱስ ነገር ተጭኖባታል ለማለት ይመስላል።



ፎቶ ግራፍ 6፦ የአህያዋ ዱካ የተባለው

### 5.2.4. ደወል

የገዳሙ ደወል ከነሀስ የተሰራ እና አፄ ኢዮአስ በዘመነ መንግስታቸው ለገዳሙ ያበረከቱት እንደሆነ ይነገራል። የደወሉ ቅርፅ ከላይ ጠበብ ብሎ ወደታች ሰፋ እያለ የሚሄድ የቃጨል ቅርፅ ያለው ነው። ክብደቱ ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሰው ለብቻው ሊያነሳው ያስቸግራል። የተቀመጠው መሬት ላይ ነው። በጥንት ዘመን መደበኛ አገልግሎቱ  መጋቢው የጸሎት ሰዓት መድረሱን ለማህበረ መነኰሳቱ የሚያሳውቅበት እንደነበር ይነገራል፤ ሆኖም በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ለመሳለም የሚመጡ ምዕመናን ግን ደወሉ ከሰማይ የወረደ ነው ይላሉ፤ በመሆኑም ደወሉ ኃጢአት ላለበት ይከብዳል ኃጢአት ለሌለበት ይቀላል ብለው ያምናሉ። ደውሉንም መሸከም የቻለ ኃጢአት እንደሌለበት ያልቻለ ደግሞ ኃጢአት እንዳለበት ስለሚቆጠር ወደገዳሙ የሚመጡ ምዕመናን ኃጢአት እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው ለማረጋገጥ ሲሉ ደወሉን ተሸክሞ ለማሳየት ይሞክራሉ(አባ ወልደ ገብርኤል፣ ካሴት ቁጥር 2A፣ ግንቦት 25 ቀን 2002)። ከላይ የተጠቀሱት ቁሶች ለአምልኮ መፈፀሚያ ከማገልገላቸው ባሻገር የስፍራውን ቅዱስነት ለማሳየትም ይጠቅማሉ፤ ይኸውም ቦታው ቅዱስ በመሆኑ፣ከሌሎች ቦታዎች በተለየ ሁኔታ ድንግል ማርያምና ተከታዮቿን ማስተናገድ እና ቅዱስ ነገር ከሰማይ ማውረድ መቻሉን ስለሚገለፅባቸው ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ በቁሳዊ ባህሎቹ አማካይነት ድንግል ማርያምና ተከታዮቿ ከቦታው ድረስ መጥተዋል ብለው የሚናገሩት ነገር በአድማጭ ዘንድ እምነት እንዲያገኝ እንደማስረጃ ይጠቀሙበታል።

## 5.3 ገዳማውያኑ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው የሚጠቀሙባቸው ቁሶች

### 5.3.1.ገዳሙ የሚጠቀምበት የሰዓት አቆጣጠር ሰንጠረዥ

ገዳሙ የራሱ የሆነ የሰዓት አቆጣጠር ይከተላል። የሰዓት አቆጣጠሩም የጫማ /የፀሐይ/ ስፍር በመባል ይጠሩታል። የሰዓት አጠቃቀሙ በአንዳንድ የአገራችን ክፍል በተለምዶ ፀሐይ ሙሉ በሙሉ በምታገኘው ቦታ ላይ በትር በመትከል ወይም የራስን ጥላ በማየት ሰዓትን ከመገመት ጋር ተመሳሳይነት አለው። እንደ መምህር ክፍለ ማርያም አነጋገር ይህን የሰዓት አቆጣጠር የጀመረው ፊሊጶስ ንጉሠ ዕርዕ እንደሆነ ይጠቀሳል። ንጉሥ ፊሊጶስ አንድ ዕለት ወደሰማይ ሲመለከት መላዕክት ፀሃይን እያሽከረከሩ በየሦስት ሰዓቱ ልዩነት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ ተመለከተ። ንጉሱም እኔስ ይህንን አይቼ አመሰገንሁህ የኋላ ፍጥረት ምን ብሎ ሊያመሰግንህ ነው ብሎ ወደ ፈጣሪው ቢፀልይ መልአከ እግዚአብሔር ተገልያለት የፀሎት ጊዜያቱን በፀሐይ ስፍር /በጫማ/ እንዴት መለካት እንደሚችል ነገረው።

ይኸውም መላዕክት በየሰዓቱ ፀሐይን አሽከርክረው በሚያጠናቅቁበት ወይም ዕረፍት አድርገው ምስጋና በሚጀምሩበት ሰዓት ጥላህ የደረሰበትን ርዝመት በራስህ ጫማ ስፈረውና መዝግበህ ያዘው የሚል ነው።

ንጉሱም በየሦስት ሰዓቱ ያለውን የጥላ ርዝመት መልአኩ በአመላከተው መሠረት ሰፈረው። የጫማ ስፍሩና መላዕክት ፀሐይን አሽከርክረው የሚያቆሙበት ወይም ፈጣሪያቸውን ማመስገን የሚጀምሩበት ሰዓት እኩል ሆኖ አገኘው። ከዚያ በኋላ በቤተ መንግስቱ ያሉት ክርስቲያኖች ሁሉ በጫማ (በፀሐይ) ስፍሩ መሠረት እንዲፀልዩ አወጀ። ይህ ልማድ ሲያያዝ መጥቶ በሂደት ከቤተ መንግስት ወደ ቤተክርስቲያን ገባ። ጣና ቂርቆስም ለንጉሥ ፊሊጶስ እግዚአብሔር የገለፀለትን የፀሎት ጊዜያት ተቀብሎና አክብሮ እየተገለገለበት መሆኑን ይገልፃል (ካሴት ቁጥር 5(A)፣ጣና ቂርቆስ ገዳም፣ ግንቦት 26፣ 2002)።

የጥላው ርዝመት የሚለካው በባለ ጥላው ጫማ ብቻ ሲሆን የጥላው ርዝመት በየወሩ የተለያየ ሊሆን ይችላል።መስከረም ወር የሰለስቱ 10 ጫማ፣ የስድስቱ አራት ጫማ፣ የተሰዓቱ አስር ጫማ፤ የጥቅምቱ የሰለስቱ 12 ጫማ፣ የስድስቱ ስድስት ጫማ፣

የተሰዓቱ 12 ጫማ፤ የህዳር የሰለስቱ 13 ጫማ፣ የስድስቱ ሰባት ጫማ፣ የተሰዓቱ 13 ጫማ፤ የታህሣስ የሰለስቱ 15 ጫማ፣ የስድስቱ 9 ጫማ፣ የተሰዓቱ 15 ጫማ፤ የጥር የሰለስቱ 13 ጫማ፣ የስድስቱ 7 ጫማ፣ የተሰዓቱ 13 ጫማ፤ የየካቲት የሰለስቱ 12 ጫማ፣ የስድስቱ 6 ጫማ የተሰዓቱ 12 ጫማ፤ የመጋቢት የሰለስቱ 10 ጫማ፣ የስድስቱ 4 ጫማ፣ የተሰዓቱ 10 ጫማ፤ የሚያዝያ የሰለስቱ 9 ጫማ፣ የስድስቱ 3 ጫማ፣ የተሰዓቱ 9 ጫማ፤ የግንቦት የሰለስቱ 7 ጫማ፣ የስድስቱ 1 ጫማ፣ የተሰዓቱ 7 ጫማ፤ የሰኔ የሰለስቱ 6 ጫማ፣ የስድስቱ አልቦ ጫማ፣ የተሰዓቱ 6 ጫማ፤ የሐምሌ የሰለስቱ 7 ጫማ፣ የስድስቱ 1 ጫማ፣ የተሰዓቱ 7 ጫማ፤ የነሐሴ የሰለስቱ 9 ጫማ፣ የስድስቱ 3 ጫማ፣ የተሰዓቱ 7 ጫማ፤ የጳጉሜን የሰለስቱ 9 ጫማ፣ የስድስቱ 3 ጫማ፣ የተሰዓቱ 9 ጫማ ሲሆን የሰርክ ከመስከረም እስከ ጳጉሜን ድረስ 70 ጫማ ይሆናል።

ከሠርክ ጀምሮ እስከ ጥዋት ድረስ ባሉት የጸሎት ጊዜያት ፀሐይ ባለመኖሯ በጫማ ስፍር አይጠቀሙም። በመሆኑም መነኰሳቱ የምሽቱን ሦስት ሰዓት፣ የመንፈቀ ሌሊቱንና የማለዳውን ጸሎት የሚያደርሱት የእጅ ሰዓት በመጠቀም ነው፤ ሆኖም የእጅ ሰዓት ከመጠቀማቸው አስቀድሞ የመንፈቀ ሌሊቱንና የማለዳውን የጸሎት ለማድረስ በምን ይጠቀሙ እንደነበር የሚታወቅ ነገር የለም ምናልባት ተለምዷዊ ወይም ግምታዊ በሆነ መንገድ ሊሆን ይችላል።

የገዳሙ መነኰሳት የሚጠቀሙበት የጫማ (የፀሃይ) ስፍር ዘመኑ ካፈራው የእጅ ሰዓት ጋር አገናዝበው በሠንጠረዥ እንዴት እንዳቀረቡት በሚከተለው መልኩ ለማሳየት ይሞከራል።

| የፀሐይ ሰዓት | ☼ መስከረም | ☼ ጥቅምት | ☼ ህዳር | ☼ ታሕሣስ | ☼ ጥር | ☼ የካቲት | ☼ መጋቢት | ☼ ሚያዝያ | ☼ ግንቦት | ☼ ሰኔ | ☼ ሐምሌ | ☼ ነሐሴ | ☼ ጳጉሜን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ነግህ | 2:50<br>10<br>2:45 | 2:30<br>12<br>2:39 | 2:29<br>13<br>2:46 | 2:40<br>15<br>2:50 | 3:00<br>13<br>2:50 | 3:05<br>12<br>2:50 | 3:08<br>10<br>2:50 | 2:55<br>9<br>2:53 | 3:15<br>7<br>3:20 | 3:45<br>6<br>3:45 | 3:27<br>7<br>3:30 | 3:06<br>9<br>3:00 | 3:00<br>9<br>3:00 |
| ነድስቱ፡ | 8:10<br>4<br>7:43 | 8:35<br>6<br>8:20 | 8:37<br>7<br>8:26 | 9:00<br>7<br>9:45 | 8:45<br>7<br>9:13 | 8:35<br>6<br>9:05 | 8:00<br>4<br>8:22 | 7:55<br>3<br>7:50 | 6:55<br>1<br>6:35 | 6:30<br>አልቦ<br>6:30 | 6:40<br>1<br>7:05 | 8:00<br>3<br>7:50 | 7:50<br>3<br>7:50 |
| ተሰዓቱ፡ | 10:06<br>10<br>9:45 | 10:03<br>12<br>9:48 | 10:00<br>13<br>9:58 | 10:10<br>15<br>10:25 | 10:13<br>15<br>10:33 | 10:22<br>12<br>10:34 | 10:10<br>10<br>10:15 | 10:00<br>9<br>10:03 | 9:40<br>7<br>9:38 | 9:08<br>6<br>9:16 | 9:46<br>7<br>9:50 | 10:12<br>9<br>9:55 | 9:55<br>9<br>9:55 |
| ሰርክ | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 | 12:00<br>70<br>12:00 |

መግለጫ

- ከጫማው ስፍር በላይ የተፃፈው አኃዛዊ የሰዓት ስፍር ከላይ ከተጠቀሰው ወርህ ከ1 እስከ 15 ባሉት ዕለት ያገለግላል
- የመሀሉ የጫማ ስፍር ሰዓት ነው
- ከጫማው ሥፍር በታች የተፃፈው አኃዛዊ የሰዓት ስፍር ከላይ ከተጠቀሰው ወር ካ16 እስከ 30 ዕለት ያገለግላል

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ሠንጠረዥ መሠረት ማህበረ መነኰሳቱ ሰዓት እየጠበቁ ፀሎት ያደርሳሉ። ገዳማውያኑ ይህን የሰዓት አቆጣጠር ከየት መጣው ከፈጣሪያችን ነው ብለው ስለሚያምኑ የጸሎት ሰዓቶቹን አክብረው ሲጸልዩ ከሰማይ መላዕክት ጸሎት ጋር (በአንድ ጊዜ የሚፈጸም) ሕብረት ያለው ጸሎት እንደሆነ እንዲያስቡ ስለሚያደርጋቸው ሰዓቱን ሳያስታጉሉ ወይም ሳይሸራርፉ እንዲጸልዩ ሊያግዛቸው ይችላል።

### 5.3.2.መሶበ ወርቅ

በገዳሙ ያለው መሶበ ወርቅ ከሰላሳ እስከ አርባ ሣንቲ ሜትር የሚደርስ ርዝመት ያለው በአክርማ ሳር የተሰፋ ጌጠኛ ቁስ ነው። ቁሱ የመሶብ ቅርፅ ያለው ሲሆን በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍል ለቆሎ ማቅረቢያ እና ለሌሎች መሰል ምግቦች ማቅረቢያነት ከሚያገለግለው ቆሎምሻሽ ይመሳሰላል። አገልግሎቱ ገዳማውያኑ ከቀኑ ስምንት ሰዓት አካባቢ ጸሎተ ማዕድ ሊያደርሱ ጸሎተ ማዕድ ተብላ ወደምትጠራው ትንሽ ክብ ባለሁለት ክፍል ጎጆ ቤት ሲገቡ ሕብስቱን ለማቅረቢያነት ይገለገሉበታል።

ጸሎተ ማዕድ ከመጀመሩ በፊት መጋቤው ሕብስቱን በመሶበ ወርቅ ግምጃ አልብሶ ከፀበሉ ጋር በውስጠኛው ክፍል በተዘጋጀለት አውድ (መቀመጫ) ላይ ያስቀምጣል። ወደዚህ ክፍል የሚገቡት ካህናትና መነኮሳት ብቻ ናቸው። ሕብስቱና መጠጡ ወደ ጸሎተማዕዱ ከገባ በኋላ ማንኛውም ሰው ወደ ውስጠኛው ክፍል እንዳይገባና እንዳይወጣ ይከለከላል።

የመሶበ ወርቁን አመጣጥ እና ተምሳሌትነቱን በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች ይሰጣሉ። ከነዚህ መካከል እሸቱ(1987:48) በነገሥት ቀዳማዊ (19፣1-8)ኤልያስ ኤልዛቤል ስትዝትበት ፈርቶ በሸሸ ጊዜ ስንቅ ስላልያዘ ተራብ ተጠማ ዛለ፤ ደከመም አን ቀላፋ። የእግዚአብሔር ሰው በመሆኑ በእግዚአብሔር መልአክ እጅ ተዳሰሰ። ርቦት ነበር እና እንጀራ በመሶብ ውኃ በመንቀል ስለቀረበለት በላ እና ተኛ ። የእግዚአብሔር መልአክ የሚያበረታ ምግብ ይመግበው ዘንድ ዳግመኛ ቀስቅሶ ሲመግበው ሌላ ሐይል ሳያስፈልገው ለሁለተኛ ጊዜ የበላው ምግብ በሰጠው ብርታት ብቻ አርባ መዓልት እና አርባ ሌሊት ተጉዞ ኮሬብ ደረሰ በማለት ከጠቀሰ በኋላ ኤልያስ የአለም፣ መሶብ የድንግል ማርያም፣ ምግብ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች ናቸው፤ ምክንያቱም

የሕይወት እንጀራ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው በመሶብ ከምትመሰለው ድንግል ማርያም ነው በማለት ይመስላሉ።

በሌላ መልኩ በመጻሕፍተ ብሉያት ፪ቱ እሉ እሙንቱ ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደት)ኦሪት ዘፀአት አንድምታ ትርጓሜ ላይ ሙሴ ወንድሙን አሮንን ጠርቶ ወርቁን እንደ ቅጠል አሳስቶ፣ መሶቡን ውስጡን እና ውጪን በወርቅ ለብጦ፤ በውስጧም ዘመን ሳትወስን ጎሞር ሙሉ መና እንዲያኖርበት ማዘዙን፣ አሮንም የሙሴን ቃል ሰምቶ ለልጅ ልጁ ዘመን ይጠብቅላቸው ዘንድ መሶበ ወርቁን ወስዶ በደብተራ ኦሪት ማኖሩን ፤ይኸውም ለጊዜው ቀጣዩ ትውልድ በአባቶቻቸው ላይ እግዚአብሔር ይህን የመሰለ መና ሲመግባችሁ እንዴት ከዳችሁት? ብለው መፈራረጃ እንዲያደርጉባቸው ሲሆን ፍጻሜው ግን መሶበ ወርቅ የድንግል ማርያም ፣ወርቁ የንፅህናዋና የቅድስናዋ ፣መና የወልደ እግዚአብሔር፣ መናውን ብዙ ዘመን ሲኖር ዘመን እንዳለወጠው፣ እግዚአብሔርም ሰው ሲሆን አምላክነቱ ላለመለወጡ ምሳሌ ነው በሚል ተጠቅሷል (1999:103- 104)።

በገዳሙ በመሶበ ወርቅ ቀርቦ የተፀለየበት የፀሎት ማዕድ ምግብ መንፈስ ቅዱስ የሚቀርብበት፣ አጋንንት የሚርቅበት፣ ትንሽ ቢመገቡ ረድኤትና በረከት የሚሆንበትና ድውይ የሚፈውስበት እንደሆነ በገዳማውያኑ ዘንድ ስለሚታመን ለጸሎተ ማዕድ ከሥጋ ወደሙ ቀጥሎ ከሰንበት ቂጣ ከፍ ብሎ ክብር ይሠጡታል። በመሆኑም አስቀድሞ ምግብ የበላ፣ ሠውነቱ የተዳደፈ፣ ዝንብ እና ትንኝ አፉ ውስጥ የገባበት፣ እንቅፋት የመታው፣ የደማ፣ አክታ ያለበት ሰው እንዲበላ አይፈቀድለትም።

### 5.3.3. የገዳሙ የመቅጫ ቁሶች

በፍትሐ ነገሥት በገዳማውያኑ ላይ ክፉ የሚያደርግ፣ በመካከላቸውም ጠብን የሚያነሳ፣ የማይታዘዝ፣ ስራውን ችላ የሚል፣ የአባላቱን ምግብ የሚያባክን፣ በተደጋጋሚ ተመክሮ ከጥፋቱ የማይመለስ እና ሰክሮ የሚገኝ ስለበደሉ ይቅጡት(ፍትሐ ነገሥት፣ 1 990:11)ይላል። እንዲሁም በጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም ገዳማውያን እምነት አባላቱ ጥፋት የሚፈጽሙት የቅዱስ ቂርቆስ ታቦት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት በንጉሡ አማካይነት ወደዚህ ስፍራ መጥቶ በአካባቢው ያለውን አጋንንት ሲያስወጣ አንዱ ቆሪጣ መንቀሳቀስ ስላልቻለ በዚያው ተቀምጦ ማግኘቱን፤ ቂርቆስም

ማንንም እንዳይነካ አስገዝቶ የተወው መሆኑን፤ ጋኔኑ ግን የገባውን ግዝት ትቶ በመነኰሳቱ መካከል ጠብን ሲዘራ፤ ክፉ ሥራም እንዲፈፅሙ ሲያደርግ የሚገኝ ሲሆን ቅጣቱ በአባሉ ላይ የሚጣለው አባሉን ለመጉዳት ታስቦ ሳይሆን በአባሉ ላይ ያደረውን ክፉ መንፈስ (ቆራጣውን ጋኔን) ለማስለቀቅ በማሰብ እንደሆነ ነው። በመሆኑም አባላቱ ሲቀጡ ጉዳዩን ከቆራጠው ጋኔን ጋር ስለሚያገናኙትእና ቅጣቱን ከክፉ መንፈስ ለመንፃት የሚደረግ ጥረት አድርገው ስለሚቆጥሩት ቅጣቱን በወሰነባቸው ማህበረ መነኮሳት ላይ ቂም አይዙም(አባ ባዬ፣ ካሴት ቁጥር 1A፣ ግንቦት 25ቀን 2002)። በገዳሙ አባላቱ አጥፍተው ከተገኙ ከሚቀጡባቸው ሥርዓቶች መካከል እንደ ጥፋቱ ቅለት እና ክብደት በደረጃው በሣር፣ በእንጨት እና በደሴት ላይ ባለች ጎጆ ለብቻው ታስሮ ወይም ተገልሎ እንዲቆይ በማድረግ ነው።

## 5.3. 3.1.በሣር ማሰር

ሣሩ ማንኛውም በአካባቢው የሚገኝ የተነቀለ ወይም የታጨደ ደረቅ ወይም እርጥብ ሊሆን ይችላል። አባሉ የሚታሰርበት ሣር መጠን በቁጥር በጣም ጥቂት ሲሆን አስተሳሰሩ እስራት የተወሰነበት አባል ሁለት እግሩን ለእስራት ያተዘጋጀ በመሰለ መልኩ እግሮቹን አጠጋግቶ እንዲቀመጥ ከተደረገ በኋላ በመጋቢው አማካይነት በተጠጋጉት እግሮቹ ጫማዎች ላይ ሣሩ እንዲቀመጥ ይደረጋል። ታሳሪው የተቀመጠበትን ሣር እንደ ማሰሪያ ቆጥሮና ቅጣቱን አክብሮ መጋቤው በድንገት ወይም መቁትን ሊሰጠው ሲሄድ ታሳሪው እግሩ ላይ የተቀመጠውን ሣር ሳይነካና ከተቀመጠበት ሳይነቃነቅ ከተገኘ የተወሰነበት ቅጣት እንዲቀልለት ሆኖ ሊፈታ ይቻላል።

ሣሩ የምነና ህይወቱ እና ታሳሪው የጠፋው ጥፋት ቀላል ለመሆኑ ተምሳሌት ነው፣ ሣሩ የታጨደ ወይም የተነቀለ መሆኑ ሣር ከታጨደ በኋላ ፍሬ እንደማይሰጥ ሁሉ ገዳማውያኑም ከመነኮሱ በኋላ ዘር የማይተኩእና በአለም ዘንድ የሞቱ ለመሆናቸው፣ ሣር በታሳሪው እግር ጫማ ላይ መቀመጡ ደግሞ ምነና ይሰር ለሚለው ተምሳሌት መሆኑን ፣በሌላ መልኩ ሣር ክብደቱ ቀላል እንደሆነ ሁሉ አባሉ ያጠፋው ጥፋት ቀላል ለመሆኑ ማሳያ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ታሳሪው በጫማው ላይ ያለውን የተነቀለ ወይም የታጨደ ሣር ሲመለከት የእርሱን ሕይወት ከንቱነት ተመልክቶ ወደ መንፈሳዊ

ሕይወቱ እንዲመለስ ያግዘዋል በማለት ይገልፃሉ(አባ ወልደ ገብርኤል፤ካሴት ቁጥር 2B ግንቦት 25 ቀን2002 ዓም፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም)።

### 5.3.3.2. በእንጨት ማሰር

በገዳሙ ለአባላት መቅጫ የሚያገለግለው እንጨት ቁመቱ አንድ ሜትር አካባቢ ሆኖ የተጠረበ ነው። አሠራሩ በባህላዊ መንገድ ከሚዘጋጀው ቀንበር ይመሳሰላል። ከእንጨቱ በግራ እና በቀኝ በኩል ሁለት ሰፋፊ ቀዳዳዎች አሉት። ከገዳማውያኑ መካከል ጥፋት ሰርቶ የሚገኝ አባል በመጋቤው አማካይነት መሬት ላይ እንዲቀመጥ ከተደረገ በኋላ ሁለት አግሮቹ በቀዳዳዎቹ እንዲገቡ ተደርገው ይታሰራል። የቀንበር ማሰሪያው አገልግሎት ወይፈን ለእርሻ ከሚቀናበት ተግባሩ ጋር ያመሳስሉታል። ወይፈኑ ለእርሻ ሥራ ከመሰማራቱ በፊት ባህሪው እንዲገርም በቀንበር እንዲቀና እንደሚደረገው ሁሉ፣ ጥፋት ሲፈፅም የተገኘ ገዳማዊም በመፈሳዊ ሕይወት እንዲገራ በቀንበር እንጨት እንዲቀና ይደረጋል።



ፎቶ ግራፍ 7፦ የእንጨት ማሰሪያ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሣር በክብደት ቀላል ሆኖ ለቀላል ጥፋት መቅጫ እንዳገለገለው ሁሉ በቀንበር መታሰር ደግሞ ጥፋቱ ከፍ ብሎ ለመታየቱ እና ታሳሪው በሣር ቢታሰርም ከክፉ ባህሪው ላለመመለስ መሞከሩን ማሳያ ነው። አባሉ ቅጣቱ ሲወሰንበት በአኮቴት ወይም በደስታ አልቀበልም ካለ ማህበሩ እስር ቤቱ ድረስ ወስዶ ሁለት ቀዳዳ ባለው ቀንበር መሰል ግንድ እግሮቹን አስገብቶ ያስረዋል። ሲታሠርም

ለማንኛውም የማህበሩ አባል የሚሠጠውን ያህል መቁንን አያገኝም። የተነሳበት ያር (የቆራጣው ጋኔን መንፈስ) እስኪወገድ ድረስ ኩርማን መኩሬታው ላይ በርበሬ ተጨምሮበት በሁለት ወይም በሦስት ቀን አንድ ጊዜ እንዲበላ ይሠጠዋል። አባሉ ከታሠረ በኋላ ሁለት ወይም ሦስት ቀን ያህል ታይቶ ርሃቡና ጥሙ ሲፈትነው ወደ ልቡ ተመልሶ ይቅርታ ከጠየቀ መጋቢው ይቅርታውን ለማህበሩ ያቀርብለታል። ማህበሩም አባሉ ከቀድሞ ግብሩ ተመልሷል ብሎ ይፈታዋል ወይም እስራቱን ያቀልለታል።

ሆኖም ማህበሩ ወስዶ በግንድ ካሠረው በኋላ የአመጽ ቃል እየተናገረ ካስቸገረ ቅጣቱ በግንድ ከነበረ ሀብል ተጨምሮበት እንዳይንቀሳቀስ ተደርጎ ይታሠራል ወይም ወደ ቀጣዩ የእስራት ደረጃ ይሸጋገራል።

#### 5.3.3.3. በደሴት ላይ ያለች የማሰሪያ ጎጆ

ደሴቷ ከገዳሙ ግማሽ ኪሎ ሜትር ደቡባዊ አቅጣጫ ትገኛለች። ደሴቷ ጠባብ እና ድንጋያማ ናት። ስፋቷ ቢያንስ ሃያ ካሬ ሜትር አካባቢ ትደርሳለች።በደሴቷ ላይ አንዲት በግምት ሦስት ክንድ የምትደርስ የሳር ጎጆ ትገኛለች። አንድ ገዳማዊ እጅግ ከፍተኛ እና ተደጋጋሚ ጥፋት ከፈጸመ ወይም በእንጨት ማሰሪያው ታስሮ እያለ የትዕቢት ቃል እየተናገረ ካስቸገረ ወደዚያች ከሰው ፍጹም ወደተገለለች ጎጆ ተወስዶ ለረጅም ጊዜ ይታሰራል። መጋቢውም በቀን የሚያስፈልገውን ምግብ እና መጠጥ ከመደበኛው መቁኑን ባነሰና እንደሁኔታው ወጥ ሳይሆን በመኮሬታው ላይ የሚያቃጥል በርበሬ እየጨመረ ይሰጠዋል። ታሳሪው በዚህ ቅጣት ካልተመለሰ ከገዳሙ አባልነት ይሰናበታል።

### 5.4. የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ሥርዓት

ተግባር ቤት የምግብ ማዘጋጃና መቆነኛ ቦታ ነው። በኃላፊነት መጋቢው የሚሠራው ሲሆን በስሩ ጓል መጋቢና ሊቀ አበው ይኖሩታል። ተግባር ቤት እንደ ቤተ እግዚአብሔር ስለሚቆጠር ወደ ቅጥር ግቢው ጫማ ተደርጎ አይገባም፤ ከገቡም በኋላ ከፍ ያለ ድምፅ ማሰማት አይፈቀድም፤ እንግዳ ሰውም አይገባም። ለማህበረ መነኰሳቱ የሚቀርቡት የምግብ አይነቶች መኩሬታ፣ወጥ እና ጭልቃ ናቸው።

### 5.4.1.መኮሬታ

መኮሬታው የሚሠራው ከበቆሎ፣ ከዳጉሣና ከጤፍ ቅልቅል ሲሆን እህሉ ወደጐተራ እንደገባ ሳይለቀም ወይም ሳይበጠር በዘመናዊ ወፍጮ ይፈጫል፤ ተቦክቶ ሶስት ወይም አራት ቀን ከቆየ በኋላ ተዘጋጅቶ ከተቦካው ቡሆ መካከል በመጠኑ ተጨልፎ በፈላ ውሃ ውስጥ እንዲጨመር ይደረጋል፤ በትልቅ ማመሰያ እንጨትም ይማሰላል። ቡሆው ከወፈረ በኋላ በጎላው ወደ ተዘጋጀው ቡሆ ተጨምሮ እስከሚዋሃድ ድረስ ይማሰላል፤ ይህንንም አብሲት መጣል በማለት ይጠሩታል። ከዚያም ለሦስት ቀናት ያህል ከቆየ በኋላ ይጋገራል። የሚጋግረውም በወንድ ጓል መጋቢ ነው።



ፎቶ ግራፍ 8፦ መኮሬታ

### 5.4.2.ወጥ

ወጡ ደግሞ ከጓያ ሽሮ የሚዘጋጅ ሲሆን ራሱን የቻለ ጓል መጋቢ አለው። ወጡ ሲሰራ በቅድሚያ በፈላው ውሃ ላይ በርበሬ ከተነሰነሰ በኋላ ትንሽ እንደቆየ ሽሮው ተበጥብጦ ወደ ድስቱ (ጐላው) ይገባል፤ ሽሮውም ከፈላ በኋላ ጨው ተደርጐበት ይወጣል። ወጡ ቀጭን ሆኖ የሚሠራ ሲሆን ዘይት ወይም ሽንኩርት አይጨመርበትም። እስኪበስልም አይቆይም። የዚህ ምክንያቱ ሥጋን እንዳይደላው ሲባል እንደሆነ መነኰሳቱ ይናገራሉ።

5.4.3.ጭልቃ

ማህበረ መነኮሳቱ በዋናነት ለመጠጥነት የሚጠቀሙት ከጣና ሐይቅ የሚቀዳውን ውሃ ሲሆን ከሌላ ቦታ የመጣ ውሃ አይጠጡም፤ ይኸውም ጣና አስቀድሞ በኢየሱስ ክርስቶስ በኋላም በአባ ሰላማ ተባርኮ እንደ ዮርዳኖስ ባህር ሆኗል፤ ስለሆነም ለሚጠጣው ሰው ድህነተ ነፍስ ድህነት ሥጋ ያስገኛል ብለው ስለሚያምኑ ነው። ዕለቱ የሥራ ቀን በሚሆንበት ጊዜ ግን ከሱፍ የተዘጋጀ ጭልቃ የሚባል መጠጥ ይዘጋጃል። አዘገጃጀቱም ሱፉብፈላ ውሃ ከተቀቀለ በኋላ በሙቀጫ ይወቀጣል፤ከላመ በኋላ ውሃ እየተጨመረበት በወንጠፍት(መንፌት ይመስላል) እንዲንጣለል ተደርጎ ለገዳማውያኑ በፋጋ ይታደላል።

ማህበረ መነኮሳቱ ምግብ የሚመገቡት በቀን አንድ ጊዜ ከ9፡30 እስከ 10፡00 ሰዓት ድረስ ነው። ይኸውም የጸሎተማዕድ ሥርዓት ደርሶ ከተጠናቀቀ በኋላ መጋቢው የአባላቱን መቁንን በየፋጋቸው አድርጎ ከቤተ እግዚአብሔሩ የእህል ማስቀመጫ በር በቀኝ በኩል ከግድግዳው ጋር ተያይዞ በተሠራ የእንጨት መደርደርያ ላይ ያስቀምጣል። ከዚያም በኋላ በየበዓታቸው ያሉትን ደካሞች፣ በሥራ ላይ ያሉትን አገልጋዮችና በጸሎተ ማዕድ ላይ በጸሎት የቆዩትን አባቶች መቁንኑ ደርሷልና ውሰዱ በማለት መጋቢው ደወል ይደውላል። አባላቱም ደወሉን እንደሰሙ ቤተ እግዚአብሔር ድረስ መጥተው እንደ የአቅማቸው ይቆነናሉ። አንዱ አባል በሥራው ወይም በድካም ምክንያት ቢቀር ሌላኛው ተቆንኖ ሊወስድለት ይችላል።

## ማጠቃለያ

በጣና ቂርቆስ የአባቶችና የእናቶች የአንድነት ገዳም ከአመሰራረቱ ጋር ተያይዞ ልዩ ልዩ ተረኮች ይነገራሉ፤ ቁሳዊ ባህሎችም ይቀርባሉ። ተረኮቹ የገዳሙን አመሰራረት ወይም ታሪክ ለመንገር ሲፈለግ በጊዜ ቅደም ተከተል የሚቀርቡ ናቸው፤ ከቁሳዊ ባህሎቹም አንዳንዶቹ የተረኮቹን እውነታነት ለማረጋገጥ በማስረጃነት የሚቀርቡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በገዳማውያኑ የዕለት ከዕለት ሕይወት ጋር የተያያዙና የአምልኮ ስርዓት መፈፀሚያ ናቸው።

ተልዕኳቸውም ተረኮቹ የገዳሙን ጥንታዊነት ወይም ቀዳሚነት ለማሳየት ያገለግላሉ። የገዳሙን ቅድስና ወይም ክብር ከፍ ለማድረግም በቤተክርስቲያኗ በዋናነት የሚታወቁትን ቅዱሳንና የአምልኮ መፈጸሚያ ቁሶች በቦታው እንደነበሩ አድርጎ ማቅረብ ነው።

ዋኖቹ በቦታው ለመኖራቸውም ከዋኖቹ ጋር ተያያዥነት አላቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን ቁሳዊ ባህሎች በማስረጃነት በማቅረብና በዋኖቹ አማካይነት በስፍራው ተፈጸሙ የተባሉ ተአምራትን ወይም ተግባራትን በመንገር ለማስረዳት ይሞክራሉ።

ሌላው በተረኮቹ ውስጥ የዋኖቹ ተግባር ተጠቅሷል። በዋናነትም ዋኖቹ እንደ ስልጣን ተዋረዳቸው አንዱ ለአንዱ መታዘዝ፣ ስለቦታው ቅድስና እንዲናገሩ ማድረግ፣ የገዳሙን መተዳደሪያ ስርዓት በእነርሱ እንደተበጀ መንገር፣ ዋኖቹ ገዳሙን በተደጋጋሚ እንዲጎበኙት ማድረግ፣ ከእነርሱ በታች ላሉት ጥበቃና ድጋፍ ሲያደርጉላቸው ማሳየት እና ዋኖች ፈጸሙት ተብሎ በሚነገር ገድል ስፍራውን ማስከበር ናቸው።

ቁሳዊ ባህሎቹ የኦሪት መስዋዕት ማቅረቢያ፣ ከስርዓተ አምልኮ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና ገዳማውያኑ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው የሚጠቀሙባቸው ሲሆኑ የኦሪት መስዋዕት ማቅረቢያዎቹ የገዳሙን (የስፍራውን) ጥንታዊነትና ክብር ለማሳየት፣ ከአምልኮ ስርዓት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁሶችም ገዳማውያኑን በባታቸው አጽንቶ ለማቆየት፣ ገዳማውያኑ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው የሚጠቀሙባቸው ደግሞ በዋናነት

የገዳሙን ስርዓት ለማስጠበቅ ያገለግላሉ። ከዚህም ባሻገር ሁሉም ቁሶች ባላቸው ተምሳሌታዊ ትርጉም ከአምልኮ ስርዓት ጋር የተሳሰረ ትርጉም አላቸው።

በአጠቃላይ በገዳሙ የሚነገሩ ተረኮችና የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች ገዳሙ ክብሩንና ሕልውናውን ጠብቆ እንዲዘልቅና ገዳማውያኑ በስፍራው ፀንተው እንዲኖሩ በማድረግ በኩል የየራሳቸውን ድርሻ ያበረክታሉ።

## ዋቢ ጽሑፎች


ሀብተ ማርያም አሰፋ። የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎች እና ባሕሎች። አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቤቱ አልተጠቀሰም) 1986።

ሐረገ ወይን አገዘ እና እሸቱ ታደሰ ። ነገረ ማርያም። አዲስአበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣1996 ።

መልአኩ አስማማው። ሀብታችን እና ሥርዓቱ ። አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፣ 1993 ።

ምኒልክ መርዕድ። መጽሐፍ ቅዱስ እና ኢትዮጵያ። አዲስ አበባ፣ ኢሜጅ ማተሚያ ቤት፣ 1999።

ማህበረ ቅዱሳን። ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣16ኛ ዓመት፣ ቁ.6። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፐራይዝ፣ 1991።

ምክረሥላሴ ገብረአማኑኤል። የእግዚአብሔር መንግስት ታሪክ በምድር ላይ (ጠቅላላ የቤተክርስቲያንታሪክ) አንደኛ መጽሐፍ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 2000።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግ። አዲስ አበባ፣ ብርሃን ና ሠላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት፣ 1951።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ። ተአምረ ማርያም (ግዕዝና አማርኛ)። አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ማተሚያ ቤት፣ 1998።

ታደሰ አይችሉህም። "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ስርዓት እና የገዳማዊያኑ የዕለት ከዕለት ሕይወት ከትምህርታዊነቱ አንፃር፡ በዝቋላ አቡነ በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ኃይማኖት እና ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳማት"። ኤምኤ ቲስስ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍ ል፣ 1999።

ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት። ፍትሐ ነገሥት ንባቡ እና ትርጓሜው። አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣ 1990።

____________________። መጻሕፍተ ብሉያት ፬ቱ እሉ እሙንቱ ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደት) ኦሪት ዘጸአት አንድምታ ትርጓሜ። አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ 1999።

አማከለ ገበየሁ። ቅድስት አገር። ማተሚያ ቤቱ አልተጠቀሰም፣ 1992።

አባይነህ ካሤ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (አንደኛ መጽሐፍ)። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት፣ 1992።

እሸቱ ወንድም አገኘሁ እና ደጀኔ ሽፈራው። ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ። አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣1979።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948።

ካህሳይ ገብረ እግዚአብሔር። ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛሬ እና ትናንትና። አዲስ አበባ፣ (ማተሚያቤቱ አልተጠቀሰም)፣ 2000።

ክንፈ ገብርኤል አልታዬ እና ጌታቸው። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን። አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 2002።

ጋስፓሪኒ። የኢትዮጵያ ታሪክ። አሥመራ፣ ማተሚያ ቤቱ አልተጠቀሰም፣ 1948።

ጌታቸው ተስፋዬ (ተር)። ታቦተ ፅዮንን ፍለጋ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1993።

ደስታ ተክለወልድ። ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1962።

ዳንኤል ክብረት። የቤተክርስቲያን መረጃዎች። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣1999።

ዘመድኩን በቀለ። ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1992።

የአማራ ብሔራዊ ክልል ባሕል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ። የአማራ ክልል የቱሪስት መስሕብ ሐብቶች/ አጭር ቅኝት/፣ 1991።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። መጽሐፍ ቅዱስ ፡የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍት። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት፣ 1962።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገብ ቃላት። አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 1992።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። ክብረ ነገሥት ግዕዝና አማርኛ። አዲስ አበባ፣ 1994።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን።ድርሳነ ዑራኤል በግዕዝና በአማርኛ። አዲሰ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1991።

ብርሃኑና ሌሎቹም። የኢ.ትዮ.ጵ.ያኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትናንት እና ዛሬ። አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣ 1997።

የክልል ሦስት ቱሪዝም ቢሮ። ክልል ሦስት ሲጎበኝ። አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1996።

ወርቁ ከተማ። "የሊሙና ቢል ቢሎ ወረዳ፣ የጨፋ መድሃኔ ዓለም፣ ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም አመሠራረት ፎክሎራዊ ገጽታ"። ኤምኤ ቲስስ፣ በኢ.ትዮ.ጵ.ያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 2000።

ጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም። የጣና ቂርቆስ ታሪካዊ እና ጥንታዊ የአባቶች እና የእናቶች ገዳም። ባህርዳር። ቅ.ገብርኤል ማተሚያ ቤት፣ 1992።

ፈቃደ አዘዘ። የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመጻሕፍት ማዕከል፣ 1991።

ፍሬሕይወት ባዩ ። "በኢ.ትዮ.ጵ.ያኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገፅታ"። ኤም ኤ ቲስስ፣ በኢ.ትዮ.ጵ.ያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 2000።

Aymro Wondmagegnew and Joachim Motovu. The Ethiopian Orthodox Church Mission. Addis Ababa, Berhanna Selam H.S.I. Printing Press. 1970.

Ames,L,Kenneth,«Meaning in Artifacts:Hall Furnishings in Victorian Americans,»In Journal of Interdisciplinary History;Vo1.Ix; No. 1, 1978.

Bascom, William. «Four Functions of Folklore». In Dundes, A. (Ed.) the Study Folklore. Englewood Cliffs, N.J: Prentice-Hall, Inc, 1965.

Sims, Martha C. &Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions. London, Logan, Utah: Utah State University Press, 2005.

Daniel Hailu. «Founders of Ethiopian Monasticism. » Unpublished B.A Thesis, Holy Trinty Theology College, 1999.

Gebre Sellase Mersha. "A brief History of Martula- Maryam Monstery since 14th century focusing on its educational developmental

activities.» unpublished B.A Thesis, Holy Trinty Theology College, 2006.

Getu Ambaye. "A Short History of the Monastery of Walata Petros (1901_1974)."Unpublished B.A Thesis, Unpublished Addis Ababa University, 1999.

Getnet Fetene. "Lake Tana and its Tourism Potentials." Unpublished Amhara National Regional State Culture and Tourism Bureau, 2005.

Habtamu Mengistie. "A History of the Monastery of Martulamariam Cc.1500 1974). Unpublished B.A Thesis, Addis Ababa University, 1998.

Hagos Gebremariam. "Monastic Life in the Ethiopian Orthodox Church." Unpublished B.A Thesis, Holy Trinty Trinity Theology College, 1964.

Hailemariam Asefa. "The Addis Ababa Genete Eyasus Monastery." Unpublished B.A Thesis, Addis Ababa University, 1991.

Haile Michael Welde Tekele Hymanot". A brief History of Debrahayk Sanit Stephen Abuna Iyasus Moa communal Monastery in South Wollo." Unpublished BA thesis, Trinity theology college 2005.

Hastings, James. <u>Encyclopedia of religion and Ethics (Volume VIII)</u> Scotland.1994

Jones, Michael Own. (Ed). <u>Putting Folklore to Use</u>. Unknown Town, the University of Press of Kentucky, 1994.

Leikungifa Wosen. "History of Abuna Habtemariam and his Monastery." Unpublished B.A Thesis, Holy Trinity Theology College 2006.

Degh, Linda. «Oral Folklore: Oral Narratives. » In <u>Folklore and Folk life</u>: <u>An Introduction</u>. Richard M. Dorson [Ed.]. Chicago and London: The University of Chicago Press,

1972.

Mengistu Kebede. "The Role of Debre Libanos Monastery in the Ethiopian Orthodox Tewaido church." Unpublished B.A Thesis, Holy Trinity Theology collage, 1999.

Meraw Enchalew. "A Brief History of Mahibere Silassie Monastery." Unpublishd. B.A Thesis, Holy Trinity Theology College, 2000.

Mezgebu Kassa. "Monastic Life in the Ethiopian Orthodox church." Unpublished B.A Thesis, Holy Trinity Theology Collage, 2001.

Michael Gebru. "Monastic in Life in the Ethiopian Orthodox church." Unpublished B.A thesis Holy Trinity Theology collage, 2002.

Oring, Elliot. Folk Genres and Folklore Genres: An Introduction.Utah State University Press, Loganutah, 1986.

Prown, J.David. "Mind in matter: An Introduction to Material Culture Theory and Methd"; on line. Available at: http:/www.Joster. org/about/terms.htm1/

Ritezer, George. Sociological Theory. Singapore.2000.

Sergew Hable Selasie. The Church of Ethiopia: apanarama of History and Spiritual Life. Addis Ababa.1970.

Schlerth, T.J. (1980). "Artifacts and the American Past." American Association for State and Local History; Nashville, TN.P.

Sileshe Mengste. "AHistory of Dima Giyorgis Monastery from foundation to 1974." Unpublished B.A Thesis, Addis Ababa University, 1998

Solomon G/Meskel. "The Brief History of Entoto Hamere Noha Kidane Mihret Monastery of Addis Ababa." UN published B.A thesis, Holy Trinty Theology College, 2007.

Tadese Tamirat. Church and State in Ethiopia :12701527. Great Britain: Oxford University Press, 1972.

Tegbaru Adane. "A Brief History of Dima Giyorgis Monastery." Un published B.A Thesis, Holy Trinity Theology College, 2002.

Tigab Bezie."The Ethiopian Claim on the Monastery Deir Es-Sultan in Jerusalem:1850 1994."Unpublished M.A Thesis, Addis Ababa University, 2002.

Vansina, Jan. "Oral Tradition as History." The University of Wisconsin Press, London, 1985.

Zlalem Assefa. "A brief History and activities of Zeway Debere Tsion Monastery." Unpublished BA Thesis, Holy trinity Theolgy College, 2001.

Zelalm Nigussie. "A brief History of Zuramba Aregawi Monastery." Unpublished B.A thesis, Trinity Theology College, 2002.

## አባሪዎች

### አባሪ አንድ

### ተረክ አንድ

የንግስተ ሳባ (ንግስት ማክዳ) አባት በሞት ሲለይ አልጋ ወራሽ የሚሆን ወንድ ልጅ አልነበረውም። ብቸኛዋ ልጅ ማክዳ ነበረች። አባቷ እንደሞቱ በዙፋኑ ዙሪያ ለነበሩ መኳንንቶች ንግስናውን እንዲሰጧት ጠየቀች። መኳንንቱም የአባቷን በትረ ስልጣን ለመያዝ አስቀድማ ግዳይ መጣል እንደሚኖርባት ነገሯት። እርሷም ሕዝቡ ያመልከውና የበኩር ልጅ ይገብርለት የነበረውን ዘንዶ ገድላ ለማሳየት ፈለገች። ዘንዶውን በቀጥታ በጦር ወግታ መግደል ድፍረት በማጣቷ አስቀድማ በእሳት አቃጠለችው፤ በኋላም ለመኳንንቱ ግዳይዋን በጦር ወግታ ለማሳየት ስትሞክር ደሙ ተፈንጥቆ ተረከዟ ላይ ነካት። በተረከዟም ላይ እንደ ፍየል ቀንድ የዞረ የአህያ ሸኮና መሳይ ነገር ወጣባት።

ንግስት ማክዳ ግዳይዋን ለመኳንንቱ በማሳየት የአባቷን የንግስና መንበር ይዛ ሕዝቡን በማስተዳደር ላይ እያለች በኢትዮጵያዊው ነጋዴ በታምሪን አማካይነት ስለኢየሩሳሌሙ ንጉሥ ሰሎሞን ጥበብ ሰማች። ሂዳም ጥበቡን ለመቅዳት ልቧ ተነሳሳ። በሂደትም በብዙ ሠራዊቷ ታጅባ አስቸጋሪውን የኢየሩሳሌም ጉዞ ጀመረች። ከንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መንግስት ደርሳ በሩን ተሻግራ ልትገባ ስትል በር ላይ የተጋደመው ግንድ ተረከዟን ቢነካው ሸኮናው ወለቀላት። እግሯም እንደቀድሞው ሆነ።

በንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መንግስትም ታላቅ አቀባበል ተደረገላት። በቆየችባቸውም ጊዜያት የቤተመንግስቱን ወግና ሥርዓት፣ የሃይማኖቱን መሠረትና ሕግጋት አጠናች። በአንድ ወቅት ስለ ሀገሯ ወግና ልማድ ስትናገር በግዛቷ ሥርቆትና ዝሙት እንደማይታወቅ ነገረችው። አንድ ዕለትም በነገረችው ነገር ሊፈትናት አሰበ። ይኸውም ንጉሡ ለንግሥቲቱ ውሃ የሚያስጠማ ምግብ ጋብዞ ውሃ ሳይሰጥ በቤተ መንግሥቱ የእንግዳ ማረፊያ ክፍል አስተኛት። ንግሥቲቱም ትንሽ እንደቆየች ውሃ ጥሙ በረታባት። እንቅልፍም ሊወስዳት አልቻለም።

ከዚያም እንቅልፍ እንደወሰደው ከአረጋገጠች በኋላ ከመኝታ ቤቱ ገብታ ውሃ ለመጠጣት ወሰነች። ሆኖም ሰሎሞን ሲያንቀላፋ አይኑን ገልጦ፣ ሲነቃ ደግሞ አይኑን ከድኖ የመተኛት ጠባይ እንዳለው አታውቅም ነበር። ወደ ንጉሱም መኝታ ቤት ገብታ ማንቀላፋትና አለማንቀላፋቱን ለማረጋገጥ ስትሞክር አይኑን ከድኖ አየችው። የአንቀላፋ መስሏት ውሃ ቀድታ ስትጠጣ ንጉሡ ድንገት ያዛትና 'በሀገራችሁ ስርቆት የለም አላልሽኝም?' ብሎ እዚያ ይዞ በግብር አወቃት።

በዚያም ሌሊት ንጉሥ ሰሎሞን ተኝቶ እያለ ታላቅ ሕልም አየ። ሕልሙም ፀሐይ ከሰማይ ወርዳ በኢስራኤል ምድር ላይ ስታበራ ታየው። ከትንሽ ጊዜ በኋላም ወደ ኢትዮጵያ በረረች። በኢትዮጵያም ከበፊቱ ይበልጥ አበራች። ወደ ኢስራኤል ትመለሳለች ብሎ ቢጠብቅም ለዘላለሙ ሳትመለስ ቀረች።

ንግሥቲቱም ወደ ግዛቷ ስትመለስ ቀስተ ደመና ሲከተላት የኢስራኤል ሕዝብ ሁሉ ተመለከተ። ንጉሥ ሰሎሞንም ከእኔ ዘርን ብታገኚ ምልክት ይሁንሽ ብሎ የትንሽ ጣቱን ቀለበት አውልቆ ሰጣት።

በጉዞም ላይ እያለች ለንጉሥ ሰሎሞንና ለእርሷም የበኩል የሆነውን ምኒልክን ወለደች። ምኒልክም ሃያ ሁለት ዓመት ሲሞላው ወደ አባቱ አገር ሄደ። ከንግሥት ሳባ የተወለደው ቀዳማዊ ምኒልክ አባቱን ለመጠየቅ ወደ ኢየሩሳለም ሄዶ በ አባቱ ቤተመንግሥት እየኖረ እያለ ከአባቱ ጋር ስለሚመሳሰል ንፋስ ለመቀበል፣ ተናፍሶ ለመመለስ እና አገር ጎብኝቶ ይወጣ ይገባ ጀመር። ሲወጣ ሕዝቡ እየተነሳ መስገድ እና መረበሽ ጀመረ። «ለምንድነው የምትረበሹ?» ሲሏቸው «ይህ ንጉሥ ሰሎሞን አይደል?» ይሏቸዋል። ሰዎቹም «ምን ሰሎሞን ነው! ከኢትዮጵያ የመጣው የበኸር ልጅ ነው እንጂ።» «እንዴት እንግዲያ እርሱን መስሎን ምን ያህል ነገር ነው» እያሉ ሲሉ አሁንም ይህ ነገር ዝም ብሎ ሰው ሲያዩ ንጉሥ ሰሎሞን መጣ እያለ መውደቅ መነሳት ሆነ። «አይ ይህ ነገር እንደዚህ ብለን ለሁለት ንጉሥ አንገዛም። እንንገረው እና በእናቱ አገር ይሂድ። ከዚያ አንግሦ ይስደድ እንጂ እኛ ለሁለት ንጉሥ ተገዝተን አንኖርም» ብለው ምክር ሲያቀርቡ ከዚያ በኋላ ምክሩ ተመከረ። ሁሉ ነገር አበቃ።

ከዚያ በኋላ «በል ንጉሥ እኛ ለሁለት ንጉሥ ተገዝተን መኖር አንችልም ፤ይህ ልጅህ በገባ በወጣ ቁጥር ሕዝቡ እየተረበሸ ነው። መልኩ አንተን ነው የሚመስለው። እናም በናቱ አገር አንግስልን» ብለው መኳንንቱ ነገሩት።

ንጉሡም «አይ ይህ ልጄ የበኸር ልጄ ነው አሁንም ወዲያ አባረህ የበኸር ልጅህን በእናቱ አገር ይንገስ ካላችሁ የበኸር ልጄ ነው ብቻውን አልሰድም።እናንተም የበኸር የበኸር ልጆቻችሁን ስጡ አለና በፈረዳችሁት እኔ እፈርዳለሁ። ልጄ በሰው አገር ይቅር ካላችሁ እናንተም ልጆቻችሁን ስጡ» አለ። ከዚያ በኋላ ፍቃደ እግዚአብሔር ነውና «እሽ» አሉ። ከዚያ በኋላ አስራ ሁለቱ ነገደ ኢስራኤል ልጅ ልጃቸውን ሲያወጡ ጠቅላላ ሃይማኖት ያለውም ሆነ የሌለው አናጢ የለ ግንበኛ የለ ብረት ቀጥቃጭ የለ አዝማሪ ዘዋሪ ሁሉ የሊቀ ካህናቱ የአዛሪያስ ልጅ ሳዶቅ ወጣበት።

ከዚያ በኋላ ምኒልክ «አባቴ ወደ እናቴ አገር ስሄድ በእናንተ በኢየሩሳሌም ማምለኪያ ታቦተ ፅዮን የምትባል አለች፤ እኛ ግን ዝም ብለን እግዚአብሄርን እያመለክን እንኖራለን እንጂ እንደዚህ የተለየ መስገጃ ክብረ በዓል የምናከብረው ታቦት የሚባል ፅላት የሚባል የለንም። ለምን አትሰጠኝም ይችን ይገዬ አልሄድም?» «ይችማ ሃይል ሆናን ለህገሪቱ ግርማ ሆና የኖረች ናትና ይችንማ አልሰጥህም።» «እንዴት ያላአንድ ነገር እሄዳለሁ?» ሲለው «መጽሐፍት አሉ የኦሪት፣ የነቢያት መጻሕፍት እርሱን አስጽፌ እሰጥሃሉ እንጂ ሌላስ አልሰጥህም አለው።» አባቱ እምቢ እንዳለው ሲያውቅ የካህኑን እና የመኳንንቱን ልጆች ሰብስቦ «ይህችን ፅዮን የምትባለውን መውሰድ አንችልም?» አላቸው።

የመኳንንቱ ልጆችም «እርሷማ አትነሳልንም መውሰድ አንችልም» አሉት። ከዚያም እርሱ «እንግዲያስ እንዴት እናድርግ?» ሲላቸው «መውሰድ የሚቻለው እነደዚያች አስመስለህ አሰቀርፀህ እርሱን ተክተህ ነው እንጂ መውሰድ አትችልም» ።ሊቀካህናቱ በቀን በቀን ይዳስሳታል። ከዚያም በካህናቱ አስቀርፆ ትክ በማድረግ በሊቀ ካህናቱ የበኸር ልጅ ሰሎሞን የፈቀደላቸውን መጽሀፍ የሚወስድ መስሎ ታቦተፅዮንን ሰርቆ ወሰደ።

ትንሽ እንደተጓዙ ምድር ተንቀጠቀጠች ሰሎሞንም «ያልጅ ታቦተ ፅዮንን ወስዷት ይሆን! እስኪ ሊቀካህናቱ ዳሳት» ብሎ አዘዘው። ከዚያ በኋላ ሄዶ ቢዳስስ ሌላ የተቀባባ እና የተጠረበ እንጂ ታቦተፅዮን የለችም። ከዚያም የታቦተ ፅዮን ወደ ኢትዮጵያ መግባት ፈቃደ እግዚአብሄር ስለነበር ሊመልሷት ከመሄድ ይልቅ ተሰባስበው ማልቀስ ጀመሩ።ሊቀ ካህኑም «እንመልሳታለን» ብሎ ሲናገር ሰሎሞን «አዬ ሊቀካህናት ምን እነግርሃለሁ ያች ሴት በመጣች ጊዜ ቀስተ ዳመና ሲከተላት አይቻለሁ። ሊሊትም ተኝቼ ፀሐይ ወደ ኢትዮጵያ አገር ሄዳ በዚያው አብርታ ስትቀር አይቻታለሁ። ስለዚህ አትመለስም።»

እነ ምኒልክም ታቦተ ፅዮንን ይዘው ሲመጡ የአባይን ወንዝ ተከትለው መጡ። ከዚያም «አይ ሰሎሞን ይህችን የመሰለች ሃይል የምትሆን እመቤት መጥታበት ዝም አይልም። ሰው ከማይደርስባት ለሰራዊት ወይም ለጦርነት ከማይመች ቦታ ማስቀምጥ አለብን» እያሉ እየዞሩ ሲፈልጉ፣ ምን ይሁን ብለው ምክር ሲመክሩ መርከብ የሌለበት ደሴት ያለበት ቦታ ፈልጉ ሲባል ይህች ደሴት ተገኘች። በወቅቱ ፎገራ ባህር ነበር።ፎገራ ተራራ ላይ ያለው አገር ታንኳ ፅዮን ይባላል።

ከዚያ በኋላ ከዚህ ደሴት መጡ። ምንም ዛፍ አልነበረውም፤ ድንጋዩን ብቻ አገኙ። የእግዚአብሄር ፈቃድ እንደሆነ አወቁ። በዚህም ድንኳን ጠለው ተቀመጡ። ከዚህ ዛሬ የኦሪት መስዋዕት ድንጋይ ካለበት ድንጋዩን ጠርበው ታቦተ ፅዮንን ከዚያ ላይ አስቀምጠው፣ ዙሪያውን ድንኳን ተክለው እየሰዉ ሲኖሩ፣ ምኩራብ ሰርተው እያለ ደሴቷ የመጣውን ሰው ሁሉ መያዝ ስላልቻለች ከዚህ የተወሰነ ሊቀካህናት ይቅርና የተቀረው ወደ ቤተ መንግስቱ ይግባ ተባለ።

ከዚያ በኋላ ፅላት የሙሴን ፅላት አስመስለው መቅረፅ ጀመሩ። ሦስት ቀረፁ ይባላል። ተድባበ ማርያምን፣ መርጡለ ማርያምንና አክሱም ፅዮንን ቀርፀዋል። በዚህ ቦታ 8መቶ 88 ዓመት በኦሪት ተሰዉቶበታል። ሊቀ ካህኑ ሳዶቅ ይባላል። በዚህ ቦታ የሳዶቅ መቃብር አለ። ይህ የኦሪት እና የነቢያት ገዳም ነው። በኦሪቱም ሴት አይገባበትም።ሊዋውያን 46ቱን መጻሕፍት እየተማሩ ለክህነት የበቁበት በዚህ ገዳም ነው። ቀዳማዊ ምኒልክ ከነገሠ በኋላ ለአምኖን ልጅ ለሴት ሱዳንን፣ ለጋፋት ጅቡቲን፣ ለእርሱ ደግሞ መካከለኛውን ክፍል ወስዷል ይባላል።

ምንጭ፣ (አባ ባዬ ፍስሐ፣ካሴት ቁጥር1A፣ ግንቦት 25 ቀን2002፣ ጣናቂርቆስ ገዳም ፤መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር3-4፣ ግንቦት 26 ቀን 2002፣ ጣናቂርቆስ ገዳም)

## ተረክ ሁለት

ሄሮድስ በእስራኤል በነገሠበት ዘመን ሕፃኑን እገላለሁ ብሎ ባሰበ ጊዜ መልአከ እግዚአብሐር ተነስቶ ለዮሴፍ «እናቱንና ሕፃኑን ይዘህ ተሰደድ» ባለው መሰረት ወደ ግብፅ ወርዷል። በግብፅ አገር ሁለት አመት ከኖረ በኋላ ወደዚህ ደሴት ከመግባታቸው በፊት ሀሙሲት አካባቢ ምዕራፌት ማርያም በምትባል ቦታ አርፈው ከዚያ በኋላ ወደዚህ ለመግባት ሲያስቡ፣ ያው ይህ ቦታ በጊዜው ይጎበኛል። የታቦተ ፅዮን ቦታ ስለሆነ ቦታው ይጎበኝ ነበር። ደሴቱ አስደናቂ ስለሆነ፣ አምልኮተ እግዚአብሔር ስለሚፈጸምበት ይጎበኛል።

ከደሴቱ አስተዳዳሪ የነበሩት ሰዎች ታዘው በአካባቢው የነበረውንም እህልም ለማምጣት፣ ማገዶ እንጨትም ለማምጣት የሚጎበኘውንም ሰው ለማስጎብኘት ሲሉ፣ ያው እመቤታችን፣ ሰሎሜና ዮሴፍ ተጠጉና አነጋገሩአቸው። «ምንድናችሁ አሏቸው?» እነሱም «አይ ደሴት ለመጎብኘት እኛ የመጣነው ከኢየሩሳሌም ነው።» «ታዲያ ገንዘብ አላችሁ?» «ኧረ የለንም!» «ኧረ እንውሰዳቸው! አስተዳዳሪው እኮ የኢየሩሳሌም ሰው ነው»አሏቸው። ከዚያ እንግዲህ ከኦሪት ጀምሮ የሚመራቸው የራሳቸው አይደል! አስተዳዳሪውም ያገራችሁ ሰው። «አይ እንውሰዳቸው የአገሩን ሰው ስንወስድለት ደስ ብሎት በጣም ያከብረናል» ብለው ወሰዱአቸው።

ታደያ አስተዳዳሪው ልጁ ታሞበት ከባህር ቆሞ ሲፀልይ መልአኩ ኡራኤል ተገለፀና «ዛሬ ሰማይ እና ምድር የፈጠረ አምላክ በሴት ልጅ ጀርባ ታዝሎ ወደ አንተ ይመጣልና አክብረህ እነዚያን ሰዎች ተቀበላቸው» ብሎ ኡራኤል ነገረው። ከዚያ በኋላ ገብተው አስተዳዳሪው ጋር አገናኟቸው። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ «አይ ከዚያ ሕጻናትን እንደ ጎመን ቅጠል እየቀረደደ ከሚበላ ከሄሮድስ አምልጣችሁ የመጣችሁ የኢየሩሳሌም ሰዎች እናንተ ናችሁ?» አላቸው። ዮሴፍም «እግዚአብሄር በጥበቡ ነው ያመጣን የመጣነው ከኢየሩሳሌም ነው ይህችን ደሴት ለመጎብኘት፣ የእግዚአብሔርንም ጥበብ ለማድነቅ ነው» አለው። በዚህን ጊዜ እመቤታችን ደንግጣ እንደ ትኩስ አስከሬን ሬሳ ሆነች

ይላል። ምክንያቱም የሄሮድስ ሰራዊት በየት አልፎ አገኙኝ ብላ። ከዚያ መደንገዒን ሲመለከት «እመቤቴ ሆይ አትደንግጭ ዛሬ መምጣትሽን አገራችሁም ከዚያ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው እንጂ ዛሬ ወደዚህ ቦታ እንድትገቡ በሌሊት መዝሙረ ዳዊትን ቆሜ ስፀልይ'አቤቱ የሃያላን አምላክ ሀይልህን አንሳ አድነን' ማለት ይህ ሲተረጎም ልጅህን ሰደህ ከዚህ አለም መከራ አድነን ማለት ነው። እናም ይህንን ስፀልይ ሀይልህን አንሳ ስል አይ ሃይሉን የሚያነሳ የሰማይ እና የምድር ንጉሥ ተወልዶ መጥቶልሃልና አክብረህ ተቀበለው» ብሎ ነግሮኛልና አትደንግጭ አለ። ከዚያ በኋላ በሉ ኅብኙ ተብሎ ተፈቀደላቸው። ተራራውን ሲመለከቱ እመቤታችን የቆመችበት በተአምራት እርጥብ ጭቃ እንደተረገጡት ጫማዋ እየተቀረፀ፣ አሁን አሁን እርግጫው እየበረታ ጠፍቶ ነው እንጂ የመላዕከት ክንፍ ተለጥፎ ከድንጋዩ ላይ ይገኝ ነበር፤ ዛሬ ዘመኑ በዝቶ እና ሰው ሁሉም ስለሚረግጠው ጠፋ እንጂ እኛ ደርሰን እንኳ ስንት እርግጫ ነበር። ድሮ አምስት እምስት እጣቷ ከጭቃ የወጣ ይመስል ነበር። እኔ ዛሬ በጣም አዝናለሁ።

ከዚያ በኋላ ቤት ተሰጣቸው ከዚያ አረፉ። ሲያርፉ እንግዲህ ከዚህ ዘጠኝ ቤተ መቅደስ የተሰወረ አለ። በዚያ በድንጋዩ ውስጥ። ቤተ መቅደሱ ተከፈተና እመቤታችን ገባች። «ምንድናችሁ?» አለቻቸው። አይ እኛ «እስራኤላዊያን ነን» አሏቸው። ከዚያ በኋላ «በምን ጊዜ ነው የተሰወራችሁ?» አሏቸው። «በኤልያስ ዘመን ነው የሰወረን።» የተሰወሩት ቅዱሳን የተገለጹት ለጌታ እና ለእመቤታችን ለመስገድ ነው። በኤልያስ ዘመን አክአብና ኤልዛቤል ካህናትን ሲያስገድሉ ኤልያስ «ካህናትህንም ገደሉ፤ መሰዊያህንም አፈረሱ እኔ ብቻየን ቀረሁ» ብሎ ኤልያስ በሚጸልይ ጊዜ ለበአል ያልሰገዱ ሰባት ሽህ ሰዎች አስቀርቼልሀለሁ ያለው እነዚህን ጨምሮ ነው። ከዚያ በኋላ እየተዛወሩ «ይህች አገር ኢያሪኮን ትመስላለች፤ ያች ኤፍራታን ትመስለኛለች» እያለች በእየሩሳሌም አካባቢ በኅበኘችው አገር ምሳሌ ሰጠች።

በዚህ ባህር ውስጥ አራት ነገስታት የሚገዙት አገር አለ ይባላል። ከዚያ በኋላ ገብርኤል መጥቶ ባህሩን ለሁለት ከፍሎላት ገባች። አገሩን አየች፤ የሰዎቹንም ኑሯቸውን አየች። በአለም ቸነፈር ሲታዘዝ ከዚህ ከባህር ውስጥ የቸነፈር ንጉስ እንዳለ ተገልጿል። እመቤታችንም ይህን ሁሉ አይታ ተደሰተች።

በዚህ ቦታ ሦስት ወር ከአስር ቀን ከተቀመጡ በኋላ መልአክ እግዚአብሄር ተገልፆ «ሄሮድስ ሞቷል አገሩ ሰላም ሆኗል ተነሱ ወደ አገራችሁ ሂዱ» አላቸው። «እመቤታችንም አይ አልሄድም እየሩሳሌም አገሬ ሰዎቹ ክፉ ናቸው፤ ከስደት ከርሀብና ከጥም በቀር ያገኘሁት ነገር የለም። ይህችን የመሰለች አገርማ እኔ ትቼ አልሄድም፤ እነዚህን ቅዱሳን አልለይም።» «አይ እንደዚህ አይደለም ልጅሽ የመጣው አለምን ለማዳን ነው። ተነሽ ተባለች»፤ ጌታም አምስት ዓመት ሞልቶት መናገር ጀምሮ ነበር። «እንሂድ እናቴ ወደ አገራችን በዚያ ነው ብዙ ሥራ የምሰራው» ብሎ አላት።

ከዚያ በደመና ተጭነው ባህሩን ወጡ ከዚያ ጻና በተባለው ባህሩ ጻና ተባለ። ኢትዮጵያንም ከዳመናው ላይ ሆና አስባረከች። «እንግዲህ ይህች አገር አስራት ትሁንሽ እስከ ዕለተ ምፅአት ድረስ ተዋህዶ ሃይማኖት አይጠፋባትም፤ ይህች አገር ያንችን ስም እና የእኔን ስም አብዝተው የሚጠሩ ብዙ ቅዱሳን ይወለዳሉ» አለ። ከዚህ በኋላም እናቱ በጣና ቂርቆስ ደሴት በ24 ሰዓት አንድ ጊዜ እንድትጐበኝ መነኰሳቱን እንድትባርክ፣ ይህን የተሳለመና የረገጠ ኢየሩሳሌም ሄዶ የመቃብሩን ቦታ እንደተሳለመ እንደሚቆጠርለትና እስከ መቶ ትውልድም እንደሚምር ቃል ኪዳን ገባላት። ከዚያም ወደ አገራቸው ሄዱ።
ምንጭ፣ (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992 ፡ 17-21፤መምህር ክፍለ ማርያም፣ካሴት ቁጥር4B፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ጣናቂርቆስ ገዳም)።

## ተረክ ሦስት

ከሳቴ ብርሃን የተባለ አባ ሰላማ በኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ በተሾመ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በአክሱም ከተማ ተቀምጦ ሳለ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የፀናች ክብርት እመቤታችን ተገለፀችና«ወደ ጣና ደሴት ሂደህ በዚያ ሰዎችን አጥምቅ፣ የክርስትናም እምነት አስተምር። ደጋግና ቅዱሳን የሚሆኑ የኢትዮጵያ ነገሥታት አብርሃና አፅብሐም ከሠራዊቶቻቸው ጋር ሆነው ከአንተ ጋር ይሂዱ ዘንድ ንገራቸው»አለችው።

ከሳቴ ብርሃንም ለአብርሃና ለአፅብሃ እመቤታችን እንደተገለፀችለትና እንዳዘዘችው ነገራቸው። አብርሃና አፅብሐም ይህንን በሰሙ ጊዜ ፈፅመው ደስ ተሰኝተው «ወደ ታዘዘው ቦታ ከአንተ ጋር ለመሄድ ዝግጁ ነን» አሉት።

ከዚህ በኋላ ብዙ ሠራዊት አስከትለው ወደ ጣና ደሴት ለመሄድ ጉዞ ጀምሩ። ከዚያም ከጣና የባህር ወደብ በደረሱ ጊዜ ከባህሩ ዳርቻ ድንኳናቸውን ተክለው በዚያ ሠፈሩ። አባ ሰላማም ከዚያ ከደረሱ በኋላ «በምን ላጥምቅ?» ብለው ጌታን ጠየቁ። ጌታም ማጥመቂያ መስቀል፣ በማዕጠንት ጊዜ የሚያዝ መስቀል፣ ቀብአሜሮን፣ ፀሎተ እጣን፣ መጽሐፈ ክርስትና፣ መጽሐፈ ቅዳሴ፣ መጽሐፈ 4ቱ ወንጌላት፣ 5 የአልባሳት ወርቀ ዘቦ ሰጥቷቸዋል።

ወደምስራቅ ካለው የጣና ሐይቅ ላይ አህዱ አብ ብለው ሲባርኩ 7ቱ ሰማያት ተከፍተው መላዕክት ረበውበት ታየ። አምደ ብርሃን ተተክሎ 7 ቀናት ያህል በሌዋውያን ካህናት ተጽዕኖ ምክንያት በአክሱም ሳይጠመቁ ቆይተው በቅድስት ማርያም አሳሳቢነት ወደ ጣና ቂርቆስ ከሄዱት ነገሥታት ጋር ሕዝቡን አጠመቁ።

መንፈስ ቅዱስ በእሳት ነበልባል አምሳል በጣና ባህር ላይ ወርዶ ስለቀደሳት የጣና ባህር ልክ እንደዮርዳኖስ ባህር የተቀደሰች ሆነች።

አብርሃና አፅብሐ ከሳቴ ብርሃን ከተባለ አባ ሰላማ ጋር ሥርዓተ ጥምቀቱን ለማስፈፀም ትምህርተ ሃይማኖትን ለማከናወን ለሦስት ዓመት ያህል በዚያው ከተቀመጡ በኋላ ርዕሰ ከተማቸው ወደምትገኝበት ወደ አክሱም ለመሄድ ተነሱ።

ሲሄዱም አባ ሰላማ የሚባል ከሣቴ ብርሃን ከኢየሩሳሌም ከአቡነ ጴጥሮስ የተቀበሉትን ካባ ከሰማይ የወረደላቸውን የማጠኛ መስቀል አስቀምጠውታል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ጣና ደሴት ተመልሰው፣ ሕዝቡን አሰባስበውና ባርከው «የእረፍቴ ቀን ደርሷል እመቤታችን እንደነገረችኝ ወንዶች፣ ደሴተ ጸአና እያገለገላችሁ ተቀመጡ። ሴቶችን ደምበዛ ተቀመጡ ብለው ሴቶቹ ከወንዶች ገዳም እንዳይገቡ ሥርዓት ደነገጉ። ይህንንም የጣሰ ቢኖር እስከ 12 ትውልድ የተረገመ ይሁን አሉ።» በኋላም ሕዝቡን በ4 ማዕዘን ባርከው ከሰማይ የወረደላቸውን በትረ መስቀል ከመሬት ተክለው አርፈዋል። ቅስና፣ ዲቁና የሰጧቸው ካህናትና ዲያቆናት በክብር ገንዘው ወደ ቤተ መቅደስ አስገብተዋቸዋል። አፅማቸውም እስከዛሬ ድረስ አለ። ያሬድም በዚህ ቦታ ከሁለት ዓመት በላይ ተቀምጦ ምልክት አልባውን ድጓ ለመፃፍ በቅቷል።

ምንጭ፣(ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡ 10-15፤መምህር ክፍለ ማርያም፣ካሴት ቁጥር4B፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ጣናቂርቆስ ገዳም፣)

## ተረክ አራት

እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ዋልድባ ገዳም ከማህበረ መነኰሳቱ ጋር ስታገለግል ከቆየች በኋላ ትልቅ ደዌ አመማት። ከዚያው ገዳም ያሉት መነኰሳት ተጨነቁ፤ አዘኑ። መነኰሳቱ ወደ እመቤታችን ሲፀልዩ ለአንዲት ፈላሴት መነኩሴ ተገልጻ ወደ ደምበዛ ቁስቋም ውሰዷት አለች። እነሱም እመቤታችን እንደነገረቻቸው አልጋ አበጅተው ተሸክመው ይዘዋት ሲመጡ "ተውኝ አውርዱኝ እመቤታችን ፈውሳኛለችና" ብላለች። ይህንን እንደተናገረች አወረዷት። ሲያወርዷት አስቀድሞ ደዌ እንዳነካት ሆነች። ከዚያም ማህበረ መነኰሳቱ ተሰነባብታ እመቤታችን እየመራቻት ሚካኤልና ገብርኤል እየተከተሏት ደሴት ፀአና ደረሰች።

ከደረሰችም በኋላ "እመቤቴ ሆይ እግርሽ ከረገጠበት ልጅሽ ከባረከበት ቦታ ያደረስሽኝ ክብር ምስጋና ይድረስሽ"፣ ደሴቱን፣ ውሃውን፣ ተራራውንና ድንጋዩን እያየች እያመሰገነች ከቆየች በኋላ እመቤታችን "ከምን ቦታ ከየት ገብቼ ነው የምፀልየው?"

እያለች ውዳሴ ማርያም ከሀሙስ ላይ ስትደርስ እመቤታችን ሰሎሜን፣ ኤልሳቤጥን፣ እናቷን ሀናን፣ ከአጋንንት ጋር ተዋግተው ድል የነሱ ደናግልንና መነኰሳትን አስከትላ "የተባረክሽ፣ የተቀደስሽ ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ እንዴት ነሽ! በመድኃኔዓለም ፈቃድ ከዚህ ቦታ ደረስሽ። የእኔም ፈቃድ ሆኖ ውሃዎች ከተባረኩበት፣ እንጨቶች ከማይደርቁበት ከዚህች ከተቀደሰች ቦታ አድርሼሻለሁ፤ ደስ ይበልሽ ብዙ ገዳማት አድባራት አሉ። ከነዚህ ሁሉ መርጬ ፀአና አድርሼሻለሁ። ይህም ደሴት ልጄ በፈቃዱ አምጥቶ 3 ወር ከ10 ቀን ተቀምጬበታለሁ። በዚህም ደሴት ላይ የሚኖሩ መነኮሳትንና መነኮሳያትን ቀንም ሌትም መጥቼ እጐበኛቸዋለሁ። አንቺም ከዚህ ቦታ ፈቃዴ ነውና ተቀመጪ" ብላት ተሠወረች።

ወለተ ጴጥሮስም እመቤታችን እንደተሰወረቻት አውቃ 3 ሱባኤ ገባች። በ3ኛው ሱባኤ እመቤታችን ሚካኤልንና ገብርኤልን አስከትላ መጣች። "ወዳጄ ወለተጴጥሮስ ፈቃድሽን ልፈፅምልሽ መጥቻለሁ እና ንገሪኝ" አለቻት። ቡርክት ወለተ ጴጥሮስም ለእመቤታችን ሰገደችና "አበው የተቀበሩበት መቅደስ ፀአና 3 ብርሃን ተተክሎበት አየዋለሁና መላዕክት ሲወጡባት ሲወርዱባት አየዋለሁና ከዚህ መቅደስ ገብቼ ልሳለም እልሻለሁ" አለቻት።

እመቤታችንም "ልጄ በስልጣኑ በአቡነ ሰላማ ከሳቴ አድሮ ከዚህ ደሴት ፀአና እናቶች እንዳይገቡ አውግዟል። ለአንቺ ለወዳጄ ወለተ ጴጥሮስ ግን የልጄ ፈቃድ ሆኖ ወደ ደምበዛ ቁስቋም እንድትገቢ ተፈቅዶልሻል" አለቻት። እመቤታችን ለወለተጴጥሮስ ይህን ስትላት ሚካኤልና ገብርኤል በክንፋቸው ወስደው አስቀምጠዋት ተሰወሩ።

ወደ ደምበዛ ቁስቋም ገብታ ቆማ «ውዳሴሃ ለእግዚትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ»ብላ ስትፀልይ ከኢየሩሳሌም በሉቃስ እጅ የተሳለች ስዕል በቀይ ቀለም በቢጫ ቀለም በአረንጓዴ ቀለም በጥቁር ቀለም በፀአና ቤተ መቅደስ የነበረችው ስዕል ከፊቷ ላይ መጥታ ተቀመጠች።

እሷም ደንግጣ ወደቀች። «እመቤታችንም ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ሆይ ለምን ትደነግጫለሽ? ብዙዎች እናቶች አባቶች ሲፀልዩ ይህንን አላደረግሁላቸውም ለአንቺ ያደረግሁልሽ ወዳጄ ስለሆንሽ ነው ተነሽ አለቻት»።

ቆማም «እመቤቴ ሆይ ለኔ ለሀጢያተኛዋ ይህንን ላደረግሽልኝ ምስጋና ይገባሻል» ብላ ሰገደችላት። «ይህችንም ስዕል ለአንቺ ሰጥቼሻለሁ ትፀልይባት ዘንድ ልመናሽንም ሁሉ በዚህ ስዕል እቀበልሻለሁ» ብላ ተሠወረች።

መነኰሳቱም ተሰብስበው ከቤተክርስቲያን ግቢ ሲደርሱ ከጣና መቅደስ የነበረችው ስዕለ ማርያም ቁማ አዩአት። እነሱም «ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ነው» ብለው አለቀሱ። ስዕለ ማርያሟም አፍ አውጥታ« በፈቃዴ እንጂ ሰው አላመጣኝም» ብላ መለሰችላቸውና ወደ ገዳማቸው ተመለሱ።

በዚያ ገዳም ለስምንት አመታት ካገለገለች በኋላ የገዳሙ እመምኔት እማ ክርስቶስ አረፈች። ወንበር ዝም ብሎ ስለማያድር ሰው እንምረጥ ብለው ከተነጋገሩ በኋላ«ሥላሴ የወደደውን ይሹምልን» ብለው ወደ እመቤታችን አመለከቱ። እመቤታችንም ለአንዲት ፈላሲት ተገልፃ "የተባረከች ወለተ ጴጥሮስ ናት ገዳሙን የምታገለግለው" ብላ ነገረቻት።

ያችም ፈላሴት ወደ ፀሎተ ማዕድ ሂዳ ለአባቶች ተናገረች። እንደተባሉትም አደረጉ። እሷም በእመቤታችን በታዘዘችው መሠረት ሚካኤል፣ ገብርኤልና ሰባቱ ሊቃነ መላዕክት እየረዷት ቤተክርስቲያኑን አሠራች። በኋላም የመድሃኔአለም ፈቃድ ሆኖ የሬማ መድኃኔአለም ቤተክርስቲያንን ላሰራ ልሄድ ነውና ብላ ለፍቅርተ ክርስቶስ የመነኮሳቱን ከብቱን፣ ንብረቱን፣ ንዋየ ቅድሳቱንና የስዕል ቤቱን አስረከበቻትና «እኔ እንደምሰራው ስራ አትደንግጭ አትፍሪ እኔም እየመጣሁ በወር በወር እጠየቅሻለሁየአበው በረከት አይለይሽ በደምበዛ ቁስቋም ቅዳሴ በአመት 4 ጊዜ ስለሆነ ያንንም የሚቀድሱት ድንግሎች ከእናታቸው ከአባታቸው በአስራ ሁለት አመታቸው የተለዩ በጋብቻ ያልተወሰኑ ናቸው ይህንን ስርዓት ያገኘሁት ከብፁዕ አባታችን ከአባ ሰላማ ቃል ነው በዚህ መሰረት ሲጠበቁት ቆይቶ እስከ ዛሬ ደርሷል። አንችም በዚህ ሕግ እየሰራሽ እናቶችን ለመንግስተ ሰማያት አብቂያቸው»ካለች በኋላ ወደ ሬማ መድኃኔአለም ሄደች። እሷም የሚሰራበትን ቦታ ደሴቱን እየዞረች «ጌታየ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ከዋልድባ ገዳም ወደ ጣና ገዳም እንድገባ ብዙም እንድሰራ ፈቀድክልኝ የዋልድባ ገዳም አንተ የባረከው ነው። እህል ውሃ ኃጢአት አይግባብሽ ያልከው ቃልኪዳኑም እስከ 70 ትውልድ የሚማርበት ቦታ ነው ከዚያም አወጣኸኝ

በደሴተ ደምበዛ ቁስቋም አንተ ወርደህ በእናትህ ጀርባ ታዝለህ የረገጥከው እናትህ የተመላለሰችበት አረጋዊ ዮሴፍ ሰሎሜ የተቀመጡበት አንተ በእናትህ እቅፍ ተቀምጠህ መላ ኢትዮጵያን የባረክበት ለእናትህ ለድንግል ማርያም ኢትዮጵያን አስራት በኩራት አድርገህ የሰጠህበት ቦታውን የረገጠ ሰው 100 ትውልድ እምርልሻለሁ ብለህ ቃል የገባህለትን ቦታ አስለቅቀህ ወደ ሬማ መድኃኔአለም አመጣኸኝ »በማለት ከጸለየች በኋላ ሬማ መድኃኔአለምን ቤተክርስቲያን አሰራች።

ምንጭ፣ (ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም፣ 1992፡2-10፤መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር4B፣ ግንቦት26 ቀን 2002፣ ጣናቂርቆስ ገዳም፣)

## ተረክ አምስት

ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ወደዚህ አካባቢ ሲደርስ፣ እርሱ ድንኳኑን በህሙሲት አካባቢ ጥሎ ፈራሻማል የሚባለውን ቢትወደዱን ከሰባት መቶ ታንኳ ሰራዊቱ ጋር ብዙ ቅርስ አላቸው የተባሉትን የጣና ደሴት ገዳማትን እንዲዘርፍና መነኰሳቱንም እንዲገድል ላከው። ቢትወደዱም ከነሠራዊቱ የተወሠኑትን ገዳማት ዘርፎና አቃጥሎ፣ መነኰሳቱንም ገድሎ ወደ ጣና ቂርቆስ ሲገሰግስ በርቀት የተመለከቱት የገዳሙ አበምኔት አባ ኤልያስ ወደ ጣና ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ገብተው እጃቸውን በትምህርተ መስቀል አምሳያ አድርገው ታላቅ ለቅሶ አለቀሱ። ሕፃኑ ቂርቆስንም "ጠላት ሊያጠቃን መጥቷልና ከአምላክህ ዘንድ በ3 ዓመት ከ3 ወርህ የተሠጠህን ቃል ኪዳን አስብ፣ ገዳሙንና እኛንም ከጠላት አድነን" ብለው ለመኑ። ሕፃኑ ቂርቆስም ወዲያውኑ ፈርኦን ከነሠራዊቱ በሙሴ አማካይነት በባህሩ ሰምጠው እንደቀሩት ነፋስ አስነስቶ ሰባት መቶ ታንኳዎች ከነሠራዊቱ አስጥሞ አጠፋቸው። ግራኝም ከባህሩ ሽታ የተነሣ ድንኳኑን ነቅሎ ወደ ጎንደር ሄደ።

ምንጭ፣(ጣና ቂርቆስ ታሪካዊና ጥንታዊ የአባቶችና የእናቶች አንድነትገዳም፣ 1992:25 -26)

## ተረክ ስድስት

አባ ሰላማ የአካባቢውን ሕዝብ እንዲያጠምቅ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሠጠው መስቀል በገዳሙ ውስጥ መስዋዕተ ሀዲስ ይሠዋበት ነበር ተብሎ በሚታመንበት ድንጋይ አጠገብ ምልክት ይሆን ዘንድ ተተክሎ ይኖር የነበረ ሲሆን አንድ ዕለት አንድ መነኩሲ ሠርቆ ወሰደው። ቅዱስ ቂርቆስም ለመነኩሴው በሕፃን ልጅ ተመስሎ «ሳላጠፋህ ዕቃዬን መልስ» እያለ በሕልሙ ታየው። መነኩሴውም በነገሩ ፈርቶ ከገዳሙ በግምት ግማሽ ኪሎ ሜትር ላይ በምትገኘው ክርስቶስ ሰምራ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ አምጥቶ ተክሏት ሄዷል። በዚያም ቦታ ለረጅም ጊዜያት ተተክላ ከኖረች በኋላ ሌባ እንዳይወስዳት ተብሎ ወደ ጣና ቂርቆስ ገዳም ዕቃ ቤት እንድትገባ ተደርጓል።

ምንጭ፣ (መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር4A፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ ጣናቂርቆስ ገዳም)

## ተረክ ሰባት

አፄ አምደ ፅዮን ጦርነት ሲገጥሙ የቂርቆስን ታቦት ይዘው ስለሚሄዱ በተደጋጋሚ ድል ይቀናቸው ነበር። በአንድ ወቅት በዘመቻው ድል አድርገው ሲመለሱ ታቦቱን ከቤተ መንግሥቱ ወደ ገዳሙ ላለመመለስ መወሰናቸውን ለመኳንንቱ ተናገሩ። መኳንንቱም «ይህን ታቦት ወደ ቦታው ካልመለሱ ሃይለኛ ስለሆነ በሠራዊቱ ላይ አንድ ነገር ያስመጣበዎታል ወይም ጦር ያስነሳበዎታል» አሏቸው። ንጉሱም ሁኔታውን ለማወቅ በገዳሙ መነኰሳት ሱባኤ አስያዙ። ቅዱስ ቂርቆስም ወደ ቦታው መመለስ እንደሚፈልግ ለመነኰሳቱ በራዕይ አሳየ። ንጉሱ ታቦቱን ወደ ገዳሙ ሲመልሱ በመኳንንቱ ምክር ተነሳስተው መጐናፀፊያውን አስቀሩት። ቂርቆስም በሕልም ተገልፆ «ሃይል ብሰጥህ እንዴት ይህን ታደርጋለህ?» በማለት ንጉሱን ወቀሳቸው። ንጉሱም መልዕክተኞቹን ልከ መጐናፀፊያውን እንደመለሱ ይነገራል።

ምንጭ፣ (መምህር ክፍለ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር4A፣ ግንቦት26 ቀን2002፣ ጣናቂርቆስ ገዳም)

## ተረክ ስምንት

በጣና ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ክልል ውስጥ በነዳጅ የሚሠሩ ጀነሬተር፣ ወፍጮና የመሳሰሉት ነገሮች ገብተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ አይፈቀድም። የዚህ ምክንያቱ በአንድ ወቅት ገዳሙ በሞተር በሚሠራ ወፍጮ በቤተክርስቲያኑ አካባቢ ቢተክል ሞተሩ አይሠራ በማለቱ ነው። በወቅቱ ወፍጮው ከቦታው ተነስቶ ከሴቶች ገዳም ሲተከል ሠራ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቅ.ቂርቆስ በሞተር የሚሠራ ነገር ፍላጐቱ አይደለም ተብሎ ስለታመነበት ለቅዳሴ ጊዜ የሚያገለግል መብራት ለማስገባት ሲታሰብ በፀሐይ ብርሃን የሚሠራ እንዲገባ ተደረገ።

ምንጭ፣ (አባ ወልደ ተንሳይ፣ሚያዝያ 22 ቀን 2003፣ ጣና ቂርቆስ ገዳም)

አባሪ ሁለት

የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

ሀ. የቁልፍ መረጃ አቀባዮች «ፕሮፋይል»

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | መኖሪያ አካባቢ | የስራ ድርሻ | መረጃ የሰጡበት ቀን | የሰጡት መረጃ አይነት | መረጃው የተያዘበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አባ ባዬ | ወ | 67 | ጣና ቂርቆስ ገዳም | የገዳሙ እቃ ጠባቂ | 25/9/02 | ስለ ገዳሙ ታሪክ፣ ስርዓትና ቁሳዊ ባህሎቹ | በቴፕ ሪከርደርና በእጅ ማስታወሻ |
| 2 | መምህር ክፍለ ማርያም | ወ | 31 | » » » » | የገዳሙ የቅኔ መምህር | 26/9/02 | ስለ ገዳሙ አመሰራረትና ስለተረኮቹ | በቴፕ ሪከርደርና በእጅ ማስታወሻ |
| 3 | አባ ተክለ ሥላሴ | ወ | 29 | » » » » | መጋቢ | 22/8/03 | ስለገዳማዊያኑ የዕለት ከዕለት ሕየወት፣ የምግብ ዝግጅት | በቴፕ ሪከርደርና በእጅ ማስታወሻ |
| 4 | አባ ወልደ ገብርኤል | ወ | 35 | » » » » | የገዳሙ ፀኃፊ | 25/9/02 | ስለገዳሙ አስተዳደራዊ መዋቅርና የምርጫ ሂደት | በቴፕ ሪከርደርና በእጅ ማስታወሻ |

## ለ.ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | መኖሪያ አካባቢ | የስራ ድርሻ | መረጃ የሰጡበት ቀን | የሰጡት መረጃ አይነት | መረጃው የተያዘበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አባ ወልደ መድህን | ወ | 34 | ጣና ቂርቆስ ገዳም | ካህን | 22/8/03 | ስለገዳሙ ስርዓትና ዘጠኙ ቤተመቅደስ | በእጅ ማስታወሻ |
| 2 | አባ ወልደ ተንሳይ | ወ | 37 | ጣና ቂርቆስ ገዳም | ካህን | 22/8/03 | ስለገዳሙ ስርዓትና ስለ ቂርቆስ ገድላት | በእጅ ማስታወሻ |
| 3 | አባ ገ/ፃድቅ | ወ | 63 | ጣና ቂርቆስ ገዳም | ዘበኛ | 25/9/02 | ስለ እንግዳ አቀባበል | በእጅ ማስታወሻ |
| 4 | አባ ተክለ ማርያም | ወ | 29 | ጣና ቂርቆስ ገዳም | እረኛ | 24/9/02 | ስለ በሬዎቹ ወደ ገዳሙ የመግባት ምክንያትና ስለርቢ በጎቹ | በእጅ ማስታወሻ |
| 5 | አቶ ባዘዘው መስፍን | ወ | 37 | አንበሳሜ/ደራ | የባህልና ማስታወቂያ ኃላፊ | 22/9/02 | ስለቦታ ስያሜዎቹና ስለ ቁሳዊ ባህሎቹ | በቴፕ ሪከርደርና በእጅ ማስታወሻ |
| 6 | አቶ አብርሃም ማርጌ | ወ | 51 | ባህርዳር | የፓርክ ባለሙያ | 11/8/03 | ስለ ጣና ገዳማት ስሪት | በእጅ ማስታወሻ |
| 7 | ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ | ወ | 38 | አዲስ አበባ | የማህበረ ቅዱሳን የህትመትና ሚዲያ ኃላፊ | 13/7/02 | ስለ ገዳሙ ስርዓት | በእጅ ማስታወሻ |
| 8 | አቶ ብርሃን ደግፌ | ወ | 35 | ባህር ዳር | የገዳሙ የልማት ኮሚቴ | 16/9/02 | ስለገዳሙ የልማት እንቅስቃሴ | |

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት በማሟያነት የቀረበው ጥናት የኔ መሆኑንና ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በሙሉ በተገቢው ሁኔታ የገለፅኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም ምሕረት ተስፋዬ

ፊርማ ________________

ቀን ሰኔ 29/2003 ዓም.